# የሙናፊቆች ምስጢር

*እነርሱ የሚጠሉትን ለአላህ ያደርጋሉ፤ መልካም (ፍፃሜ) እንደሚኖራቸውም ምላሶቻቸው ይቀጥፋሉ፡፡ እሳት የተዘጋጀላቸውና ከማንም በፊት ወደርሷ በጥድፊያ የሚነዱ መሆኑ ቅንጣት አያጠራጥርም፡፡ (አል–ቁርአን፣ ሱረህ አን–ነሕል፡62)*


ዝግጅት፡- ሃሩን የሕያ

ትርጉም፡- ዐብዱር-ረሒም



ሚያዝያ 2004

**መጽሐፉ የሕትመት መብት የለውም**

**አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**

<u>አስተያየት ካልዎት</u>

**ማውጫ**

# አርዕስት

ገጽ

1. መግቢያ..............................
2. ሙናፊቆች የሰይጣን ጭፍሮች ናቸው .................
3. ለምን ሙናፊቆት ከአማኞች ጋር በመቆየት
የአምልኮ ተግባራትን ይፈጽማሉ? .............
4. የሙናፊቆች ባህሪያት .......................
5. የሙናፊቆች በራስ ሙብቃቃት .................
6. በራስ ሙብቃቃት በሽታ ምክንያት የሚመጣ ችግር ..........
7. ሙናፊቆች በፍጹም በነብያት ላይ ድል አልተቀዳጁም.........
8. በሙናፊቆች ላይ ልኖረን የሚገባ ባህሪይ ...............
9. ሙናፊቅ ተውበት ማድረግ ይችላልን? ...............
10. በቀጣዩ ዓለም ሙናፊቆች የሚኖራቸው ገጽታ .............
11. ማጠቃለያ .........................

# መግቢያ

*ከሰዎች መካከል "በአላህና በመጨረሻው ቀን መኖር አምነናል" የሚሉ (ወገኖች) አሉ፡፡ ፈጽሞ አማኞች አይደሉም፡፡ አላህንና እነዚያን ያመኑትን ሊያታልሉ ይሞክራሉ፡፡ ራሳቸውን እንጂ ሌላ ማንንም አያታልሉም፡፡ ግና ይህን አይገነዘቡም፡፡ ልቦናቸው ውስጥ በሽታ አለ፡፡ አላህ በሽታን ጨመረላቸው፡፡ ይዋሹት በነበረው አሳማሚ ቅጣት ይጠብቃቸዋል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡8-10)*

ለበርካታ ሰዎች አስመሳይ (ሙናፊቅ) የሚለው ቃል ምንም ማለት አይደለም፡፡ ጥቂቶች በዕለት ዕለት ንግግራቸው እንደሚጠቀሙት ሁለት ፊት ወይም ውሸታም በሚል ይፈቱታል፡፡ ሆኖም በቁርአን ውስጥ የተሰጠውን ትርጉም አይረዱም፡፡ በሌላ በኩል ጥቂት የዲን ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ሙናፊቆች በረሱል (ሶ.ዐ.ወ) ዘመን ይኖሩ የነበሩ ከሀዲያን ይመስሏቸዋል፡፡

ሆኖም እውነታው ሙናፊቆች አላህ (ሱ.ወ) በመቶ በሚቆጠሩ የቁርአን አንቀጾች የገለፃቸውና ከነርሱም እንድንጠነቀቅ ያሳሳበን ስብስቦች ናቸው፡፡ ሙናፊቆች አልፎ አልፎ የሚገኙ ሳይሆኑ ይልቁንም በሁሉም የአማኞች ሕብረተሰብ ውስጥ "የተደራጁ" መሆናቸውን ከቁርአን እንረዳለን፡፡

ቁርአንን ስንመለከት ይህ የንፍቅና ሁኔታ በሁሉም ጊዜያት እንደሚሠራ እንረዳለን፡፡ ነብዩ ሙሳን (ዐ.ሰ) ለተከተሉት፣ በነብዩ ሱለይማን (ዐ.ሰ) ላመኑት፣ ለነብዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ) ማሕበረሰብ፣ ከአንድ ሺህ አራት መቶ ዓመታት በፊት ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ) ባጭሩ ማንኛውም ቁርአን የጠቀሰው ሙስሊም ማሕበረሰብ ውስጥ ሙናፊቆች ነበሩ፡፡ የዚህም ምክንያት የቁርአን አንቀጹ እንደሚገልጸው፡-

*ይህ በቀደምቶች ላይም ተፈፃሚ ይሆን ዘንድ አላህ የፈቀደው ልምድ ነው፡፡ አላህ ባጸደቀው ልምድ ላይ ለውጥን አታገኝም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አሕዛብ፡62)*

አላህ (ሱ.ወ) ሁሉንም የምእመናን ማሕበረሰብ በተመሳሳይ ሁኔታ ይፈትናል፡፡ ማንኛውም የምእመናን ማሕበረሰብ ውስጥ ያለ ጥርጥር የሙናፊቅ ስብስቦች በውስጡ ይገኛሉ፡፡ ይህ የማይቀየረው የአላህ (ሱ.ወ) ሕግ ነው፡፡

ስለዚህ አላህ (ሱ.ወ) በብዙ የቁርአን አንቀጾች ለምእመናን አደጋ ስለሆነው ስለዚህ ቡድን ባህሪይ ይገልፃል፡፡ በዚህም ምክንያት ሙናፊቅ በቁርአን ለበርካታ ጊዜ ከተጠቀሱት የሰው ዓይነቶች አንዱ ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ሕይወታቸውን በሙሉ ለአላህ (ሱ.ወ) ከሰጡት ቅን አማኞች ጋር ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ሕይወታቸውንና ንብረታቸውን መስዋዕት በማድረግ በአላህ (ሱ.ወ)

መንገድ የሚታገሉትን ለማስመሰል ይጥራሉ፡፡ ነገር ግን በፍጹም እንደ ምእመናን አይደሉም፡፡ የሚጨነቁትም ለራሳቸው ጥቅም ብቻ ነው፡፡ ይህ ቡድን በታሪክ ውስጥ በእያንዳንዱ እውነተኛና ታማኝ የአማኝ ማሕበረሰብ ውስጥ ታይቷል፡፡ በርግጥ ከላይ እንደተጠቀሰው ቁርአን ነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) አጠቃሎ በበርካታ ነብያት (ዐ.ሰ) ጊዜ ስለነበሩ ሙናፊቆች በርካታ መረጃን ይሰጣል፡፡

በዚህ መጽሐፋችን በቁርአን በጥልቀት በተገለጸው መሠረት የሙናፊቆችን ባህሪይ አንድ በአንድ እንቃኛለን፡፡ በመቀጠል ትኩረታችንን ሙናፊቆች የሚሰቃዩበት ዋነኛ ጉድለት የሆነውን የራስ መብቃቃት ላይ እናደርጋለን፡፡

በቀጣይ ምዕራፎች በጥልቀት የምንዳስሰው በራስ መብቃቃት የተባለውን በሽታና አንዱ የሙናፊቆች መለያ ባህሪይ የሆነውን ነው፡፡ ማንኛውም የሙናፊቅ ባህሪይ ያለው ሰው የሚጎድለው ነገር እንደሌለና ሁሌም በትክክለኛው መንገድ ላይ እንዳለ ይናገራል፡፡ በዚህም ምክንያት በአንቀጹ እንደተጠቀሰው ሙናፊቆች ወሰንን ያልፋሉ፡፡

*በእውነቱ የሰው ልጅ ወሰንን ያልፋል፡፡ የዚህ ምክንያቱ ራሱን የተብቃቀ አድርጎ ማየቱ ነው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ዐለቅ፡6-7)*

የተለጎመ ተፈጥሮአቸውና ክህደታቸው ያለማቋረጥ ይጨምራል፡፡ እራሳቸውን ከሁሉም በላይ እንደሆኑና ከማንኛውም ፍላጎት ነፃ ነን ብለው ስለሚያስቡ የአላህን ትዕዛዝ ማክበርም ሆነ ምክር መቀል አይችሉም፡፡

## የከህዲያንና የሙናፊቆች ልዩነት

*(ሙሐመድ ሆይ!) ብዙዎቹ ሰዎች እንዲያምኑ ጉጉት ቢኖርህም አማኞች አይሆኑም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ዩሱፍ፡103)*

ከላይ ያለው አንቀጽ እንደሚነግረን አብዛኞቹ ሰዎች እምነት የላቸውም፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) የማያምኑት ምንጊዜም ከአማኞች በቁጥር የበረከቱ ናቸው፡፡ ይህ "ከህዲያን" የሚባለው ቡድን አላህን በግልጽ የካዱትን፣ ጣዖታዊያንና ልባቸው ላይ በሽታ ያለባቸውን፣ እንዲሁም ሙናፊቆችን ያጠቃልላል፡፡ ሁሉም የሚጋሩት አንድ ባህሪይ አላህን እንደሚገባው አለመፍራታቸውና ሕይወታቸውን በአላህ (ሱ.ወ) መጽሐፍ መሠረት አለመምራታቸው ነው፡፡ ሆኖም ከከህዲያን ቡድን ውስጥ አላህ (ሱ.ወ) እንደሚከተለው የገለጸው አንድ ቡድን ይገኛል፡፡

*መናፍቃን ከእሳት የታችኛው አዘቅጥ ውስጥ ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡145)*

ታዲያ ምን ዓይነት ልዩነት ነው ሙናፊቆችን ከሌሎች ከሀዲያን የባሰ ቅጣት እንዲገባቸው ያደረገው? ከሀዲ በአላህ (ሱ.ወ) አያምንም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) መኖሩንና እንዲሁም ቁርአንን አይቀበልም፡፡ ነገር ግን ሙናፊቅ አላህን በቀጥታ አይክድም፡፡ ከዚህ በተቃራኒ በአላህ (ሱ.ወ) ዲንና በቁርአን እንደሚያምን ይናገራል፡፡ አላህን ከሚክዱት በተቃራኒ ሙናፊቅ ክህደቱን በመደበቅ አማኝ ለመምሰል ይናገራል፡፡ አላህን እንደሚፈራና እምነት እንዳለው ያስመስላል፡፡ ሆኖም በቁርአን አንቀጾች ሙናፊቅ እውነት እንደማይናገርና እውነተኛ የአማኝ እምነት ልቡ ውስጥ እንደሌለ ተጠቅሷል፡፡ በሱረህ አል-በቀራህ ተከታዩ ተገልጿል፡-

*ከሰዎች መካከል "በአላህና በመጨረሻው ቀን መኖር" አምነናል የሚሉ (ወገኖች) አሉ፡፡ (ሱረህ አል-በቀራህ፡8)*

ሙናፊቅ እምነት አለኝ ስለሚል በቅን የምእመናን ማሕበረሰብ ውስጥ ይገኛል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሙሉ ሕይወቱን ከነርሱ ጋር ያሳልፋል፡፡ ነገር ግን ክህደቱን ስለሚደብቅ በአላህ (ሱ.ወ) በእውነት ያመኑትን ለመጉዳትና እምነታቸው እንዲቀንስ ለማድረግ ሁልጊዜም በምእምናን መካከል ጥል እንዲነሳ ይፈልጋል፡፡ ይህ ጠብ አጫሪ የሙናፊቆች ፀባይ በቁርአን ውስጥ እንደሚከተለው ተጠቅሷል፡-

*መናፍቃንና እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ያለባቸው ወገኖች "አላህ እና መልዕክተኛው የገቡልን ቃል ኪዳን ባዶ (ቅዠት) ነበር" ባሉ ጊዜ የሆነውንም አስታውስ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አሕዛብ፡12)*

*ጠላት በከተማዋ የተለያዩ አቅጣጫዎች ሰብሮ መግባት ቢችልና ከኢስላም ወደ ክህደት እንዲመለሱ ቢጠየቁ ኖሮ የተጠየቁትን ፈጥነው በፈጸሙ ነበር፡፡ (አል-ቁርአን፡14)*

ሙናፊቅ ምንም እንኳን ከሀዲ ቢሆንም ግና በፍጹም በግልጽ "እኔ ከሀዲ ነኝ" አይልም፡፡ በተቃራኒው ከፍተኛ የአላህ (ሱ.ወ) ፍራቻ ወይም ተቅዋ እንዳለው ይናገራል፡፡ በርሱ አመለካከት አማኞች በተሳሳተ መንገድ ላይ ናቸው፡፡ እርሱ ግን በትክክለኛው መንገድ ላይ ነው፡፡ ስለዚህ የርሱ ዓላማ አማኞችን ወደ እውነተኛው ጎዳና መምራት መሆኑን ይረዳል፡፡ይህ አንዱ የሙናፊቆች የብልሸት ማነሳሻ ዘዴ ነው፡፡

## ሙናፊቆች ዲን አልባ ናቸው?

የሙናፊቆች አንዱ መለያ ባህሪይ ምንም እንኳን በዲን እናምናለን ቢሉም ዲንን የሚረዱበት አስተሳሰብ ከቁርአን ጋር የሚስማማ አይደለም፡፡ የዚህ ምክንያት የቁርአንን አመክንዮ ሳይሆን የራሳቸውን ነፃ አመክንዮ መጠቀማቸው ነው፡፡ የሙናፊቆች የአመክንዮ ድር በቁርአን ተገልጿል፡፡

*አዕምሮዎቻቸው ናቸው በዚህ እብለት ያዘዟቸው? ወይስ ወሰን አላፊዎች ሕዝቦች በመሆናቸው ነው በአስተባባይነት አቋም የጸኑት? (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አጥ-ጡር፡32)*

ከላይ እንደተጠቀሰው ሙናፊቅ አላህን እንደሚፈራ ይናገራል፡፡ ሆኖም ፀባዩ አላህን ከሚፈሩት ጋር በፍጹም አይገናኝም፡፡ ዓላማው አላህን ማስደሰት አይደለም፡፡ የአላህን ቁጣ የሚያመጡበትን ሁሉንም ባህሪያት ያሳያል፡፡ ነገር ግን ይህን ሁሉ እየሠራ አላህን እንደሚፈራና ተግባሩም ከቁርአን ጋር ተስማሚ እንደሆነ አጥብቆ ይገልፃል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አብዛኛውን ሃይማኖታዊ አምልኮዎችን ለመፈጸም ሊገኝና አምልኮዎችንም ሊፈጽም ይችላል፡፡ ሆኖም ግን በአላህ (ሱ.ወ) እውነተኛ ሆኖ ያመነና ይህ ሰው ይህን የሚተገብሩበት ባህሪይና ዓላማ ይለያያል፡፡ ለምሳሌ - አንድ አማኝ የአላህን ተቀባይነት ለማግኘት ብቻ ሲል ይሰግዳል፡፡ ሆኖም ሙናፊቅ ይህን የሚያደርገው ለታይታ/ለእዩልኝ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይህን የሙናፊቆች ባህሪይ በቀጣዩ አንቀጽ ገልፆታል፡-

*መናፍቃን አላህን ሊያታልሉ ይሞክራሉ፡፡ ግና እርሱ ነው አታላያቸው፡፡ ለሶላትም የሚቆሙት እየታከታቸውና ለመታየት ሲሉ ብቻ ነው፡፡ አላህንም ጥቂትን እንጂ አያወሱም፡፡ (ሱረህ አን-ኒሳእ፡142)*

ከላይ ሲታይ ሙናፊቆችና አማኞች ተመሳሳይ አምልኮ የሚፈጽሙ ይመስላሉ፡፡ ሆኖም እውነታው ምእምናን እነዚያ ሶላታቸውን በእውነተኛ ኹሹዕ የሚሰግዱ ሲሆኑ ሙናፊቆች ደግሞ ታካቶች ናቸው፡፡

*በርግጥም አማኞች መድህን አግኝተዋል፤ እነዚያም ሶላታቸውን በፍጹም ተመስጦ የሚፈጽሙት፡፡ (አል-ቁርአን፣ሱረህ አል-ሙእሚኑን፡1-2)*

ስለዚህ እውነተኛ አማኞች አምልኮአቸውን ለአላህ (ሱ.ወ) ብለው ስለሚፈጸሙ ሽልማትን ያገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል ሙናፊቆች በክህደትና በአታላይነታቸው የአላህ (ሱ.ወ) ቁጣ ይወርድባቸዋል፡፡ እንዲሁም እነርሱ ዲን ያላቸው ሰዎች አይደሉም፡፡

ሆኖም ግን ሙናፊቅ በአላህ (ሱ.ወ) እንደሚያምንና በበርካታ ዲናዊ ሕግጋት እንደሚሠራ ይናገራል፡፡ ነገር ግን የዲን ሰው አይደለም፡፡ ታማኝነቱ ለራሱ

የእምነት ጽንሰ ሐሳብ ብቻ ነው፡፡ ይህም "የማስመሰል ወይም የሙናፊቅነት ዲን" ነው፡፡ ምንም እንኳን የሥነ-ምግባር እሴቶችን ጠንቅቆ ቢረዳም ብልሽትን ስለሚፈልግ ሁሉም ጥረቱ በቀጣዩ ዓለም ዋጋ ቢስ ይሆናል፡፡ በሌላ የቁርአን አንቀጽ አላህ (ሱ.ወ) ያንን ቀን እንዲህ ሲል ይገልፃል፡-

*እነርሱ በጌታቸው አናቅጽ የካዱና እርሱን መገናኘትን ያስተባበሉ ናቸው፡፡ ሥራዎቻቸው በርግጥም ከንቱ ሆነዋል፡፡ የትንሳኤ ቀን ቅንጣት ዋጋ አንሰጣቸውም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ከህፍ፡105)*

ይህ የንፍቅና ዲን ሰዎችን ከአላህ (ሱ.ወ) መንገድ ለማስወጣት፣ ጭንቅላታቸውን በሁሉም መንገድ ለመቆጣጠር የሚሻውና በሰዎች ላይ ድብቅ የበላይነት የመሠረተው የሰይጣን ዲን ነው፡፡ ሰይጣን መጥፎ ነገር እንዲሠሩ ያበረታታቸዋል፡፡ እንዲሁም ጥሩ እንዳይሠሩ ይከለክላቸዋል፡፡ በቀጣዩ ምዕራፍ ውስጥ ሙሉ ዝርዝሩን የምናየው፣ እንዲሁም በርሱና በሰው ልጅ ንፍቅና መካከል ያለውን ልዩነት የምንቃኘው ሰይጣን ልዩ የሆነ አመክንዮ አለው፡፡ ሙናፊቆች ይህን የሰይጣን አመክንዮ በአግባቡ ይረዱታል፡፡ ሆኖም ይህ ለነርሱ ምንም ለውጥ የለውም፡፡ ምንም እንኳን ማንኛውም ሙናፊቅ "ሰይጣንን እከተላለሁ፣ በርሱም ዲን እኖራለሁ" ባይልም በተግባር ግን ተመሳሳይ የተጣመመ አመክንዮን ያሳያል፡፡

## ሙናፊቆች የሰይጣን ጭፍሮች ናቸው

*ሰይጣን ተቆጣጥሮአቸዋል፡፡ አላህን ማስታወስንም አስረሳቿዋል፡፡ እነርሱ የሰይጣን ጭፍሮች ናቸው፡፡ አዋጅ! የሰይጣን ጭፍሮች ከሳሪዎች ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙጃደላህ፡19)*

በምድር ላይ ሁለት ህብረተሰቦች ይገኛሉ፡፡ አላህን የሚከተሉና ሰይጣንን የሚከተሉ፡፡ የሰይጣን ወታደሮች/ሠራዊቶች የፈጠራቸውን ጌታ፣ አላህን የረሱና ከእውነተኛው ጎዳና በማፈንገጥ የሰይጣንን ኮቴ የሚከተሉ ናቸው፡፡

ይህን ህብረተሰብ ለበርካታ ንዑስ ክፍሎች መከፈል እንችላለን - ጣዖት አምላኪያን፣ ከሀዲያንና ሙናፊቆች፡፡ ሆኖም ከነዚህ ቡድኖች ሁሉ ሙናፊቆች እጅግ አዋራጅ ቅጣትን እንደሚቀጡ አላህ (ሱ.ወ) ይገልፃል፡፡ ሙናፊቆች ሁሉንም የሰይጣን ባህሪያት የያዙ ህብረተሰቦች ናቸው፡፡ ይህን ከመተንተናችን በፊት ስለሰይጣን የተጣመመ አመክንዮ ወይም ሎጂክ በጥቂቱ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡

እስቲ በቅድሚያ ስለሚታወቀው የሰይጣን ዋናው ባህሪይ፣ ማለትም "ስለአስደናቂ አመጹ" እንመልከት፡፡ ይህ ባህሪው በሱረህ አል-አዕራፍ እንደሚከተለው ተነግሮናል፡፡

*መንገድ እንድስት ስላደረግከኝ ከቀናው ጎዳና መካከል እቀመጥባቸዋለሁ አለ፡፡ ከዚያም በፊት ለፊታቸውም፣ ከበስተኋላቸውም፣ ከበስተግራቸውም እመጣባችኋለሁ፡፡ አብዛኞችንም ለጸጋዎችህ ምስጋና አድራሾች ሆኖ አታገኛቸውም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አዕራፍ፡16-17)*

የሰይጣን ዋነኛ ዓላማ ሰዎች በአላህ (ሱ.ወ) እንዲክዱ ማድረግ ነው፡፡ በነዚህ አንቀጾች እንዳየነው ባለው ኃይል ሁሉ ይህን ለማሳካት ይጥራል፡፡ ሆኖም ከከፍተኛ ጥረቱ ጋር ሌላ ይህን የሚቃረን የሰይጣን አስተሳሰብ ይገኛል፡፡ የሚከተለው አንቀጽም ስለዚህ ይነግረናል፡፡

*እንደ ሰይጣን ናቸው፡፡ ሰይጣን የሰው ልጅን "በአላህ ካድ" አለው፡፡ የካደ ጊዜ "እኔ ካንተ የጠራው ነኝ፣ የዓለማት ጌታ የሆነውን አላህን እፈራለሁ" አለው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሐሽር፡16)*

ከላይ እንደምንረዳው ሰይጣን ሰዎች እንዲያምጹ ያዛቸዋል፡፡ ነገር ግን ዞር ብሎ እርሱ እንኳን አላህን እንደሚፈራ ይገልፃል፡፡ እነዚህ አባባሎች የተጣመመ አስተሳሰቡን ለሁሉም ግልጽ ያደርጋሉ፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) ላይ ማመጽና ሰዎችም እንዲያምጹ አበረታትቶ ሲያበቃ ዞር ብሎ አላህን እንደሚፈራ ይናገራል፡፡ ይህ ያለ ጥርጥር ሰይጣን ሚዛኑን ያልጠበቀ መሆኑን ነው፡፡ ሙናፊቆችንም ከሰይጣን ጋር የሚያቀራርባቸው አንዱ መለያ ባህሪይ ምስጢራዊ አመፃቸው ነው፡፡ ይኸውም ሙናፊቆች በአንድ በኩል አላህን ይጠላሉ፣ በምድር ላይ ብልሽትንም ለመፍጠር ይጥራሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን በእርሱና በቀጣዩ ዓለም እንደሚያምኑና ለርሱ ዲን፣ ለመልዕክተኞቹና ለትዕዛዛቱ ታዛዥ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡

ከዚህ በመነሳትም አላህ (ሱ.ወ) በበርካታ የቁርአን አንቀጾች ከዚህ የሙናፊቆች ሥነ-ምግባር አማኞችን አስጠንቅቋል፡፡

*"እነዚያን በአንተም ካንተ በፊትም ለነበሩ ነብያት በተወረደው መልዕክት አምነናል" የሚሉ ወገኖችን አላየህምን? የጣዖትን ዳኝነት ይሻሉ፤ በርግጥ በርሱ እንዲክዱ የታዘዙ ሆኖ እያሉ፡፡ ሰይጣንም ቅኑን መንገድ ይበልጥ ሊያሳስታቸው ይሻል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡60)*

ቁርአን ሙናፊቆችና ሰይጣን ከዚህ ከሚያጋሩት ግልጽ ባህሪይ በተጨማሪ ሌሎች በርካታ ተመሳሳይነቶችንና ግንኙነቶችን ገልጿል፡፡

## ሙናፊቆች ሰይጣንን እንደ ጓደኛ ይወስዱታል

የቁርአን ኣያው እንደሚጠቁመው፡-

*የናንተ የልብ ወዳጆችና ኢጋሮች አላህ እና መልዕክተኛው፣ እንዲሁም እነዚያ ሶላትን በትክክል የሚሰግዱ፣ ዘካንም የሚሰጡና ለአምልኮ የሚያጎነብሱት አማኞች ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ማኢዳህ፡55)*

ምእመናን አላህንና እንደነርሱ ያመኑትን ሰዎች ብቻ እንደ ወዳጅ በመያዝ የአምልኮ ተግባሮቻቸውን ይፈጽማሉ፡፡ ይህ የጥንካሬያቸው ዋነኛ ምክንያት ነው፡፡ አማኞች አላህን እንደ ወዳጅ በሚይዙበትና በእያንዳንዱ ሥራቸው ወደርሱ በሚመለሱበት አኳኋን ሙናፊቆች ደግሞ ሰይጣንን እንደ ጓደኛና ጠባቂ ይወስዱታል፡፡ ሰይጣንን እንደ ጠባቂ የሚወስዱ ሰዎች ደረጃ በነዚህ የቁርአን አንቀጾች ተገልጿል፡-

*እርሱና ሠራዊቱ እናንተ ከማታዩዋቸው ቦታ ሆነው ያዩዋቿዋል፡፡ እኛ ሰይጣናትን የነዚያ የማያምኑት ወገኖች ወዳጆች አድርገናል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አንፋል፡27)*

*ከፊሉን ወደቅኑ ጎዳና መራ፡፡ ከፊሎችም መንገድ እንዲስቱ ተወሰነባቸው፡፡ ምክንያቱም እነርሱ ከአላህ ሌላ ሰይጣናትን ወዳጆች አድርገዋል፡፡ ቅኑን ጎዳናም እንደያዙ ያስባሉ፡፡ (ሱረህ አል-አዕራፍ፡30)*

*አር-ረሕማንን ከማውሳት ራሱን ያገለለ ሰይጣንን የቅርብ ወዳጁ ይሆን ዘንድ እናዘጋጅለታለን፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አዝ-ዙኽሩፍ፡36)*

ከላይ በሱረህ አዝ-ዙኽሩፍ እንደተጠቀሰው የሙናፊቆች ዋነኛ መለያ ባህሪይ አላህን ከማስታወስ መዘንጋታቸውንና ከርሱ ጋር በመንፈስ መቆራረጣቸውን ነው፡፡ በድጋሚ የዚህ ዓይነት ባህሪይ እንዲይዙ ያደረጋቸው ሰይጣን ነው ፡፡

## ሰይጣን አላህን እንዲረሱ ያደርጋቸዋል

*ሰይጣን ተቆጣጥሯቸዋል፡፡ አላህን ማስታወስንም አስረስቷቸዋል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙጃደላህ፡19)*

አንድ ሰው ሙናፊቅ ለመሆን ከሁሉም በፊት በአማኞች ማህበረሰብ ውስጥ መኖርና በምስጢርም ሆነ በስውር ጉዳት ለማድረስ የሚጥር መሆን አለበት፡፡ ሙናፊቅ በአማኞች ቡድን ሥር የራሱን መንገድ ያበጃል፡፡ ከሁኔታው መረዳት እንደሚቻለው ለጊዜው ከነርሱ የአኗኗር ሁኔታ ጋር እራሱን ለማመሳሰል ይጥራል፡፡ ከነርሱ ጋር አላህን ያስታውሳል፣ አንቀጾቹንም ማንበብን ይማራል፡፡

ሆኖም ከእምነት ወደ ክህደት ተመልሷል፡፡ የሙናፊቆች ደረጃ በአንድ የቁርአን አንቀጽ እንዲህ ተገልጿል፡-

*ይህ እነሱ (በምላስ) ያመኑ፤ ከዚያም (በልብ) የካዱ በመሆናቸው ነው፡፡ በልቦቻቸውም ላይ ታተመባቸው፤ ስለዚህ እነሱ አያውቁም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙናፊቁን፡3)*

ሆኖም አንድ ሰው በአላህ (ሱ.ወ) መኖርና በአንድነቱ ካመነና ቁርአንን ከተከተለ እንዴት ወደ ክህደት ይመለሳል? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ እርግጥ ነው፣ ይህ ወዲያውኑ አይከሰትም፡፡ የሙናፊቆች ነብስ ከእምነት ይልቅ ወደ ክህደት ያዘነበለች ናት፡፡ የነዚህን ሰዎች ደካማ ልብ ማነሳሳት፣ ከትክክለኛው ጎዳና ማስወጣትና ወደርሱ መንገድ እንዲገቡ ለማድረግ በርካታ ወጥመዶችን የሚያዘጋጀው ሰይጣን ነው፡፡ ከነዚህ ወጥመዶች ሁሉ ታላቁ ሰዎች አላህን እንዲረሱ ማድረግ ነው፡፡ ሙናፊቁ አላህን እንዲረሳ ለማድረግ ሰይጣን በተለያዩ ስልቶች ይቀርበዋል፡፡ ሙናፊቁ የቁርአንን አንቀጾች በማንበብ እነዚህን ስልቶች በደንብ መረዳት ነበረበት፡፡ ነገር ግን እርሱ በራሱ ፈቃድ በሰይጣን ወጥመዶች ይያዛል፤ ምክንያቱም በቁርአን እንደተጠቀሰው በልቡ ውስጥ የማመጽ ሕመም አለበትና፡፡ የሙናፊቆች ስቃይ በአንድ የቁርአን አንቀጽ እንደሚከተለው ተገልጿል፡-

*በልቦቻቸው ውስጥ የንፍቅና (በሽታ) አለባቸው፤ አላህም በሽታን ጨመረባቸው፡፡ ለነርሱም ይዋሹት በነበሩት ምክንያት አሳማሚ ቅጣት አላቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡10)*

እዚህ ጋ መረሳት የሌለበት ነገር ሰይጣን ተጽዕኖ ያለው በእምነታቸው ደካማ የሆኑ ሰዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ ትክክለኛና ቅን አማኞችን በየትኛውም መልኩ ማጥመድ አይችልም፡፡ በአማኞችና በአፈንጋጮች መካከል ያለው ልዩነት በሌላ የቁርአን አንቀጽ እንደሚከተለው ተገልጿል፡-

*እነሆ ባሮቼ በነርሱ ላይ ላንተ ሥልጣን የለህም፤ ከጠማማዎቹ የተከተለ ሰው ብቻ ሲቀር፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሒጅር፡42)*

ሙናፊቆችን ሁሌም ወደ ትዕቢት፣ ለአላህ (ሱ.ወ) ያላቸው ቅንነትና ለጌታቸው ማደራቸው እንዲቀንስ የሚያበረታታቸው ሰይጣን ዓላማውን ወዲያውኑ ያሳካል፡፡ በእምነቱ ድክመት ምክንያት ለማመን በሚያዳግት ፍጥነት ከሰይጣን ጋር አብሮ የተጓዘው ሙናፊቅ አሁን የአማኝ ባህሪን ለማስመሰል የሚያደርገውን ጥረት በማቆም ሰይጣናዊ ፀባይን ማሳየት ይጀምራል፡፡ ከዚህ በፊት አማኞች ላይ በፍጹም አሳይቶ የማያውቃቸውን አሉታዊ ገጽታዎች ማሳየት ይጀምራል፡፡ ለምሳሌ - በድንገት እጅግ በጣም ይቆጣል፣ ይሸበራል፡፡ እናም አማኞችን ይጎዳል ብሎ

የሚያስበውን ፀባይ ያሳያል፡፡ የሰይጣን ተጽዕኖ በፈተና ጊዜና በተለይ እርሱ ላይ ችግር በደረሰበት ጊዜ በግልጽ ይታያል፡፡ ድንገተኛና ያልተጠበቀ ችግር የሚያጋጥመው ሙናፊቅ ይህ በአላህ (ሱ.ወ) መልካም ውሳኔ እንደተፈጸመ፣ ታጋሽ መሆን እንዳለበትና አላህ (ሱ.ወ) ዱዓውን እንደሚቀበለው አይረዳም፡፡

ሙናፊቅ በችግር ጊዜ ማንኛውም አማኝ ከሚያሳየው ፀባይ ተቃራኒውን ያሳያል፡፡ ሙናፊቁ በእምነቱ ሲፈተን በፍጹም አሳይቶ የማያውቀውን ባህሪይ ያሳያል፡፡ ይህ አላህን ረስቶ ለሰይጣን ያደረው ሙናፊቅ ትክክለኛ መገለጫ ነው፡፡

ከዚህም በመነሳት በማንኛውም መንገድ ሙናፊቆችን ከትክክለኛው ጎዳና ማራቅ ለሰይጣን ከባድ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡ በርግጥም ሰይጣን ሁሉንም ሰዎችን ወደ እርጉም መንገድ ይጠራቸዋል፡፡ ታዲያ ያንን ጥሪ ተቀብሎ ሲያበቃ በኋላ ላይ ወደ አላህ (ሱ.ወ) የማይመለሰው፣ እንዲሁም ይህን ሁሉ በራሱ በጎ ፈቃድ የሚሠራው ሙናፊቁ ራሱ ነው፡፡

*በመጨረሻይቱም ዓለም የሚያምነውን፣ ከዚያ እርሱ ከርሷ በመጠራጠር ውስጥ ከሆነው ሰው ለይተን እንድናውቅ እንጂ በነርሱ ላይ ለርሱ ምንም ሥልጣን አልነበረውም፤ ጌታህም በነገሩ ሁሉ ላይ ተጠባባቂ ነው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ሰበእ፡21)*

በቀጣዩ ዓለም ሰይጣን እርሱን የተከተሉትን ይክዳቸዋል፡፡ እናም በድጋሚ ይህን እንዲሠሩ በፍጹም እንዳላስገደዳቸውና እርሱን የተከተሉት በፍላጎታቸው መሆኑን ያውጃል፡፡

*ነገሩም በተፈጸመ ጊዜ ሰይጣን ይላቸዋል፡- አላህ እውነተኛውን ቃል ኪዳን ገባላችሁ፤ ቃል ኪዳንም ገባሁላችሁ፤ አፈረስኩባችሁም፤ ለኔም በናንተ ላይ ምንም ሥልጣን አልነበረኝም፤ ግን ጠራኋችሁ፤ ለኔም ታዘዛችሁ፤ ስለዚህ አትውቀሱኝ፤ ነፍሶቻችሁንም ውቀሱ፤ እኔ የምረዳችሁ አይደለሁም፤ እናንተም የምትረዱኝ አይደላችሁም፤ እኔ ካሁን በፊት ለአላህ ተጋሪ ባደረጋችሁት ነገር ካድኩ፤ በዳዮቹ ለነርሱ በርግጥ አሳማሚ ቅጣት አልላቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ኢብራሂም፡22)*

## ሰይጣን የጥርጣሬ ፍሬዎችን ይዘራባቸዋል

ማንኛውም በአላህ (ሱ.ወ) ትክክለኛና የተረጋገጠ ዕውቀት ያመነ እምነቱን ለቅጽበት ያህል እንኳን አይጠራጠርም፡፡ እንዲሁም ከእንደዚህ ዓይነት ውድቀት በአላህ (ሱ.ወ) ይጠበቃል፡፡ ነገር ግን ሙናፊቅ በእምነቱ ላይ ጥርጣሬ አለበት፡፡ በርግጥም እንደ ጓደኛ የወሰደው፣ መንገዱን የሚከተለው ሰይጣን ነው እነዚህን ጥርጣሬዎች ልቡ ውስጥ የሚያስነሳበት፡፡

*በርግጥ አጠማቻቸዋለሁም፤ (ከንቱን) አስመኛቸዋለሁም፤ አዛቸውምና የእንስሳትን ጆሮዎች ይተለትላሉ፤ አዛቸውምና የአላህን ፍጥረት ይለውጣሉ፤ (ያለውን ይከተላሉ)፤ ከአላህም ሌላ ሰይጣንን ረዳት አድርጎ የሚይዝ ሰው ግልጽ ከሰረትን በርግጥ ከሰረ፡፡ (ሱረህ አን-ኒሳእ፡119)*

በዚህ የቁርአን አንቀጽ እንደተገለጸው ሰይጣን በሰዎች ልብ ላይ ፍጹም ባዶና ሞኝ ጥርጣሬዎችን ማሳደር ይፈልጋል፡፡ ሆኖም እነዚያ ደካማ እምነት ያላቸው እነዚህን በልዩ ሁኔታ እንደሚያስፈልጉ በመቁጠር በቀላሉ ተግባራዊ ያደርጓቸዋል፡፡ ከቁርአን አስተምህሮት እጅግ የራቁ በመሆናቸው በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ማሳየት የሚገባቸውን ባህሪይ አያሳዩም፡፡

*ከሰይጣንም (በክፉል) ጉትጎታ ቢያገኝህ በአላህ ተጠበቅ፤ እርሱ ሰሚው ዐዋቂው ነው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አዕራፍ፡200)*

ስለዚህ አማኞች ሰይጣንን ሲያሸንፉ ሙናፊቆች ግን ያለ ጥርጥር በርሱ ይሸነፋሉ፡፡

## ሰይጣን በቃል ኪዳን ያታልላቸዋል

(1) ሰይጣን ለሰዎች ሁሉም ጊዜያዊ ከሆነው ከዚህች ዓለም ጸጋ ጋር የተያያዙ ቃል ኪዳኖችን ይገባላቸዋል፡፡

*(የማይፈጸመውን) ተስፋ ይሰጣቸዋል፤ ያስመኛቸዋልም፤ ሰይጣንም ለማታለል እንጂ አይቀጥራቸውም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡120)*

ምንም እንኳን ለአማኞች እንደ ጸጋ የሚሰጠው ጥበብ ባይኖረውም ለዓላማው ጠንክሮ የሚሠራው ሰይጣን በእያንዳንዱ ሰው ላይ ክፍተቶችን ይፈልጋል፡፡ እነዚህ ድክመቶች አንድ ሰው ከአላህ (ሱ.ወ) ተቀባይነት ይልቅ የሚመርጣቸው "ጣዖቶች" ናቸው፡፡

ጣዖት ሲባል ሃይማኖት የለሽ ሰዎች የሚያጎነብሱለትንና የሚሰግዱለትን ድንጋይ ብቻ ማሰብ የለብንም፡፡ በዚህ አባባል ጣዖት ማለት ማንኛውም ጽንሰ ሐሳብ፣ አስተሳሰብ ወይም ከሃይማኖት ይልቅ አንድ ሰው የሚመርጠው የሰው ልጅ እንኳን ሊሆን ይችላል፡፡ ደረጃ፣ ሃብት፣ ዝና ወይም ውበት፣ አልያም ሰዎች ክብርን ያሳድጋሉ ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች ወይም ማንኛውም፣ ጠፊው የዚህች ዓለም ርካሽ ቴፕ ሊሆን ይችላል፡፡ የሰይጣን ቃል ኪዳን በሌሎች ነገራት ላይም ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ከባዶ ቃል ኪዳንነት አያልፍም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም አላፊ

ናቸው፡፡ የሰው ልጅ በድጋሚ በሚቀሰቀስበት ዕለት በዚህች ምድር ላይ ክብር ያሰጠው ማንኛውም ነገርም ሆነ ሰው ከርሱ ጋር አይሆንም፡፡

የመረዳት ጥልቀት ለሚጎድላቸው ሙናፊቆች በነዚህ ባዶ ቃል ኪዳኖች ለመታለል ቀላል ናቸው፡፡ በዚህች ዓለም መስብቶች በጭፍኑ በመታለል ሙናፊቆች የሰይጣን ቃል ኪዳን እውን የሚሆን ይመስላቸዋል፡፡ እውነታው ግን የሰይጣን ቃል ኪዳኖች የታቀዱት ሰውየውን ወደ ጀሀነም ለመምራት ነው፡፡ በዚህች ዓለም ላይ ምንም ጥቅም የላቸውም፣ በተለይ በቀጣዩ ዓለም ዋጋ ቢስ ናቸው፡፡ በሱረቱል ሐሽር ተከታዩ ተነግሮናል፡-

*እንደ ሰይጣን ብጤ ለሰውየው ካድ ባለው ጊዜና በካደም ጊዜ እኔ ካንተ ንጹሕ ነኝ፣ እኔ አላህን የዓለማትን ጌታ እፈራለሁ እንዳለው ነው፡፡ መጨረሻቸውም እነርሱ በውስጡ ዘውታሪዎች ሲሆኑ በእሳት ውስጥ መሆን ነው፡፡ ይህም የበዳዮች ዋጋ ነው፡፡ (ሱረህ አል-ሐሽር፡16-17)*

በሰይጣን ቃል ኪዳን የማይታለለውና ከርሱ ጋር የማይጓዘው ብቸኛው ሕብረተሰብ የምእምናን ሕብረተሰብ ነው፡፡ ሰይጣን ያለ ማቋረጥ ለሚያንሾካሽካቸው ማታላያዎች ክፍት አይደሉም፡፡ ሁሉንም ነገሮች በምክንያታዊነትና በሕሊና ስለሚመዝኑ መሠረት የለሽ ቃል ኪዳኖች ላይ እምነት የላቸውም፡፡

## እውነተኛ ገጽታቸውን ለሰይጣን ያሳዩታል

ሙናፊቆች እራሳቸውን ከልብ ያመኑ አስመስለው ለአማኞች ለማቅረብ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የራሳቸው ጥቅም እስኪነካ ድረስ ችክ ብለው በዚህ አታላይነታቸው ይቀጥላሉ፡፡

በቀጣይ ይህን የሚያደርጉበትን ዓላማ በዝርዝር እንመለከታለን፡፡ ሙናፊቆች ከአማኞች እስኪለዩ ድረስ እራሳቸውን ይደብቃሉ፡፡ እናም በኋላ ትክክለኛ ገጽታቸውን ለሰይጣን ብቻ ይገልፃሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የሙናፊቆችን ሁኔታ በአንድ አንቀጽ እንዲህ ሲል ይገልፃቸዋል፡-

*እነዚያንም ያመኑትን በተገናኙ ጊዜ አምነናል ይላሉ፤ ወደ ሰይጣኖቻቸውም ባገለሉ ጊዜ እኛ ከናንተ ጋር ነን፤ እኛ (በነሱ) ተሳላቂዎች ብቻ ነን ይላሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡14)*

እዚህ ጋ ሰይጣን በአካል ለሙናፊቆች እንደማይገለጽላቸው ማወቁ ጠቃሚ ነው፡፡ የሰው ልጅን መልክ መያዝን አጠቃሎ ሰይጣን በርካታ ችሎታዎች አሉት፡፡ እርሱ ይህን ገጽታ ስለመያዙ ጥቂት ማብራሪያ መስጠቱ አስፈላጊ ነው፡፡ "እንደ

ሰይጣን" የሚለው ማነፃፀሪያ በዕለት ዕለት ቋንቋ "ድንበር ማለፉን" ለመግለጽ ይውላል፡፡ ታዲያ አንድ ሰው እንዴት እንደ ሰይጣን ሊሆን ይችላል? አንድ ሰው ጥቂት የሰይጣን ባህሪያትን ከተጋራ ይህን ሰው እንደ ሰይጣን ወይም ሰይጣናዊ ማለቱ ትክክለኛ ነው፡፡ በፊት እንደተጠቀሰው ሙናፊቆች የሰይጣን ባህሪይ በመሸከማቸው ሰይጣናዊ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እነሱን የመሰሉትን ለመለየት ንቃት ያለው ችሎታ አላቸው፡፡ ከነሱ በፊት ካለው ሰው ጋር አንድ የጋራ ነገር እንዳላቸው ያያሉ፡፡ ለዚያ ሰው ትክክለኛ ፊታቸውን ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ሙናፊቆች ከአማኞች በመነጠል እነሱን ከመሰሉ ሌሎች ሰዎች ጋር በሚደባለቁበት ጊዜ ነው በትክክል ከሰይጣን ጋር ፊት ለፊት የሚሄዱት፡፡ በኋላ እንደምንዳስሰው የምስጢር ስብሰባዎችን በማድረግና እርስ በርስ በምስጢር በመነጋገር በአመጽና ነብያት ላይ ጠላትነት ማወጅን የመሳሳሉ ብልጣ ብልጥ ስልቶችን ያዘጋጃሉ፡፡

## ሙናፊቆች ለምን ከአማኞች ጋር በመቆየት የአምልኮ ተግባራትን ይፈጽማሉ?

*መናፍቃን በመጡህ ጊዜ አንተ የአላህ መልዕክተኛ መሆንህን በርግጥ (ምለን) እንመሰክራለን ይላሉ፤ አላህም አንተ በርግጥ መልዕክተኛው መሆንህን ያውቃል፤ አላህም መናፍቃን (ከልብ እንመሰክራለን በማለታቸው) ውሸታሞች መሆናቸውን ይመሰክራል፡፡ (ሱረህ አል-ሙናፊቁን፡1)*

ባለፈው ምዕራፍ ሙናፊቆች ከሰይጣን ጋር የሚጋሩትን ምስጢራዊ አመጽ አይተናል፡፡ ከሃይማኖት የለሾች ጋርም በአስደናቂ ሁኔታ በማነፃፀር ሙናፊቆች ልዩ ምክንያታዊነትን እንደያዙ ተረድተናል፡፡ ምንም እንኳን ስለአላህ (ሱ.ወ) መኖር በአግባቡ ቢረዱም በርሱ ትዕዛዝ ለመኖር አይሞክሩም፡፡ ይህንንም በሚሠሩበት ጊዜ እራሳቸውን እንደ ታማኝ ግለሰብ በማስመሰል እውነተኛ ባህሪያቸውን ከአማኞች ይደብቃሉ፡፡

ለምንድን ነው በልባቸው እምነት ሳይኖራቸው የአማኞችን ባህሪይ የሚያስመስሉት? የዚህ ምክንያት የነርሱ ሁኔታ ከሌሎች ከሀዲያን የተለየ መሆኑ ነው፡፡ ሙናፊቅ በቁርአን የተጠቀሱ ነገሮችን በበቂ ሁኔታ ይረዳል፡፡ አላህን መገዛቱን በተሟላ ሁኔታ እንዲወጣ አንቀጾቹን በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ይገነዘባል፡፡ ሆኖም የሚናገረውና የሚሠራው ይለያያል፡፡ በልቡ ጥርጣሬና አመጽን ቋጥሮ በአላህ (ሱ.ወ) ስም የሚያወራው ነገር የንፍቅናው ዋነኛ ማሳያ ነው፡፡

እምነት ላለው ሰው የሙናፊቅን የልብ ጽልመት ሙሉ ለሙሉ መረዳት አዳጋች ነው፡፡ ምክንያቱም አላህን የሚፈራ ሰው ተግባሩና ንግግሩ ምንጊዜም

ተመሳሳይ ነው፡፡ ስለዚህ የሙናፊቆች ሁለት ፊት ማሳየትና ውሸት እውነተኛ አማኞችን ያስደንቃቸዋል፡፡ ነገር ግን ቁርአን የዚህ ንፍቅና አስተሳሰብ ምክንያቶችን ለአማኞች ገልጽዋል፡፡

## (1) ቁሳዊ ጥቅምን ማግኘት ይፈልጋሉ

ሙናፊቅ አማኞችን እንደ ጓደኛ የሚቀርብበት ዋነኛ ምክንያት ቁሳዊ ጥቅምን ለማግኘት ካለው ፍላጎት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ለሰጣቸው ጸጋዎች ምስጋና ይግባቸው አማኞች የመንፈስ ጥንካሬና የቁስ የበላይነት አላቸው፡፡ ታሪክ በእንደዚህ ዓይነት ምሳሌዎች የተሞላ ነው፡፡ ለምሳሌ – ነብዩሏህ ሱለይማን (ዐ.ሰ)፣ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ)፣ ነብዩ ዳውድ (ዐ.ሰ)፣ ዙል ቀርነይን፣ እንዲሁም ሌሎች በቁርአን የተጠቀሱ በርካታ ነብያት (ዐ.ሰ)፡፡ ለምሳሌ – ቀጣዩ የቁርአን አንቀጽ ስለነብዩ ሱላይማን (ዐ.ሰ) ይነግረናል፡–

*ከምኩራቦች፣ ከምስሎችም፣ እንደ ገንዳ ከሆኑ ገበታዎችም፣ ከተደላደሉ ታላላቅ ድስቶችም፣ የሚሻውን ሁሉ ይሠሩለታል፤ (አልናቸውም) የዳውድ ቤተሰቦች ሆይ! አመስጋኞች ሆናችሁ (ለጌታችሁ) ሥሩ፤ (አል–ቁርአን፣ ሱረቱ ሰበእ፡13)*

ነብዩ ሱለይማን (ዐ.ሰ) የነበራቸው ግንቦች፣ ሃውልቶች፣ ትላልቅ ድስቶችና ገንዳዎች የጊዜው የውበትና የሃብት መለኪያ ናቸው፡፡ ሌላ የቁርአን አንቀጽ ነብዩ ሱለይማን (ዐ.ሰ) ጊቢው በመስታወት የተነጠፈ ትልቅ ቤት እንደነበራቸው ይገልፃል፡፡ ጥቅም ላይ ለዋለው የረቀቀ ቴክኖሎጂ ምስጋና ይገባው፡፡ ንግስተ ሳባና ቢልቂስ እጅግ ተደንቀው ነበር፡፡

*ሕንፃውን ግቢ ተባለች፤ ባየቺውም ጊዜ ባሕር ነው ብላ ጠረጠረች፤ ከባቶቿዋም ገለጠች፤ እርሱ ከመስታወት የለሰለሰ ሕንፃ ነው አላት፤ ጌታዬ ሆይ! እኔ ነፍሴን በደልኩ፤ ከሱለይማንም ጋር ሆኜ ለዓለማት ጌታ ለአላህ ታዘዝኩ አለች፡፡ (አል–ቁርአን፣ ሱረህ አን–ነምል፡44)*

ሱረቱል ከፍህ ዕውቀትና የበላይነት የነበረውን ዙል ቀርነይንን እንደሚከተለው ይገልፃቸዋል፡–

*እኛ ለርሱ በምድር አስመቸነው፤ ከነገሩም ሁሉ (መዳረሻ) መንገድን ሰጠነው፡፡ (አል–ቁርአን፣ ሱረህ አል–ከህፍ፡84)*

ሌላ የሱረቱል ኒሳእ የቁርአን አንቀጽ በቁርአን በሥነ–ምግባራቸው የተመሰገኑት ነብዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ) ከቤተሰባቸው ጋር በርካታ ሃብት እንደነበራቸው ይገልፃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አላህ (ሱ.ወ) ምእመናን ከዚህ

በፊት ረግጠውት የማያውቁትን ሥፍራ ወራሽ እንደሚያደርጋቸው ቃል ገብቷል፡፡ ይህ ሁኔታ በቁርአን ውስጥ እንደሚከተለው ተገልጿል፡-

*ይልቁንም ሰዎችን አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ነገር ይመቀኛሉን; ለኢብራሂምም ቤተሰቦች መጽሐፍንና ጥበብን በርግጥ ሰጠን፤ ታላቅንም ንግስና ሰጠናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኑር፡55)*

የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ኪዳኖች ሁሌም እውን ይሆናሉ፡፡ ቁርአን እንዲህ ይገልፃል፡-

*ከነሱም በኋላ ምድሪቱን በርግጥ እናስቀምጣችኋለን፤ ይህ በፊቴ መቆሙን ለሚፈራ፣ ዛቻዬንም ለሚፈራ ሰው ነው፡፡ እርዳታንም (ከአላህ) ፈለጉ፤ (ተረዱም) ጨካኝ ምገደኛ የሆነም ሁሉ አፈረ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ኢብራሂም፡14-15)*

አላህ (ሱ.ወ) ያለማቋረጥ አማኞችን መደገፉ ሙናፊቆች ከአማኞች ጋር መሆን ጠቃሚ ነው ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል፡፡ ምንም እንኳን ከሃይማኖታዊ እሴቶች ሙሉ ለሙሉ የራቁ ቢሆኑም ከአማኞች ጋር ይኖራሉ፡፡

ነገር ግን ሙናፊቆች እንዳሰቡት አማኞች ሃብታቸውንና ንብረታቸውን ለራሳቸው የግል ጥቅም አያውሉትም፡፡ ምክንያቱም ሃብታቸውና ንብረታቸው የአላህ (ሱ.ወ) እንደሆኑና በአላህ (ሱ.ወ) መንገድ ብቻ ማውጣት እንዳለባቸው ያምናሉ፡፡ ወዲያውኑም ሆኖ ቆይቶ ሙናፊቁ ምንም ዓይነት የአማኞች ገንዘብ ወደርሱ እንደማይመጣ ሲረዳ እነሱን ሙሉ ለሙሉ ለመተው ቃል ይገባል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የባለ ጸጋ አማኞች መነገጃ መንገዶች ሰፊ ናቸው፡፡ ይህ በሙስሊሞች ዘንድ ታማኝ እንዲባሉና የንግድ ዕድላቸውን ለማስፋት የተወሰኑ ሃይማኖታዊ ተግባራትን በሚፈጽሙ ሙናፊቆች ላይ ከፍተኛ መደነቅን ይፈጥራል፡፡ በቁርአን ላይ አላህ (ሱ.ወ) ሙናፊቆች እንደወሳኝ ነገር የሚቆጥሩት ገንዘብ ላይ ያላቸውን መጓጓት ይገልፃል፡፡

*ንግድን ወይም ዛዛታን ባዩ ጊዜም ቆመህ የተውህ ሲሆኑ ወደርሷ ይበተናሉ፤ አላህ ዘንድ ያለው ዋጋ ከዛዛታም ከንግድም በላጭ ነው፤ አላህም ከሰጪዎች ሁሉ ይበልጥ ሲሳይን ሰጭ ነው በላቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ጁሙዐህ፡11)*

እንዴታ! ሁለት ፊት የሚያሳዩት ሙናፊቆች ተስፈ የሚያደርጉለትን አያገኙም፡፡ እዚህች ዓለም ላይ ከሚደርስባቸው ጉዳት በተጨማሪ በቀጣዩ ዓለምም ይከፋሉ፡፡

## (2) ጓደኛና ክብራቸውን ለማስፋት ተስፋ ያደርጋሉ

አማኞች በሥነ-ምግባራቸው፣ በአኗኗር ዘይቤአቸውና ለሰው በሚሰጡት ክብር ምክንያት በርካታ ጓደኞች አሏቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሃይማኖታዊ የሥነ-ምግባር እሴቶችን ለዝነኛ የማሕበረሱ አባላት ስለሚነግሩ ከነርሱም ጋር ጠንካራ ግንኙት አላቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እነርሱን ከሚቃወመው አንድ ቡድን ውጪ የአማኞች ጥንካሬና ተጽዕኖ ሲጨምር ድጋፉ ከሚጨምረው ተራው ሕዝብ በርካታ ደጋፊዎች አሏቸው፡፡

ድጋፋቸው ሲጨምር በሕብረተሰቡ ዘንድ ያላቸው ክብር፣ ከተራው ሕዝብ የተለየ ገጽታ መያዛቸውና የላቀ ሥነ-ምግባራቸው የበለጠ ይታወቃል፡፡ ለአስደሳቹ ሥነ-ምግባራቸውና አቻ ለሌለው ጀግንነታቸው ምስጋና ይገባው፣ አማኞች ተገቢ ዝነኝነትን ያገኛሉ፡፡ ለምሳሌ - የነብዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ) ሕዝባዊ ታቃዊነትና ዝነኝነት በልጅነታቸው ካሳዩት ጀግንነታቸው ጋር በቁርአን ውስጥ ተገልጿል፡-

*ኢብራሂም የሚባል ጎበዝ (በመጥፎ) ሲያነሳቸው ሰምተናል ተባባሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አንቢያእ፡60)*

በሌላ የቁርአን አንቀጽ አላህ (ሱ.ወ) ስለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ይላል፡ -

*መወሳትህንም ላንተ ከፍ አድርገንልሃል፡፡ (ሱረህ አል-ኢንሺራህ፡4)*

ደካማ ፀባይ ያላቸው ሙናፊቆች በዚህ ዝነኝነት ስምና ተቀባይነት ተጽዕኖ ሥር ወቅደው ከአማኞች ጋር በመሆን የራሳቸውን ማንነት ማግኘት ይፈልጋሉ፡፡ ይህንም በመሥራት ከእነሱ ጋር እንዳሉት ተደናቂና ተጽዕኖ ፈጣሪ የሚሆኑ ይመስላቸዋል፡፡ ሆኖም ከአማኞች ጋር በሚሆኑበት ጊዜ በሚፈጥሩት ሁከትና ብልሽት ምክንያት አላህ (ሱ.ወ) የሚጠብቁትን ክብር ሳይሆን የሚገባቸውን ውርደት እንዲያዩ ያደርጋቸዋል፡፡

# የሙናፊቆች ባህሪያት

*እነዚያ የአላህን ቃል ኪዳን ከአጠበቀባቸው በኋላ የሚያፈርሱ፣ እንዲቀጠልም በርሱ ያዘዘውን ነገር የሚቆርጡ፣ በምድርም ላይ የሚያበላሹ እነዚያ እነርሱ ከሳሪዎቹ ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡27)*

"ሙናፊቅ" የሚለው የዐረብኛ ቃል ትርጉም ማንኛውም "ብዥታና ብልሽትን የሚፈጥር" ማለት ነው፡፡ በአማኝ ሕብረተሰብ ውስጥ እንዲገቡ የሚያደርጋቸው ዋነኛ ምክንያት ይህ ነው፡፡ በአማኞች የተመሠረተውን ሥርዓት ለማበላሸት የተገኘውን አጋጣሚ በመጠቀም ለሚሠሩት ሥራ ቆራጥ ናቸው፡፡ ምንም

እንኳን ሙናፊቆች አማኝ ባይሆኑም አማኝ እንደሆኑ በማስመሰል አማኞች የሚሰጧቸውን ዕድሎች መጠቀም ይሻሉ። ነገር ግን ምንጊዜም ችግር ወይም መከራ ሲደርስ በአንዴ በመለየት ወደሌላ ቡድን ይሻገራሉ። ትክክለኛ ባህሪያቸው የሚጋለጠው በመከራ ጊዜ ነው። ይህ በግልጽ የሚያሳየው ከሙእሚኖች ጋር የሚሆኑት ለግል ጥቅማቸው መሆኑን ነው። በቁርአን የተገለጸው ባህሪያቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ገጽታዎች አሉት። ረሱል (ሶ.ዐ.ወ) የሙናፊቆችን ባህሪይ በሚከተሉት ቃላት ገልጸውታል፡-

*የሙናፊቅ ምልክት ሦስት ናቸው። ሲናገር ይዋሻል፣ ቃል ሲገባ የገባውን ያፈርሳል፣ ሲታመን ይከዳል። (ሰሒሑል ቡኻሪ)*

የሙናፊቆችን ባህሪይ ለመረዳት በቅድሚያ በአላህ (ሱ.ወ) ላይ ስላላቸው እምነት ማወቅ አለብን።

## (1) በአላህ (ሱ.ወ) እና በቀጣዩ ዓለም ያላቸው እምነት ጥልቀት የለውም

የትም ቢኖር እያንዳንዱ ሰው በአላህ (ሱ.ወ) የማመንና እንደ ብቸኛ ፈጣሪ የማምለክ ግዴታ አለበት። ስለዚህ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል የሆነው ቁርአን ያስፈልገዋል። ነገር ግን ምንም ዕውቀት የሌለው በሌላ አነጋገር ወደ ቁርአን ጥሪ ያልተደረገለት ሰው በቁርአን መሠረት እንዲኖር ጥሪ ከተደረገለትና የቁርአንን ጥልቅ ሁኔታዎች ከተገነዘበው ጋር እኩል አይደለም። ሙናፊቅ በአላህ (ሱ.ወ) እንዳመነና ቁርአንን እንደሚቀበል በማስመሰል ይህን ኃላፊነት የተሸከመ ያስመስላል። ከምንም በላይ ለአላህ (ሱ.ወ) ትዕዛዝ መኖር/ማደር እንዳለበት አውቋል። ከአማኞች ጋር በመኖሩ ምክንያት አማኞች በረሱል (ሶ.ዐ.ወ) ማመናቸውን፣ አላህን ሲገዙና በቁርአን መሠረት ሲኖሩ ይመለከታል። ሆኖም ለዚህ ሁሉ ጀርባውን ይሰጣል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ዓይነት ባህሪይ ያለባቸውን ተከታዩን ይላቸዋል፡-

*የአላህም አንቀጾች በናንተ ላይ የሚነበቡ ሲሆኑ፣ መልዕክተኛውም በውስጣሁ ያለ ሲሆን እናንተ እንዴት ትክዳላችሁ! በአላህም የሚጠበቅ ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ በርግጥ ተመራ። (ሱረህ ኣል ዒምራን፡101)*

ይህ አንቀጽ ሙናፊቆች በአላህ (ሱ.ወ) አንቀጽ ላይ ያላቸውን እምነት ለማጋለጥ እጅግ ወሳኝ ነው። ቁርአንን ማንበብና ማዳመጥ የአማኙን እምነት ይጨምራል። ከመልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ጋር ተመሳሳይ አካባቢ የሚኖረው፣ አምንባቸዋለሁ የሚላቸውን አንቀጾች የሚሰማው ሙናፊቅ እምነቱ ይጨምራል፣ ቀልቡም ይለሰልሳል ተብሎ ሊገመት ይችላል። ነገር ግን ትክክለኛ ዓላማው

እምነቱን መጨመር ሳይሆን የግል ጥቅም ለማግኘትና ዓለማዊ ጥቅማ ጥቅሞችን ማግኘት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ይህ ተዓምር ይከሰታል፡፡ ምንም እንኳን የቁርአን አንቀጾችን ቢያዳምጥም፣ እንዲሁም እንዴት እንደሚሠራባቸው ቢረዳም ልቡ ውስጥ ያለው በሽታ ሳይታከም ይቆያል፡፡

ማንኛውም የአላህን ተቀባይነት ለማግኘት የሚሠራው ሥራ ጀነትን የማግኛ ቅድመ መስፈርትና መሣሪያ መሆኑ መረሳት የለበትም፡፡ የሙናፊቅ ዋነኛ መለያ ባህሪይ የአላህን ተቀባይነት ለማግኘት የሚደረድረው ምክንያት ነው፡፡ ምንም እንኳን እምነት ያለው ቢመስልም አደጋ ሲከሰት ደካማነቱና ወላዋይነቱ በፍጥነት ይጋለጣሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ሲል ባህሪያቸውን ይነግረናል፡-

*ታዛዥነትና መልካም ንግግር (ይሻላቸዋል)፣ ትዕዛዙም ቁርጥ በሆነ ጊዜ ለአላህ (ትዕዛዝ) እውነተኞች በሆኑ ኖሮ ለነሱ የተሻለ በሆነ ነበር፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ሙሐመድ፡21)*

በችግር ጊዜ ሙናፊቅ የገባውን ቃል ኪዳን ሲያፈርስና የክህደት ባህሪን ሲያሳይ ይታያል፡፡ በማንኛውም ሁኔታ አቅጣጫውን በመቀየርና ጥልቀት የሌለው እምነቱን ለመተው ዝግጁ ነው፡፡ አምናለሁ ቢልም እንኳን በአላህ (ሱ.ወ) አለማመኑ የመነጨው በማያጠራጥር ሁኔታ በቀጣዩ ዓለም እምነት ስለሌለው ነው፡፡

በረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ትዕዛዝ አማኞች ከሀዲያንን ሲዋጉ እምነቱ ደካማ የሆነ አንድ ቡድን ስለአላህ (ሱ.ወ) እና ስለረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ነገሮችን ማሰብ ጀመረ፡፡፡ እናም በዚህ ሁኔታ እውነተኛ ገጽታውን ገለጸ፡፡

*እዚያ ዘንድ ምእምናን ተሞከሩ፤ ብርቱን መንቀጥቀጥንም ተንቀጠቀጡ፡፡ መናፍቆችና እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ያለባቸውም አላህና መልዕክተኛው ማታለልን እንጂ ሌላን አልቀጠሩንም በሚሉ ጊዜ (ያደረገላችሁን አስታውሱ)፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አሕዛብ፡11-12)*

በሙናፊቆች ላይ ከታየው ድክመት በተቃራኒው የአማኞች ጥንካሬ ጨመረ፡፡

*አማኞቹም አሕዛብን ባዩ ጊዜ ይህ አላህና መልዕክተኛው የቀጠሩን ነው፤ አላህና መልዕክተኛውም እውነትን ተናገሩ (የተናገሩት እውነት መሆኑ ተረጋገጠ) አሉ፡፡ (ይህ) እምነትንና መታዘዝንም እንጂ ሌላን አልጨመረላቸውም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አሕዛብ፡22)*

## (2) ከእምነት ወደ ክህደት ተመልሰዋል

*ምንም ያላሉ ለመሆናቸው በአላህ ይምላሉ፤ የክህደትንም ቃል በርግጥ አሉ፤ ከእስልምናቸውም በኋላ ካዱ፤ ያላገኙትንም ነገር (ነብዩን መግደልን) አሰቡ፤ አላህም ከችሮታው መልዕክተኛውም (እንደዚሁ) ያከበራቸው መሆኑን እንጂ ሌላን አልጠሉም፤ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡74)*

በሙናፊቆች ደረጃ የተለያዩ ዓይነት ሙናፊቆች ይገኛሉ፡፡ ጥቅቶች ወደ ምእመናን ማህበረሰብ የሚገቡት ቁሳዊ ጥቅምን ብቻ ለማግኘት ነው፡፡ ሌሎች በጥላቻና በምስጢር በእነሱ ላይ ሴራ ለመሸረብ ከአማኞች ጋር ይቀላቀላሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከአማኞች ጋር ሲኖሩ እምነት የነበራቸው ሆኖም ልባቸው እየደረቀ ሲሄድ ይህንን እምነት ትተው ሙናፊቆች ሆነው ሊገኙ ይችላሉ፡፡ እነዚህ መጀመሪያ የአማኝ የነበሩ ሰዎች ቅን አመለካከታቸውን አጥተው ወደ ከሀዲነት ተቀየሩ፡፡ ነገር ግን ለአላህ (ሱ.ወ) ታማኝ ለመሆንና በእምነታቸው ቆራጥ ለመሆን ምለው ነበር፡፡ ይህ ሁለት ፊት ፀባይ በቁርአን ተገልጿል፡፡

*እነዚያ የአላህን ቃል ኪዳን ከአጠበቀባቸው በኋላ የሚያፈርሱ፣ እንዲቀጠልም በርሱ ያዘዘውን ነገር የሚቆርጡ፣ በምድርም ላይ የሚያበላሹ እነዚያ እነርሱ ከሳሪዎቹ ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡27)*

# (3) የሚመነጬት ከአማኞች ሕብረተሰብ ነው

*እነዚያ (ዓኢሻን በመስደብ) መጥፎን ውሸት ያመጡ ከናንተው የሆኑ ጭፍሮች ናቸው፤ ለናንተ ክፉ ነገር ነው ብላችሁ አታስቡት፤ በእውነቱ እርሱ ለናንተ መልካም ነገር ነው፤ ከነርሱ (ከጭፍሮቹ) ለያንዳንዱ ሰው ከኃጢአት የሠራው ሥራ ዋጋ አለው፤ ያም ከነሱ ትልቁን ኃጢአት የተሸከመው (ነገሩን ያጋነነው) ለርሱ ከባድ ቅጣት አለው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኑር፡11)*

ሙናፊቆች እንዴት ነው ወደ አማኝ ሕብረተሰብ የሚገቡት? መልሱ በቁርአን ተሰጥቷል፡፡ ሙናፊቅ እራሱን አማኝ የማስመሰል ከፍተኛ ብቃት አለው፡፡ ለጥቂት ጊዜ ቢሆንም እንደ አማኞች አላህን በመጥራትና በመገዛት እውነተኛ ፀባዩን መደበቅ ይችላል፡፡ ሌላኛው እራሱን መደበቅ የቻለበት ምክንያት አማኞች የሚመኘውን ጥቅም በቀላሉ ስለሚሰጡት ነው፡፡ አንድ ሰው ወደ እነርሱ መጥቶ አማኝ ነኝ ካለ አማኝ መሆኑን ይቀበሉታል፡፡ ይህ የተቀባይነት ባህሪይ በዋናነት የመነጨው በእጹብ ሥነ-ምግባርና የአላህን ተቀባይነት ለማግኘት ካላቸው ጥረት ነው፡፡ ምንም እንኳን አማኞች የዚህ ግለሰብ ዓላማ ጥመታዊ መሆኑን በቶሎ ቢገነዘቡም በጊዜ ሂደት ራሱን በማስተካከል ወደ እምነት ይመጣል ከሚል ግምት ከእነሱ ጋር እንዲቆይ ይፈቅዱለታል፡፡

የሙናፊቆችን አጠቃላይ ባህሪይ በነዚህ ዐ. ነገሮች ነፀብራቅ መመልከቱ ጠቃሚ ነው።

## (4) ፀባያቸውና አስተሳሰባቸው

### ተፈጥሮአቸው ለሁከት የቀረበ ነው

*ለነርሱም በምድር ላይ አታበላሹ በተባሉ ጊዜ እኛ አሳማሪዎች ብቻ ነን ይላሉ። ንቁ! እነሱ አጥፊዎቹ እነሱው ናቸው፤ ግን አያውቁም። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡11-12)*

አንድ አማኝ አላህን ስለሚፈራ ቀኑ ሲደርስ ስለአሰበውና ስለሠራው እንደሚጠየቅ ይገነዘባል። ሁሌም ወደ መልካም ሥራ ፊቱን በማዞር ጊዜውን በሙሉ ጥሩና ሞራላዊ ባህሪያትን በማሰብ ያሳልፋል። በሌላ በኩል ሙናፊቆች ሁሌም በቂያማ ቀን ላይ ጥርጣሬ አለባቸው። ስለዚህ ጭንቅላታቸውን ለጥሩ አስተሳሰብ አያውሉትም። ሁሌም ብልሽትን በመፍጠር ምእመናንን ለማበሳጨት ስለሚፈልጉ ጥረታቸው ሁሉ ተንኮል አዘል ነው።

ለሁከት የቀረበው ባህሪያቸው ሲገለጽ ይህንን ለመከዳትና የአላህን መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) በሐሰት ቃላት ለማታለል ይሞክራሉ። ሆኖም ይህ አይሳካላቸውም፤ ምክንያቱም አላህ (ሱ.ወ) ቀድሞውኑ ለአማኞች ምን እንደሚሉ ነግሯቸዋል።

*ከነርሱም ውስጥ "ለኔ ፍቀድልኝ፣ አትሞክረኝም" የሚል ሰው አለ፤ ንቁ! በመከራ ውስጥ ወደቁ፤ ገሀነምም ከሀዲዎችን በርግጥ ከባቢ ናት። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡49)*

ሙናፊቆች ሙሉ ለሙሉ ለሁከት የተጋለጡ ናቸው። በምስጢር ወይም በብልጠት ወይም በግልጽ ጥልን ማስፋፋት ይፈልጋሉ። "ፊትናህ" የሚለው የዐረብኛ ቃል ትርጉም በአማኝ ሕብረተሰብ ውስጥ ብልሽትን መፍጠር ማለት ነው።

ሙናፊቆች በውስጣዊም ሆነ በውጫዊ ገጽታቸው የቃሉን ትርጉም ያሟላሉ። ከሰላምና ከውበት ይልቅ ነብስያቸው ለጥልና ለብጥብጥ የተጋለጠች ነች።

ቁርአንን ስናጤን በታሪክ ውስጥ ሙናፊቆች ሁከትን እንዳስፋፉ እንመለከታለን፡፡ ቁርአን ባህሪያቸውን በበርካታ ምሳሌዎች ያቀርበዋል፡፡ ለምሳሌ – ለሁከት የቀረቡ ሰዎች የተለያየ ባህሪይ አልነበራቸውም፣ የተጠቀሙት ዘዴም ሁልጊዜ ተመሳሳይ ነበር፡፡

ሌላኛው ለሁከት የቀረበ ባህሪይ ምሳሌ የነበረው በነብዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) ጊዜ የሙናፊቆች መሪ የነበረው ሳማሪታን ነው፡፡ በነብዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) የተፈጠረውን አጋጣሚ በመጠቀም ሳማሪታን ሁከትን በማስፋፋት አብዛኞቹን ከትክክለኛ ጎዳና እንዲያፈነግጡ አደረገ፡፡

## ከከሀዲያን ክብርንና ኃይልን ይፈልጋሉ

*እነዚያ ከምእመናን ሌላ ከሀዲዎችን ወዳጆች አድርገው የሚይዙ፣ እነሱ ዘንድ ልቅናን ይፈልጋሉን; ልቅናም ሁሉ ለአላህ ብቻ ነው፡፡ (አል–ቁርአን፣ ሱረህ አን–ኒሳእ፡139)*

የሙናፊቆች ውሳኔ በሙሉ የተጣመመ ስለሆነ ለከሀዲያን ያላቸው አመለካከትም ሙሉ ለሙሉ አቅጣጫውን የሳተ ነው፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) የማያምኑ፣ በሃይማኖት የሥነ–ምግባር እሴቶች የማይኖሩ፣ እንዲሁም ሌሎች በሃይማኖት እንዳይኖሩ ለማድረግ የሚጥሩ ሰዎችን ያፈቅራሉ፡፡ የዚህ ምክንያት ከከሀዲያን የተወሰኑ ጥቅሞችን ማግኘት መቻላቸው ነው፡፡ ስለዚህ የከሀዲያንን መስፈርት እንደ ጠቃሚ ነገር ይቆጥሩታል፡፡ በከሀዲያን መመስገንና በነርሱ ዳኝነት የበላይ መደረግ ለሙናፊቆች ከፍተኛ ክብር ነው፡፡ ክብርና ኃይል የአላህ (ሱ.ወ) መሆኑን አይረዱም፡፡ የከሀዲያን ቁጥር ከአማኞች ልቆ መገኘቱ ከከሀዲያን ጠንካራና የበላይ ናቸው ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል፡፡

ነገር ግን ሙናፊቆች ሌላ እውነታን አያውቁም ወይም መረዳት አልቻሉም፡፡ ይህም አላህ (ሱ.ወ) ሁሌም አማኞችን እንደሚደግፍና እንደሚጠብቅ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ሁሌም አማኞችን በከሀዲያን ላይ በሚያደርጉት ትግል ረድቷቸዋል፡፡ እንዲሁም ሁልጊዜ አሸናፊ አድርጓቸዋል፡፡ ይህ በሱረቱ ኒሳእ በቀጣዮቹ ቃላት ተገልጿል፡–

*እነዚያ በናንተ (የጊዜን መዘዋወር) የሚጠባበቁ ናቸው፤ ለናንተም ከአላህ የሆነ አሸናፊነት ቢኖራችሁም ከናንተ ጋር አልነበርንም; ይላሉ፤ ለከሀዲዎችም ዕድል ቢኖር (ካሁን በፊት) በናንተ ላይ አልተሾምንምን; (እና አልተውናችሁምን;) ከምእመናንም (አደጋ) አልከለከልናችሁምን; ይላሉ፡፡ አላህም በትንሳኤ ቀን በመካከላችሁ ይፈርዳል፤*

*አላህም ለከሀዲዎች በምእመናን ላይ መንገድን በፍጹም አያደርግም፡፡ (ሱረህ አን-ኒሳእ፡141)*

## ከከሀዲያን ጋር ይወዳጃሉ

*ከነሱ ብዙዎቹን እነዚያን የካዱትን ሲወዳጁ ታያለህ፤ በነሱ ላይ አላህ የተቆጣባቸው በመሆኑ ለነርሱ ነፍሶቻቸው ያስቀደሙት ሥራ በጣም ከፋ፤ እነሱም በቅጣት ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው፡፡ (ሱረህ አል-ማኢዳህ፡80)*

አላህ (ሱ.ወ) አማኞች ከከሀዲያን ጋር እንዳይወዳጁ አዟል፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) ባለማመናቸው፣ ወደርሱ ባለመመለሳቸውና ጀርባቸውን ለርሱ አንቀጾች በመስጠታቸው ከሀዲያን ለጓደኝነት የሚሆን ባህሪይ እንደሌላቸው አረጋግጠዋል፡፡ ቀጣዩን ዓለም ሙሉ ለሙሉ ዘንግተዋል፡፡ በሰይጣናዊ ጥረት ሌሎች ሰዎች ይህችንም ምድር እንዲወዱ ለማድረግ ይሞክራሉ፡፡ ይህንን ባህሪያቸውን የሚረዱት አማኞች ከከሀዲያን ይርቃሉ፡፡ እናም በፍጹም እንደ ጓደኛ ወይም እንደ ምስጢር ያዥ አይዟቸውም፡፡

በሌላ በኩል ሙናፊቆች ከከሀዲያን ጋር ይወዳጃሉ፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) ባመኑት፣ ሕይወታቸውን የርሱን ተቀባይነት ለማግኘት በሚለፉትና እጅግ ንጹሕና ታማኝ በሆኑት ላይ ጥላቻ አላቸው፡፡

*እነዚያ ከምእመናን ሌላ ከሀዲዎችን ወዳጆች አድርገው የሚይዙ፣ እነሱ ዘንድ ልቅናን ይፈልጋሉን; ልቅናም ሁሉ ለአላህ ብቻ ነው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡139)*

የዚህ ምክንያቱ ሙናፊቆችና ከሀዲያን ተመሳሳይ ባህሪይ መያዛቸው ነው፡፡ ከሁለቱ አንዱ ቡድን አላህን በመካድ ቀጣዩ ዓለምን ሊረሳ ይችላል፡፡ እናም ተመሳሳይ አቅጣጫ የሚሄዱ ሌሎችን ሊፈልግ ይችላል፡፡ ከዚህ በፊት እንዳስቀመጥነው ሁለቱም ቡድኖች የሰይጣን ጭፍሮች ሲሆኑ ለሰይጣን አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡

## ታማኞች አይደሉም

እስካሁን ከተጠቀሰው ባህሪይ እንደምንረዳው ሙናፊቆች መታመን አይችሉም፡፡ ከአማኞች ጋር ይኖራሉ፡፡ ሆኖም የእነሱ ጠላቶች ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይህን ጥላቻ በውስጣቸው ይደብቁታል፡፡ ይህ በውስጣቸው የደበቁት ጠላትነትና የውሸት ፀባይ የብልጠታቸውና የኢ-ታማኝነታቸው ግልጽ ማሳያ ነው፡፡ ስለዚህ ጥቂት እንኳን ታማኝነትን አያሳዩም፡፡ የሚገቡትንም ቃል ለራሳቸው ጥቅም

ካልሆነ በስተቀር በፍጹም አይጠብቁም፡፡ ይህ በአንድ የቁርአን አንቀጽ እንደሚከተለው ተጠቅሷል፡-

*እነዚያ ከነሱ ቃል ኪዳን የያዝከባቸው፣ ከዚያም በየጊዜው ቃል ኪዳናቸውን የሚያፈርሱ ናቸው፤ እነርሱም አይጠነቀቁም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አንፋል፡56)*

ከዚህ በፊት እንደጠቀስነው ሁከትና ብልሽት ለመፍጠር ያላቸው ጉጉት ኢ-ታማኝነታቸውን ያረጋግጣል፡፡ ለአንድ አማኝ እነዚህ ግለሰቦች በችግርና በመከራ ጊዜ ቃላቸውን ይጠብቃሉ ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ በተቃራኒው በእንደዚህ ዓይነት ጊዜ አማኞች ማድረግ ያለባቸው ጠቃሚ ነገር በእንደዚህ ዓይነት የብልጠት እንቅስቃሴዎች ከሚሳተፍ ሰው ሙስሊሞችን መጠበቅ ነው፡፡

ቁርአን በችግር ጊዜ ኢ-ታማኝነታቸው የሚጨምረው ሙናፊቆችን እውነተኛ ባህሪይ ለአማኞች በመንገር እንዲጠነቀቋቸው ይጋብዛቸዋል፡፡

*በምእምን ነገር ዝምድናንም ኪዳንንም አይጠብቁም፤ እነዚያም እነርሱ ወሰን አላፊዎች ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡10)*

## ውሸት ይናገራሉ

ሙናፊቆች የውሸት ባህሪይ አለባቸው፡፡ ውሸትን ያለ ኃላፊነትና ምንም ሳያስቡበት ይናገራሉ፡፡ ሆኖም አላህ (ሱ.ወ) ሰዎችን ከውሸት በመከልከል ከእሱም እንዲጠነቀቁ አዟል፡፡

*(ነገሩ) ይህ ነው፤ የአላህንም ሕግጋት የሚያከብር ሰው፣ እርሱ ከጌታው ዘንድ ለርሱ በጣም የተሻለ ነው፤ የቤት እንስሳትም (ግመል፣ ከብት፣ በግ፣ ፍየል) በናንተ ላይ (እርም መሆኑ) ከሚነበብላችሁ በስተቀር ለናንተ ተፈቅዶላችኋል፤ ከጣዖታትም ርክሰት ተጠንቀቁ፤ ሐሰትንም ቃል ራቁ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሐጅ፡30)*

በቁርአን እንደተገለጸው፡-

*እነዚያም (ምእምናንን) ለመጉዳት፣ ክህደትንም ለማበረታታት፣ በምእምናንም መካከል ለመለያየት ካሁን በፊት አላህንና መልዕክተኛውን የተዋጋውንም ሰው ለመጠባበቅ መስጊድንም የሠሩት (ከነሱ ናቸው)፤ መልካምን ሥራ እንጂ ሌላ አንሻም ሲሉም በርግጥ ይምላሉ፤ አላህም እነሱ በርግጥ ውሸታሞች መሆናቸውን ይመሰክራል፡፡ (ሱረህ አት-ተውባህ፡107)*

ሁሌም ውሸታቸው የኢ-ታማኝነታቸው ግልጽ ማሳያ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ከነርሱ የመንፈሳዊ አተያይ አንፃር ሁሌም ውሸታቸው ተፈጥሮአዊ ነው።ምክንያቱም ሕይወታቸውን በሚመሩበት ሥርዓት ፍጹም አያምኑም። እንደ አማኞች ማስመሰላቸው በማሕበረሰባቸው ውስጥ ሚና እንዲጫወቱ ያግዛቸዋል። ምንም እንኳን እውነት ባይሆንም ልክ እንደ አማኞች እንዴት መኖር እንዳለባቸው ማሳየት አለባቸው። በእውነቱ የማይሰማቸውን ነገር መናገር ግድ እንደሚላቸው ይረዳሉ።

*እነዚያንም የነፈቁትንና ለነርሱ ኑ በአላህ መንገድ ተጋደሉ ወይም ተከላከሉ የተባሉትን ሊገልጽ ነው። መዋጋትን (መኖሩን) ብናውቅ ኖሮ በተከተልናችሁ ነበር አሉ፤ እነርሱ ያን ጊዜ ከእምነት ይልቅ ወደ ክህደት የቀረቡ ናቸው፤ በልቦቻቸው የሌለውን በአፎቻቸው ይናገራሉ። አላህም የሚደብቁትን ዐዋቂ ነው። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ ኣል ዒምራን፡167)*

በርግጥ የሙናፊቆች ታዋቂ ውሸት አማኞች ሳይሆኑ "እኔ አማኝ ነኝ" ማለታቸው ነው። ለጥቅማቸው መዋሸትን ቀላል አድርገው ይመለከቱታል። ሌሎችን ለማታለል የአላህን ስም በመጥራት ያንን ሰው ምስክር ያደርጉታል። ስለነዚህ ሰዎች የሚገልጽ አንድ የቁርአን አንቀጽ እንደሚከተለው ይነበባል፡-

*ከሰዎችም ውስጥ እርሱ ክርክረ ብርቱ ሲሆን በቅርቢቱ ሕይወት ንግግሩ የሚደንቅህና በልቡ ውስጥ ባለው ነገር ላይ አላህን የሚያስመሰክር ሰው አለ። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡204)*

ምንም እንኳን በልባቸው እምነት ባይኖርም "ሙእሚኖች ነን" በሚለው ውሸት ላይ ከመጽናታቸው በተጨማሪ የግል ጥቅምን ለማግኘት በርካታ ውሸቶችን ይዋሻሉ። እነዚህን ውሸቶች ለምእመናንም ሆነ ለከሀዲያን ጓደኛቸው ለመንገር ምንም ችግር የለባቸውም።

ማንኛውንም ነገር ሲናገሩ የሚያሳስባቸው ነገር ቢኖር ሌሎችን በማስደሰት ትልቅ ጥቅምን ማግኘት ብቻ ነው። የሚያሳዩዋቸው ጥቂት ባህሪያት በቁርአን ውስጥ ተገልጸዋል።

*ጥቅሙ በቅርቡ የሚገኝና ጉዞውም ቀላል ቢሆን ኖሮ ሁሉም በተከተሉ ነበር። ግና መንገዱ እሩቅና አስቸጋሪ ነው። "ብንችል ኖሮ ካንተ ጋር እንወጣ ነበር" ማለት በአላህ ይምላሉ። በሐሰት መሐላም እራሳቸውን ለጥፋት ይዳርጋሉ። ዋሾዎች መሆናቸውን አላህ ጠንቅቆ ያውቃል። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡42)*

*"ሙሐመድ ሆይ! የመናፍቃንን ባህሪይ አስተዋልከን? ከመጽሐፉ ባለቤቶች ለነዚያ ለካዱት ወንድሞቻቸው "ከሀገር ብትባረሩ አብረናችሁ እንወጣለን" እናንተን*

*የሚጎዳ ጉዳይ ማንንም ፈጽሞ አንታዘዝም፡፡ ብትወጉ እንረዳችኋለን ይላሉ፡፡ እነርሱ ውሸታሞች መሆናቸውን አላህ ይመሰክራል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሐሽር፡11)*

## በቃላቸው አይጸኑም

*ከሀዲያን ሆይ! በተለያዩ እሳቤዎች ውስጥ ናችሁ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አዝ-ዛሪያት፡8)*

በዚህ አንቀጽ እንደተገለጸው የሙናፊቆች ንግግር የጸና አይደለም፡፡ ሁልጊዜ ስለሚዋሹ ንግግራቸው እርስ በርስ ይጋጫል፡፡ ሲናገሩ የአማኞች ጥበብ ስለሚጎድላቸውና የራሳቸውን አስተሳሰብ ብቻ ስለሚከተሉ ቃላቸው አለመጽናቱ ተገቢ ነው፡፡ የዚህ ምክንያት ባለ ማሰባቸው ምክንያት በቁርአን ውስጥ "ማሰብ የማይችሉ" ተብለው የተገለጹት ሙናፊቆች ጽንሰ ሐሳቦችንና ጥልቅ ነገሮችን መመልከት አይችሉም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ማሰብ ስለማይችሉ ጽኑ ያልሆኑ ቃላትን መናገር ምን ያህል አዋራጅ እንደሆነ መረዳት አይችሉም፡፡ ሆኖም ከነርሱ በስተቀር ሁሉም ሰው ይህን ይረዳል፡፡

## ለአላህ (ሱ.ወ) ማደር ያንሳቸዋል

አንድ ሰው በአላህ (ሱ.ወ) ማመኑና ለርሱ መሸነፉ ከእምነት ማሳያ ምልክቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህ ፀባይ ያመኑትንና የካዱትን የሚለይ ዋነኛ ባህሪይ ነው፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) ያመነ ማንኛውም ሰው በእያንዳንዱ በሚገጥመው ችግር ውስጥ ጥሩ ነገር እንዳለ ይረዳል፡፡ እናም ማሳየት ያለበትን ባህሪይ ያሳያል፡፡ በቁርአን አማኞች እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡-

*እነርሱም እነዚያ የታገሱትና በጌታቸው የሚመኩት ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ነሕል፡42)*

ሆኖም ሙናፊቆች በሚገጥሟቸው ችግሮች ጥሩ አሳቢ አይደሉም፡፡ ሁሉም ነገር ከነርሱ በተቃራኒ የሚሠራ ይመስላቸዋል፡፡ እያንዳንዱን ሁኔታ መጥፎ ነገር ይከሰታል ብለው በማሰብ ይኖራሉ፡፡ የዚህ ሐሳብ ዋነኛ ምክንያት ከአላህ (ሱ.ወ) ርቀው በመኖራቸው ምክንያት የሚመጡ ከዚህ ዓለም ጋር የተያያዙ ፍርሃቶችና ጥርጣሬዎች ናቸው፡፡

የዚህ ዋነኛ ማረጋገጫ ሙሉ በሙሉ ያልተጠበቀ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ነው፡፡ በቁርአን ውስጥ የትግል ጊዜያት የዚህ ዋነኛ ማስረጃዎች መሆናቸው ተገልጸዋል፡፡ በረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ጊዜ ጦርነት ሲነሳ ሙናፊቆች ለአላህ (ሱ.ወ) ባለማደራቸው ምክንያት በከፍተኛ ፍርሃት ተውጠው ነበር፡፡

*ሸብር በመጣም ጊዜ የሞት አደጋ እንደሸፈነው ሰው ዓይናቸው ከወዲያ ወዲህ እየተንከራተተ ወዳንተ ሲመለከቱ ታያቸዋለህ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አሕዛብ፡19)*

*ከበላያችሁም፣ ከበታቻችሁም በመጣባችሁ፣ ዓይኖችም በተጭበረበሩ እና ልቦችም ምንቁርት በደረሱ . . . (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አሕዛብ፡10)*

በሌላ የቁርአን አንቀጽ ሙናፊቆች የሚገጥማቸውን ፍርሃት አላህ (ሱ.ወ) ይገልፃል፡፡

*መጠጊያ ቦታ ወይም መሸሸጊያ ዋሻ ወይም አንዳች መግቢያ ቀዳዳ ቢያገኙ ኖሮ ወደርሱ በፍጥነት በሸሹ ነበር፡፡ (ሱረህ አት-ተውባህ፡57)*

## በቶሎ ተስፋ ይቆርጣሉ

የአማኞች አንዱ መለያ ባህሪይ ችግር ወይም መከራ ሲገጥማቸው በፍጹም ተስፋ አይቆርጡም፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ሁሉንም በበጎ በማየት ጥሩ ባህሪይ ያሳያሉ፡፡ በርግጥም አማኞች እጅግ ጠቃሚ እውነታን ይዘዋል፡፡ ይህም አላህ (ሱ.ወ) የሁሉም ነገሮች፣ የእያንዳንዱ ሁኔታና የእያንዳንዱ ቅጽበት ፈጣሪ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ እነሱ ላይ የሚወድቅ ነገር በአላህ (ሱ.ወ) ቁጥጥር ሥር ነው፡፡ ይህ ስለሆነ አማኞች በነሱ ላይ የሚወድቁ ነገሮችን እንደመከራ ሳይሆን በእነሱ ውስጥ ጥሩ ነገር እንዳለ ይረዳሉ፡፡

*እነዚያን መከራ በሚያገኛቸው (ችግር በሚገጥማቸው) ወቅት "እኛ የአላህ ነን፣ መመለሻችንም ወደርሱ ነው" የሚሉትን (አብስራቸው)፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡156)*

ከአማኞች በተቃራኒው ሙናፊቅ እርሱ ላይ የሚደርስን ማንኛውንም ጉዳት አስፈላጊ እንዳልሆነ ያስባል፡፡ በፍጹም ደስተኛ አይደለም፡፡ እናም ሁኔታዎችን ሁልጊዜም በጨለምተኛ ዓይን ያያቸዋል፡፡ ከርሱ ፍላጎት ተቃራኒ የሆኑ ነገሮች ሲያጋጥሙት ትዕግስት ማድረግና ለአላህ (ሱ.ወ) የመሸነፍ ባህሪን ማሳየት አይችልም፡፡ እናም በፍጥነት ተስፋ ይቆርጣል፡፡ ይህም የሆነው ከአላህ (ሱ.ወ) ምንም ስለማይጠብቅ ነው፡፡ የአላህን ገደብ የለሽ ኃይል መቀበል አይችልም፡፡ በዚህች ዓለም ላይ እርዳታና ጥቅም የሚፈልግባቸው ሰዎች ደግሞ የፈለገውን አያደርጉለትም፡፡ ስለዚህ ወላዋይ የሆነው የሙናፊቆች ተስፈ የመቁረጥ አስተሳሰብና የሙናፊቆች የውሸት ግምት ተፈጥሮአዊ ውጤት ነው፡፡

ሙናፊቅ ያምራሉ ብሎ የሚያስባቸው ነገሮች የርሱ እንዲሆኑና ሁሉም ነገር እርሱ እንደሚፈልገው እንዲሆን ይመኛል፡፡ ሁኔታው እንዲህ ከሆነ "ተገቢ"

ፀባይ ያሳያል፡፡ ሆኖም የሚፈልገው ነገር ሁሌም አይከሰትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተስፋ በመቁረጥ አያመሰግንም፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) ላይ ያላቸው እምነት ደካማ የሆኑትና ለአላህ (ሱ.ወ) ማደር የሚያንሳቸው ሰዎች ባህሪይ በቀጣዩ አንቀጽ ተጠቅሷል፡፡

*የሰው ልጅ ጸጋችንን በለገስነው ጊዜ እኛን ከማመስገን ይርቃል፡፡ ከእውነትም ይሸሻል፡፡ አንዳች ክፉ ነገር ባገኘው ጊዜም ተስፋ ይቆርጣል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ኢስራእ፡83)*

## ትዕቢተኞች ናቸው

*ኑ! የአላህ መልዕክተኛ ምሕረትን ይለምኑላችሁ በተባሉ ጊዜ ራሶቻቸውን በእምቢታ ይወዘውዛሉ፡፡ በትዕቢት ሲሸሹ ታየቸዋለህ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙናፊቁን፡5)*

ትዕቢት ከሰይጣን ጋር የመጓዝ ውጤት ነው፡፡ ትህትናና መተናነስ የእምነት ውጤቶች ናቸው፡፡ በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ እንደተጠቀሰው ሙናፊቆች በማይገባቸው መልኩ ኩራተኛና ትእቢተኛ ናቸው፡፡ በምክንያታዊነትና በእምነት አንድ አማኝ ሁሉም ነገር የአላህ (ሱ.ወ) ብቻ እንደሆነና በአላህ (ሱ.ወ) ፊት ረዳት የለሽ አገልጋይ መሆኑን ይረዳል፡፡ በዚህም ምክንያት በፍጹም አይኮራም፡፡ ሆኖም በእምነቱ፣ በአስተሳሰቡና በአረዳዱ ደካማ የሆነው ሙናፊቅ ትዕቢተኛና የራሱን ጉድለት ማየት የማይችል ነው፡፡

እውነታው ግን ያለው የሰው ልጅ በዓይን ሊታይ በማይችልና በሚሊዮኖች ጊዜ ከሰውየው በሚያንስ ቫይረስ ስለመሸነፉ በማያየውና በማይቋቋመው በትንሹ ተህዋሲ ምክንያት ታሞ አልጋ የሚይዝና በሚሸመግልበት ጊዜም እጆቹና እግሮቹ የሚንቀጠቀጡበትና በትክክል መራመድ የማይችል ረዳት የለሽ ፍጡር ነው፡፡ ሆኖም ማሰብና ማስተንተን የማይችሉት ሙናፊቆች እነዚህ ሁሉ ለእነሱ የማይሠሩ ይመስል ሙሉ ለሙሉ በማይጋቸው ትዕቢትና ኩራት ይኖራሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በአላህ (ሱ.ወ) ዘንድና በንጹሕ አዕምሮ በሚያስቡት ዘንድ የተዋረዱ ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የነዚህን ሰዎች ባህሪይ በሌላ አንቀጽ እንዲህ ይገልጸዋል፡-

*ዛሬ በምድር ላይ ያለ አግባብ ትኮሩና ታምጹ በነበራችሁት ሰበብ የውርደትን ቅጣት ትመነዳላችሁ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አህቃፍ፡20)*

## ምቀኞች ናቸው

*ወይስ ሰዎችን አላህ በለገሳቸው ችሮታ ይመቀኛሉ? (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡54)*

ሌላኛው የሙናፊቆች ሰይጣናዊ ባህሪይ ምቀኛ መሆናቸው ነው። ሌሎች ያሏቸውን የላቁ ገጽታዎች መቀበል አይችሉም። እነሱ ብቻ ሁሉም ጥሩ ነገሮች እንደሚገባቸው ይረዳሉ። በዚህም ምክንያት የጸጋ ዓይነቶችን በሙሉ ይመቀኛሉ። የሚመቀኙዋቸው ሰዎች በአጠቃላይ አማኞች ናቸው። ከሚመቀኙባቸው ነገሮች ዋና ዋናዎቹ የአማኞች ብልህነት፣ ውበትና ምቾት፣ እንዲሁም ሃብት ነው። ይህ ምቀኝነት በውስጣቸው ያለው ጥላቻ የበለጠ እንዲጨምር ያደርገዋል። በዚህም ምክንያት የአማኖችን ከቀጥተኛው ጎዳና አፈንግጠው መመልከትን ከልብ ይመኛሉ።

## ተከራካሪዎችና ጠብ ጫሪዎች ናቸው

*እነርሱ ተሟጋች ሕዝቦች ናቸው። (ሱረህ አዝ-ዙኽሩፍ፡58)*

ሙናቆች ከከሀዲያን እኩል ተከራካሪ ናቸው። እናም አስደሳችና መልካም ቃልን አይረዱም። የሚያስደስታቸው ክርክርና ጥል ነው። ሁሉንም ሁኔታዎች በጸብ የሚያስፈጽሙ ይመስላቸዋል። ይህ የሙናፊቆች ባህሪይ በቁርአን ውስጥ ተጠቅሷል።

*መሓላ የሚያበዛን ወራዳ ሁሉ አትታዘዝ። ሃሜተኛና ነገር አሳባቂን። ጽድቅን ሁሉ ከልካይን፣ ወሰን አላፊንና ኃጢአተኛን፤ ጨካኝን፣ ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ የዝሙት ልጅ የሆነን። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ቀለም፡10-13)*

## አባካኞች ናቸው፣ ገደብ አያውቁም

አላህን የሚፈራ ማንኛውም ሰው አላህ (ሱ.ወ) የወሰነውን ገደብ ለመጠበቅ ይጠነቀቃል። በአመለካከቱ ወላዋይ አይደለም። ሆኖም ሙናፊቆች የዚህ ዓይነት ባህሪይ የላቸውም። ስለቀጣዩ ዓለም ስለሚጠራጠሩ በዚህም ምክንያት ስለሠሩት ሥራ የሚጠየቁ ስከለማይመስላቸው አላህ (ሱ.ወ) የወሰነውን ገደብ ይጥላሉ። ቁርአን የቂያማ ቀን ስለረሱት ስለነዚህ ሰዎች ይነግረናል፡-

*ለነዚያ ፍርዱን ቀን መኖር ላስተባበሉ ከሀዲያን። በክህደትና ጥመት ወሰን አላፊ የሆነና ወንጀለኛ እንጂ የፍርዱን ቀን መኖር ማንንም አያስተባብልም። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙጠፊፊን፡11-12)*

አላህን የማይፈሩና እርሱ ባስቀመጠው ገደብ የማይመሩ ሰዎች ለሁሉም ዓይነት ወንጀሎችና የሥነ-ምግባር ልሽቀት ዝግጁ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ጥቂቶች ለራሳቸው ጥቂት ገደቦችን ቢያስቀምጡም ከእውነት ጋር የሚስማሙ አይደሉም፡፡ ይህን ፀባይ የሚያሳዩት ሙናፊቆች በቀላሉ የዘቀጡ ባህሪያትን ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ አዛዣቸው ሰይጣን ካሉበት መንገድ በማስወጣት በቀላሉ ወደጫፍ መምራት ይችላል፡፡ አላህን ስለሚክዱ የርሱ ቅጣት ፍራቻ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ የለውም፡፡ በነዚህ ገደብን በማያውቁ ሰዎች የሚመሠረት ሥርዓት ያለ ጥርጥር አላህ (ሱ.ወ) ፊት እንደሚጠፋ ነው፡፡

## አመስጋኞች አይደሉም

አመስጋኞች ያለመሆናቸው ዋነኛ ማሳያ ለከፍተኛ ቁጣና ጥላቻ ከአማኞች ተቃራኒ የሆኑ አካላትን መደገፋቸው ነው፡፡ ሆኖም ከነርሱ ጋር እስከቆዩ ድረስ አማኞች እነርሱን በመልካም ያዩዋቸዋል፡፡ እነርሱን ለመርዳት ይጥራሉ፣ በአላህ (ሱ.ወ) እንዲያምኑ ይጠሯቸዋል፣ እንዲሁም በቀጣዩ ዓለም ማለቂያ የለሽ ቅጣት ሊቀጡ እንደሚችሉ በመንገር ምክር ይሰጧቸዋል፡፡ ከከሀዲያን ኃይል ጋር በመተባበራቸውና አማኞችን ለማጥመድ መጣራቸው አመስጋኞች ያለመሆናቸው ተግባራዊ መገለጫ ነው፡፡ በርግጥ ለሠሩት ሥራ ምንም ሽልማት አያገኙም፡፡ ከዚህ በተቃራኒ በቀጣዩ ዓለም በዘላለማዊ ቅጣት ይቀጣሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ወደ ዲን የጠሯቸውንና ምክር የጧቸውን ነብያትን የማያመሰግኑትን በፍጹም እንደማይምር ተናግሯል፡፡

> *ምሕረትን ብትጠይቅላቸውም ባትጠይቅላቸውም ለውጥ የለም፡፡ ሰባ ጊዜ ምሕረትን ብትለምንላቸው አላህ ፈጽሞ አይምራቸውም፡፡ ምክንያቱም እነርሱ በአላህ እና በመልዕክተኛው ክደዋል፡፡ (ሱረህ አት-ተውባህ፡80)*

## በሃብት ይኅርራሉ

> *በብዛት መፎካከር (ጌታችሁን ከመገዛት አዘናጋችሁ)፡፡ መቃብሮችን እስከጎበኛችሁ ድረስ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ተካሡር፡1-2)*

የሙናፊቆች የኩራ ምክንያት የያዙት ዓለማዊ ጥቅም ነው፡፡ በውበታቸውና ቁሳዊ ሃብታቸው በመኩራት ለሌሎች ያሳያሉ፡፡ እራሳቸውን የሚቆልሉበት አንዱ ጉዳይ የከሀዲያን ቁጥር ከአማኞች መብለጡ ነው፡፡ በአስተሳሰብ ድክመታቸው ምክንያት ስለዚህ ጉዳይ ያልተረዷቸው ሁለት እውነታዎች አላህ (ሱ.ወ) ይህን ሐቅ በቁርአን መግለጹና የከሀዲያን በቁጥር መብዛት ለአማኞች ጠቃሚ እንጂ ጎጂ አለመሆኑ ነው፡፡ በርግጥ ሁሉም ሰው ጥቂት ቁጥር ያለው በምክንያታዊነት

የሚሠራ ቡድን በማንኛውም ትግል ብዙ ሆኖ ከማያስብና ከዛኛው የተሻለ በርካታ ዕድሎች ያሉት ቡድንን እንደሚያሸንፍ ይረዳል፡፡

## ጸጋዎች ሲሰጧቸው በመሞላቀቅ ከሚገባው በላይ ይደሰታሉ

ሙናፊቆች በራስ ወዳድነት የተሞሉ ናቸው፡፡ እናም እራሳቸውን ከሁሉም በላይ የተሻሉ አድርገው ይቆጥራሉ፡፡ ምንጊዜም ጸጋ ሲሰጣቸው የሚገባቸው ነገር በስተመጨረሻ እንደተሳካ በማሰብ የበለጠ ሞልቃቃ ይሆናሉ፡፡ ለምሳሌ – ሙናፊቆችን አንድ አማኝ ስህተታቸውን በመተቸት ምክር ሲሰጣቸው በመበሳጨት ተስፋ ይቆርጣሉ፡፡ ሆኖም አንድ ሰው በነሱ ላይ ፍላጎት ሲያሳይና ጥቂት ክብር ሲሰጣቸው በኩራት መነፋትና የንቀት ፀባይን ማሳየት ይጀምራሉ፡፡ ከዚህ ውጭ በማስመሰል ባሳዩት አስደሳች ባህሪይ ከተመሰገኑ በድንገት እራሳቸውን ከሁሉም ላይ እንደሆኑ ያስባሉ፡፡ እናም በአካባቢያቸው ያሉትን ይንቃሉ፡፡ ቁሳዊ ጸጋዎች ሲሰጧቸው ተመሳሳይ አስተሳሰብ ብቅ ይላል፡፡ ሆኖም እውነታው አላህ (ሱ.ወ) ሰዎችን ለመፈተን ጸጋዎችን ይጨምራል፡፡ እነሱ ግን ይህን አይረዱም፡፡ የአላህን ሥርዓት መረዳት የማይችለው የዚህ ህብረተሰብ አስተሳሰብና መጨረሻ በቁርአን ውስጥ በቀጣዮቹ ቃላት ተገልጿል፡፡

*የደረሳቸውን መልዕክት በዘነጉ ጊዜ የሁሉንም መልካም (ነገር) በሮች ከፈትንላቸው፡፡ በተሰጧቸው ምድራዊ ጸጋዎች በደስታ በሰጠሙ ጊዜ ይህንዬ በድንገት ያዝናቸው፡፡ ወዲያውኑም ተስፋ ይቆርጣሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አንዓም፡44)*

## ጸጋዎቻቸውን እንደ የበላይነት መገለጫ ይቆጥሩታል

ሙናፊቆች የተሰጣቸውን ጸጋ የበላይነት መገለጫ አድርገው የሚረዱበት መንገድ በቁርአን ውስጥ በተጠቀሰውና በድሮ ጊዜ በነበረው ከሀዲ ቃሩን ምሳሌ ተገልጿል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ሊሞክረው የተትረፈረፈ ሃብት የሰጠው ቃሩን በያዘው ጸጋ ኩራት ተወጥሮ ሃብቱ በሌሎች ላይ በላይነት እንዳለው የሚገልጽ መሰለው፡፡ ይህ ሃብት እንደሚገባው በማሰብ ከአላህ (ሱ.ወ) የተሰጠ ጸጋ መሆኑን ዘነጋ፡፡ በርግጥ ይህ የመነጨው ለአላህ (ሱ.ወ) የሚገባውን ክብር ስላልሰጠና የራሱን ደካማነት ስላልተረዳ ነው፡፡ በቁርአን የተጠቀሰው የቃሩን ምሳሌ ለሙናፊቆች ጠቃሚ ነው፡፡

*ቃሩን ከሙሳ ወገኖች ነበር፡፡ ግና በነርሱ ላይ አመጸ፡፡ በድልብም መክፈቻዎቹ ብቻ የጠነከረ አካል ላላቸው ሰዎች እንኳ የሚከብድ የሆነን ሰጠነው፡፡ ወገኖቹም "አትኩራራ፤ አላህ የሚኮሩትን አይወድምና" አሉት፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ቀሰስ፡76)*

## ድንጉጦች ናቸው

*እነርሱ ከናንተ መሆናቸውን ምለው ይናገራሉ። የናንተ ወገን አይደሉም። ግና የናንተን ጥቃት የሚፈሩ ሰዎች ናቸው። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡56)*

በጎዶሎና በሰይጣናዊ አስተሳሰባቸው ደፋር እንደሆኑ ለማሳየት የሚጥሩት ሙናፊቆች ብርታት ያንሳቸዋል። የጦርነትና የችግር ጊዜያት በልባቸው ያለውን በሽታ ለመግለጽ ወሳኝ ናቸው። ለምሳሌ - በረሱል (ሶ.ዐ.ወ) ጊዜ ሙናፊቆች ለጦርነት ሲጠሩ ለመሳተፍ ቃል ይገባሉ። ሆኖም ጦርነቱ በትክክል ሲነሳ ለሌሎች ካላቸው ኃይለኛ ፍራቻ የተነሳ ፊታቸውን በማዞር ሸሹ። ይህ የፈሪነት ተፈጥሮአቸው ግልጽ ማረጋገጫ ነው።

*ውጊያ ግዴታ በተደረጋቸው ጊዜ ከመካከላቸው ከፊሎች ሰዎችን እንደ አላህ ወይም ከዚያ በላይ መፍራት ያዙ። "ጌታችን ሆይ! ውጊያውን ግዴታ ያደረክብን ለምንድን ነው? እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ብታቆየን ኖሮ መልካም ነበር።" (አሉ)። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡77)*

## በአካልም ሆነ በመንፈስ ቆሻሻዎች ናቸው

ሙናፊቆች የድንቁርና እምነት አባላት ናቸው። በድንቁርና ሕግ የሚመሩ ሰዎች አላህ (ሱ.ወ) ለሰዎች ከመረጠው የአኗኗር ሥርዓት እጅግ ርቀው ይኖራሉ። ሕይወታቸውን በሰይጣንነት ይመራሉ። በቁሳዊ ቅድመ መስፈርት እርስ በርስ መዳኘት፣ እርስ በርስ መመቀኛነት፣ እንዲሁም ሌሎች በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰይጣናዊ ባህሪያት የሐሰት ሃይማኖት ውስጥ ይካተታሉ። ባህሪያቸው አስቀያሚና ደንቆሮ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው፣ ሁሌም መጥፎን እንዲያቅዱ፣ ሁኔታዎችን በፍጹም በመልካም እንዳያስቡ፣ ከሌሎች በተቃራኒ እንዲሠሩና አስተሳሰባቸውም የሰይጣንን መንፈስ እንዲያመጣ ያደርጋል።

በርግጥም በእንደዚህ ዓይነት አስቀያሚ አስተሳሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሙናፊቆች ላይ አላህ (ሱ.ወ) ተከታዩን የወደፊት ፀባይ ተናግሯል።

*ወደነሱ በተመለሳችሁ ጊዜ እንድትተዋቸው ለናንተ በርግጥ በአላህ ይምላሉ። ተዋቸው፤ እነሱ እርኩሶች ናቸውና። ይሠሩት በነበረው ኃጢአት ሳቢያ መኖሪያቸው ገሀነም ነው። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡95)*

ይህ የቁርአን አንቀጽ እንደሚነግረን እነዚህ ሰዎች አካላቸው ንጹሕ ሊሆን አይችልም። በርግጥም አካላዊና መንፈሳዊ ንጹሕነት የተያያዙ ጽንሰ ሐሳቦች ናቸው። በልቦቻቸው ውስጥ መጥፎ ነገር ያለባቸው ያለ ጥርጥር ቆሻሻ ኑሮን ይኖራሉ። ከዚህም በተጨማሪ በልባቸው ውስጥ ባለው በሽታ ምክንያት ቆሻሻነታቸውን እንደሚጨምረው አላህ (ሱ.ወ) በአንድ የቁርአን አንቀጽ ገልጿል።

*ግና ለነዚያ ልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ላለባቸው ወገኖች ከርከሰታቸው ላይ ርክሰትን ጨመረችላቸው። ከሀዲዎች እንደሆኑም ሞቱ። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡125)*

በልባቸው ውስጥ ባለው በሽታ ምክንያት በነብስያቸው ላይ ያለው ጨለማ በፊታቸው ላይ ይገለፃል። የእነዚህ ሰዎች ፊት በቁርአን በቀጣዮቹ ቃላት ተገልጿል።

*ፊቶቻቸውም በድቅድቅ ጨለማ እንደተሸፈኑ ይሆናሉ። (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ዩኑስ፡27)*

በሙናፊቆች ፊት ላይ ጽልመት ሲታይ በአማኞች ፊት ላይ ደግሞ ያለው ብርሃን ለሚመለከተው የመቅለል ስሜት መስጠቱ የሚደንቅ ነው።

## ቆንቋና ሲሆኑ ሌሎችንም በቋጣሪነት ያበረታታሉ

*የወንድና የሴት መናፍቃን ከፊሉ የከፊሉ አካል ነው። ከመልካም ይከለክላሉ። እጆቻቸውንም ከጽድቅ ይሰበስባሉ። (ሱረህ አት-ተውባህ፡67)*

በአላህ (ሱ.ወ) መንገድ ላይ በለጋስነት ማውጣት በቁርአን የታዘዘ ሃይማኖታዊ ተግባር ሲሆን አላህንም ያስደስታል። አላህ (ሱ.ወ) የዚህን ጥቅም በበርካታ አንቀጾች አጽንኦት ሲሰጥበት በተለይ በዚህ ተግባር ላይ የሚሠማራው ሰው ለራሱ እንደሚሠራ ገልጿል። ምክንያቱም በለጋስነት የሚሰጥ ሰው ይህን የሚያደርገው በቀጣዩ ዓለም ያለውን ደረጃና ጀነት ውስጥ ያለውን ቦታ ለመጨመር ነው። አላህ (ሱ.ወ) በርካታ ጸጋዎችን ከራሱ ዘንድ ለአማኞች ይልካል። ሆኖም ሙናፊቆች ይህ ወሳኝ መመሪያ ለእነሱ ጥቅም እንዳለው አይረዱም። ስለዚህ እንዲህ ዓይነት ባህሪን አያሳዩም። ኃይላቸው በሙሉ ቁሳዊ ሃብታቸውን ለመጨመር በመዋሉ ብዙ ባወጡ ቁጥር ብዙ የሚያጡ ይመስላቸዋል። በማንኛውም ሁኔታ ዋና ዓላማቸው የአማኞችን ህብረተሰብ በመበታተንና በመከፋፈል በሃይማኖት የሥነ-ምግባር እሴቶች እንዳይኖሩ ማድረግ ነው። ይህ ከሆነ የድንቁርና ሃይማኖት አባላት ሆነው እንዲሁም እራሳቸውን ሙሉ ለሙሉ ከሃይማኖታዊ የሥነ-ምግባር እሴቶች አርቀው ያለ ምንም ችግር ጉድለታቸው ሳይታወቅ መኖር ይችላሉ።

ስለዚህ ለአማኞች ምንም ዓይነት የቁስና የመንፈስ ድጋፍ መሆን አይሹም፡፡ እንዲሁም አማኞች እርስ በርስ እንዲረዳዱም አይፈልጉም፡፡ እራሳቸው ቋጣሪ ሆነው ሌሎችም ቋጣሪ እንዲሆኑ ያበረታታሉ፡፡ እነዚህ አማኞች ምንም እርዳታ እንደማያስፈልጋቸውና ሁሌም የአላህ (ሱ.ወ) ድጋፍ ከነርሱ ጋር መሆኑን የማይገነዘቡ ሰዎች ሌሎች ሰዎች ቋጣሪ እንዲሆኑ እንዴት እንደሚጠሯቸው በቁርአን ተነግሮናል፡፡

*ከአላህ መልዕክተኛ ዘንድ ላሉት እስኪበታተኑ ድረስ ቀለብን አትለግሱ ይላሉ፡፡ የሰማያትና የምድር ድልቦች የአላህ ናቸው፡፡ ግና መናፍቃን ይህን አይገነዘቡም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙናፊቁን፡7)*

## በማይወዷቸው ነገሮች ላይ ገንዘባቸውን ያወጣሉ

*መጥፎውንም ለመስጠት አታስቡ፡፡ ቢሰጣችሁ ዓይናችሁን ጨፍናችሁ መቀበሉ እየከበዳችሁ እንጂ የማትወስዱትን መጥፎውን ነገር ለመስጠት አታስቡ፡፡ አላህ የማንንም ውለታ የማይሻ ሃብታምና ለመልካም ሥራዎች ውለታ ከፋይ መሆኑን እወቁ፡፡ (ሱረህ አል-በቀራህ፡267)*

ምንም እንኳን ሙናፊቆች በቸርነት ቢለግሱም የሚለግሱት እነሱ በማያምኑባቸው ነገሮች ነው፡፡ ይህ የድንቁርና ሃይማኖት መመሪያ ነው፡፡ ያለ ምንም ዓላማ ለማስመሰል በሙናፊቆች የሚሰጡት ነገሮች ተቀባይነት የላቸውም፡፡ የዚህን ምክንያት አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን ውስጥ ገልጿል፡፡

*የለገሱት ሃብት ተቀባይነት እንዳይኖረው እንቅፋት የሆነው በአላህና በመልዕክተኛው በመካዳቸው፣ ሶላትን እየተሰላቹ እንጂ የማይሰግዱ፣ እየጠሉ እንጂ የማይለግሱ በመሆናቸው ነው፡፡ (ሱረህ አት-ተውባህ፡54)*

## ስል ምላስ አላቸው

*ሽብሩ በተወገደ ጊዜ ምርኮ የቋመጡ ሆነው በሳሉ አንደበቶቻቸው ያነጋግሯችዋል፡፡ ከልብ አላመኑም፡፡ ስለሆነም አላህ ሥራዎቻቸውን ሁሉ ከንቱ አደረገ፡፡ ይህ ለአላህ እጅግ ቀላል ነው፡፡ (ሱረህ አል-አሕዛብ፡19)*

ሙናፊቆች ምንም እንኳን ፈሪና ደካሞች ቢሆኑም ሙእሚኖችን በመጥፎ ቃላታቸው ለማጥቃትና ለመጎዳት ይሞክራሉ፡፡ በሚገርም ሁኔታ ይህን ለመሥራት የሚደፍሩበት አካባቢ ምንም ዓይነት አደጋ እንደሌለ ሲያረጋግጡና ደህንነት ሲሰማቸው ነው፡፡ ያለፈው አንቀጽ ይህን ይገልፃል፡፡ የዚህ ሁሉ ባህሪ ምንጭ ሰይጣን ነው፡፡ እንደምናውቀው ሰይጣን ሰዎችን ለመጉዳት ትክክለኛውን ጎዳና ሊዘጋባቸው ይፈልጋል፡፡ በዚህ ከሰይጣን በተገናኘ አሠራር ሙናፊቆች ሁሉንም

ዕድል በመጠቀም አማኞችን በመጉዳት ሕይወታቸውን አስቸጋሪ ለማድረግ ይጥራሉ፡፡ ሆኖም አማኞችን በማንኛውም ሁኔታ በፍጹም መጉዳት አይችሉም፡፡

## ተጠራጣሪዎች ናቸው

*እነርሱም በሚያዋልል ጥርጣሬ ውስጥ ነበሩ፡፡ (ሱረቱ ሰበእ፡54)*

ሙናፊቆች ሁሌም በልባቸው ውስጥ ጥርጣሬ አለ፡፡ ይህ ጥርጣሬ የሃይማኖት መሠረት ስለሆነው ቁርአን፣ ስለመልዕክተኛውና ስለቀጣዩ ዓለም ነው፡፡ ልባቸው ላይ ባለው ሕመም ምክንያት ሕሊናቸው አያርፍም፡፡ በአንድ በኩል የአማኞችን ለአላህ (ሱ.ወ) እጅ መስጠት ይመለከታሉ፡፡ በሌላ በኩል ስለምኞታቸው ሐሰተኛ ባህሪይ ያስተውላሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በረሱል (ሶ.ዐ.ወ) ጊዜ ከሙስሊሞች መስጊድ ውጪ ሌላ መስጊድ የገነቡት ሙናፊቆች ልባቸው ውስጥ ባለው በሽታ ምክንያት የመነጨው ጥርጣሬያቸው ለዘላለም እንደሚቆይ ገልጿል፡፡

*ያ ያነጹት ግንብ ልቦቻቸው ውስጥ የማይለቅ የጥርጣሬን አሻራ ጥሏል፡፡ ልቦቻቸው ተቆራርጠው እስኪሞቱ ድረስ ጥርጣሬው ምንጊዜም አይለቃቸውም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡110)*

ሰዎችን አያምኑም፡፡ በአንዳች ሁኔታ አንድ ሰው መጥመድ እንደሚያዘጋጅላቸው ወይም እንደሚያዋርዳቸው በመፍራት ሁሉንም ሰው ይጠራጠራሉ፡፡ ይህን አላህ (ሱ.ወ) በአንድ የቁርአን አንቀጽ እንዲህ እስኪላቸው ድረስ ይሠራሉ፡፡

*ጩኸት ሁሉ በነርሱ ላይ እንደሆነ ያስባሉ፡፡(ሱረህ አል-ሙናፊቁን፡4)*

በነዚህ ጉዳዮች ይያዛሉ፡፡ ምክንያቱም እምነታቸውን በአላህ (ሱ.ወ) ላይ አያደርጉም፡፡ እርሱንም እንደ ጓደኛ አይወስዱም፡፡

## ጨካኞች ናቸው

*አላህ ባወረደው ያልፈረዱ እነርሱ በርግጥ በዳዮች ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ማኢዳህ፡45)*

አማኞች በዚህ ምድር ላይ ለማሳካት ከሚፈልጉት ነገሮች አንዱ ጭካኔንና መጥፎነትን በእውነትና በጥሩ ነገር መተካት ነው፡፡ እነዚህ ሐሳቦች የመነጩት አግባብነት ካለው የሥነ-ምግባር እሴቶቻቸው ነው፡፡ አላህን ስለሚፈሩ ለዚህ ግዴታ ያድራሉ፡፡ በድንቁርና ሕብረተሰብ ውስጥ ተስፋፍቶ የሚገኘውን ጭካኔን

በማስወገድ በጥሩነት ለመመለስ የሚጥሩትን አማኞችን በመታገል፣ ከዚህም በተጨማሪ ይህን ከመሃላቸው ገብተው መሥራታቸው የሙናፊቆችን ጨካኝ ነብስያ ያሳያል፡፡ ሙናፊቆች ካመኑ በኋላ ከድተው እራሳቸውን ከጭካኔያዊ አስተሳሰብ ማዳን አይችሉም፡፡ ስለዚህ እንደሚያስቡት በሰላምና በድህንነት የተሞላ ሕይወትን መኖር አይችሉም፡፡ በርግጥም በቁርአን አንቀጽ እንደተገለጸው፡-

*እነዚያ ያመኑትና እምነታቸውን በበደል ያልበከሉት ሰላም የነርሱ ብቻ ነው፡፡ ቅኑን ጎዳና የተመሩትም እነርሱ ብቻ ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አንዓም፡82)*

ሰላምና ደህንነት በሃይማኖታቸው ላይ ቆራጥ የሆኑ አማኞች የሚደሰቱባቸው ጸጋዎች ናቸው፡፡

## ውጫዊ ገጽታቸው አታላይ ነው

*ስትመለከታቸው አካሎቻቸው ያስደንቁሃል፡፡ ሲናገሩ ንግግራቸውን ታዳምጣለህ፡፡ ከግድግዳ በተጠጉ ግንዶች ይመስላሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙናፊቁን፡4)*

ሙናፊቆች እዚህች ዓለም እስካሉ ድረስ በቀጣዩ ዓለም እጅግ እንደሚከፉ አይረዱም፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ለጀነት የታጩ ይመስላቸዋል፡፡ የዚህ እራሳቸውን ማታለላቸው ዋነኛ ምክንያት አካላዊና የተወሰኑ ዓለማዊ ጸጋዎቻቸው ነው፡፡

ለምሳሌ - ሙናፊቅ ሃብታም ወይም አካላዊ ውበት ሊኖረው ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ ሰው ይህን እንደ ጥቅም ቢቆጥረውም እውነታው ግን ይህ ሙከራ መሆኑ ነው፡፡ በሃብት፣ በንብረት ወይም በመስህብነት የተሳበ ሙናፊቅ ሁሉም ነገሮች በመልካም ሁኔታዎች እየሄዱ እንደሆነና እርሱም ኑሮውን መቀጠል እንዳለበት ሊያስብ ይችላል፡፡ ሆኖም እርሱ ሳያውቅ ሁሉም ሥራው ተመዝግቦ ለሠራው መጥፎ ሥራም ጀሀነም ውስጥ በመሰቃየት ይቀጣል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አላህ (ሱ.ወ) እዚህች ዓለም ላይ ለተወሰኑ ጊዜያት ብቻ ነው እንዲቆዩ የሚፈቅድላቸው፡፡ ጊዜያቸው ሲደርስ አላህ (ሱ.ወ) ለመልዕክተኛውና ለሙእሚኖች የሙናፊቆችን ጨለምተኛ አስተሳሰብ ያሳያቸዋል፡፡ ስለዚህ ንፍቅናን የሚረዱ ሙስሊሞች በአታላይ ውጫዊ ገጽታቸው አይሸወዱም፡፡ ይልቅ የአላህን ትዕዛዝ በመሙላት ይታገሉታል፡፡

## የፍጥረታት ሁሉ የበታች ናቸው

*የማይገነዘቡባቸው ልቦች፣ የማያዩባቸው ዓይኖች፣ የማይሰሙባቸው ጆሮዎች አሏቸው፡፡ እነርሱ ልባቸው እንደ እንስሳ፣ ከዚያም የሸባሱ ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አዕራፍ፡179)*

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ገልጿቸዋል፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳን በርሱ መኖር ቢያምኑም፣ የቁርአንን ትዕዛዛትና መመሪያዎች ቢማሩም፣ መልዕክተኛውና ሙእሚኖችን ቢያውቁም ከነዚህ ሁሉ ጀርባቸውን በመስጠት ከእምነት በመሸሽ ወደ ክህደት ገቡ፡፡ አላህን የሚገባውን ፍራቻ ባለመፍራታቸውና እንዲያምኑ ሲጠሩ ባለማመናቸው ከእንስሳ እንኳን በሚያንስ እጅግ ዝቅተኛ በሆነ ባህሪይ ፈጠራቸው፡፡ እናም ለአማኞች እውነታውን ነገራቸው፡፡

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ሙናፊቆችን ከሰዎች ሁሉ ከፉ በማለት ገልጸዋቸዋል፡፡

*ሁለት ፊት የሚያሳዩ፤ ወደነዚህ ሰዎች በአንድ ፊት ወደነዚያ ደግሞ ሌላ ፊትን በማሳየት የሚመጡ ሰዎችን ከሰዎች ሁሉ ከፉ ሆነው ታገኙችኋላችሁ፡፡*

## አያስቡም

አለማሰብ የድንቁርና ሃይማኖት ታዋቂ ገጽታ ነው፡፡ በጥልቅ ባለማስተንተን አዕምሮአቸው ጤነኛ እንደሚሆንና ደስተኛ እንደሚሆኑ ያስባሉ፡፡ ማሰብ የሚጎዳቸው ይመስላቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ማሰብ የሚገባቸው አንዳንድ ነገሮች ያሉ አይመስላቸውም፡፡

ከማያስቡዋቸው ነገሮች አንዱ ሞት ነው፡፡ ሁልጊዜም ከሞት ጋር ፊት ለፊት እንደገጠሙና አላህ (ሱ.ወ) ነብሳቸውን በፈለገው ጊዜ እንደሚወስዳት አይረዱም፡፡ አንድ ሺህ ዓመት እንኖራለን፣ እናም የዚህች ዓለም ጸጋዎችን በነፃ እንጠቀማለን ብለው በማሰብ እራሳቸውን ያታልላሉ፡፡ ከሞት በኋላ ያለውን የሒሳብ ቀን አያስቡትም፡፡ ይህ ባህሪያቸው የሚያስቡ ፍጥረታት አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡ ቀለል ያሉ ጉዳዮችን እንኳን መያዝ አይችሉም፡፡ የሚያስቡ ሰዎች ሁሌም እውነትን ይፈልጋሉ፡፡ ከየት እንደመጡ፣ ፍጥረተ ዓለሙ እንዴት እንደተገኘና ወዴት እንደሚሄዱ ያስባሉ፡፡ ቁርአንን አጥብቀው በመያዝ የሚያስቡ የሰው ልጆችን ባህሪይ ይይዛሉ፡፡

ልክ እንደ ከሀዲያን ሙናፊቆችም ያለማሰብን መጋረጃ ባለማሰብ በዓይናቸው ፊት ይጋርዳሉ፡፡ ባለማሰብ የተመቻቸ ሕይወት እንኖራለን ብለው ስለሚያስቡ በዚህች ዓለም ላይ ያላቸውን ሕይወት በባዶነት ያሳልፉታል፡፡ ከማስተንተን የራቁ ስለሆኑ የሚኖሩበትን ቆሻሻና ጨለማ ዓለም መረዳት አይችሉም፡፡ ከሁሉም በላይ እራሳቸውን እያታለሉ መሆኑን አያውቁም፡፡

## የማሰብ ችሎታቸውን አይጠቀሙም

ሰው መሆንና የተወሰኑ የሰው ልጅ ባህሪያትን መያዝ አንድ ሰው ብልህ ፍጡር ነው ለማለት የተሟሉ መስፈርቶች አይደሉም፡፡ ጥበብ በጣም የተለየ ጽንሰ ሐሳብ ነው፡፡ በበርካታ ገጽታዎች ምክንያት ይፈጠራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የጥበብን ምስጢር በቁርአን ውስጥ ጠቅሷል፡፡ እናም ሰዎች እንዲረዷቸው አበረታቷል፡፡ ከነዚህ ገጽታዎች አንዱ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለአላህ (ሱ.ወ) እጅ መስጠት፣ ሙሉ በሙሉ በርሱ ማመን፣ ለርሱ መሸነፍ፣ እንዲሁም ከርሱ ውጪ ሌላ ረዳትና ጌታ አለመፈለግ ነው፡፡ እርሱን ከማክበር ጋር መፍራት ነው፡፡ እንዲሁም ለአፍታም ቢሆን እርሱን በፍጹም አለመርሳት ነው፡፡ አማኞች ብቻ ናቸው ይህን ይዘው እውነተኛ ጥበብን የሚያገኙት፡፡ በሌላ በኩል ሙናፊቆች ጥበብን ለማስመሰል ይጥራሉ፡፡ በዚህ አመለካከታቸው እንኳን እጅግ ቀላልና ጥልቀት የሌለው ጸባይን ያሳያሉ፡፡ ምንም ያህል ለማስመሰል ቢጥሩም በፍጹም የጥበብን ምልክት ማሳየት አይችሉም፡፡ በርግጥ እውነተኛ ጥበብ የሚገኘው አማኞች ጋር ነው፡፡ ሁሉም ከሀዲያን፣ ሙናፊቆችን አጠቃሎ በቁርአን ውስጥ እንደሚከተለው ተገልጾዋል፡፡

*የማያውቁ ሕዝቦች በመሆናቸው ነው፡፡ (ሱረህ አል-ሐሽር፡14)*

ሌላኛው የማያስቡ መሆናቸውን የሚያሳየው እውነታ ለሁሉም ማስጠንቀቂያዎች ጀርባቸውን መስጠታቸው ነው፡፡ ስለሞት አይቀሬነትና ስለጀሀነም ስቃይ የሚያወሳውን የአማኞች ማስጠንቀቂያ ሰምተው የውሸት ፀባይ ማሳየታቸውን ይቀጥላሉ፡፡ የአላህ (ሱ.ወ) ስም መጠራቱ ቀልባቸው ውስጥ ምንም ፍርሃት እንዲገባ አያደርግም፡፡ እናም ለተሰጧቸው ተግሳጽ ምንም ስሜት አያሳዩም፡፡ ስለዚህ ነው አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን ውስጥ እንደሚከተለው የገለፃቸው፡-

*ደንቆሮዎች፣ ዲዳዎች፣ እውሮች ናቸው፡፡ ፈጽሞ አይመለሱም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡18)*

## መረዳት አይችሉም

ከላይ እንደተጠቀሰው ማሰብ ባለመቻላቸው ሙናፊቆች እውነትን ላለመረዳት እራሳቸውን ዘግተዋል፡፡ እናም ቀልባቸው ላይ ጋን አስቀምጠዋል፡፡ ለዚህም ምላሽ አላህ (ሱ.ወ) ጋኑን ቆልፎታል፡፡ ይህ ጉዳይ በቁርአን ውስጥ በቀጣዮቹ ቃላት ተገልጿል፡-

*አላህ ልቦናዎቻቸውን ዘግቷል፣ ጆሮዎቻቸውንም ደፍኗል፣ ከዓይኖቻቸውም ላይ ግርዶ አለ፡፡ አሳሳሚ ቅጣት ይጠብቃቸዋል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡7)*

*ልቦቻቸው ተሸገዋል፡፡በመሆኑም አይረዱም፡፡ (ሱረህ አት-ተውባህ፡87)*

የሰው ልጅ ከሚያጣቸው የከፉ ነገሮች አንዱ የማሰብና የምክንያታዊነት ችሎታው ነው፡፡ ሙናፊቆች ከውሸታቸው ጋር በሚነፃፀር መልኩ የመረዳትና የማሰብ ኃይላቸውን በሙሉ አጥተዋል፡፡ ኃይላቸውን በተረገሙ ነገሮችና በአመጽ ስለሚያሳልፉ እነሱን እጅግ የሚመለከቷቸውን ጉዳዮች እንኳን ማሰብ አይችሉም፡፡

የዚህ ጥሩ ምሳሌ የሞትን አይቀሬነት አለማሰባቸው ነው፡፡ የሰው ልጆች ሟች መሆናቸውና አንድ ቀን መሞታቸው የታዋቀ ነው፡፡ ሆኖም እነዚህ ሰዎች ሕይወታቸውን የራሳቸውን ጥቅም በማባረር ያሳልፉታል – ማሰብና መረዳት ያለመቻላቸው ግልጽ ማስረጃ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በአንድ የቁርአን አንቀጽ እንደሚከተለው ገልጿቸዋል፡–

*አላህ ልቦቻቸውን ከእውነት አዞሮታል፡፡ እነርሱ የማያውቁ ሕዝቦች ናቸው፡፡ (አል–ቁርአን፣ ሱረህ አት–ተውባህ፡127)*

## በፊታቸውና በአነጋገራቸው መለየት ይቻላል

ሙናፊቆች ማንነታቸው እንዳይታወቅ ትልቅ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ሆኖም በአንድ የቁርአን አንቀጽ አላህ (ሱ.ወ) ለመልዕክተኛው የሙናፊቆችን መለያ እንደሚከተለው ይነግራቸዋል፡፡

*ብንሻ ኖሮ እነሱን ባሳየንህ፣ በምልክቶቻቸውም ባወቅካቸው ነበር፡፡ በአነጋገር ስልታቸው በርግጥ ታውቃቸዋለህ፡፡ አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ያውቃልና፡፡ (አል–ቁርአን፣ ሱረቱ ሙሐመድ፡30)*

በርግጥም አላህ (ሱ.ወ) ከፈለገ ሙናፊቆች በመልዕክተኛው እንዲለዩ ማድረግ ይችላል፡፡ የሚያጋልጣቸው ዋነኛ ባህሪያቸው ሚዛኗን ያልጠበቀችው ነብስያቸው ናት፡፡ እንዲሁም በአማኞች ፊት ላይ ያለው ብርሃን ፊታቸው ላይ አለመገኘቱና ንግግራቸው ውስጥ የአማኞች ጽናትና የመረዳት ችሎታ የሌለው መሆኑ ላይ ነው፡፡ ፊታቸው በጭለማ የተሞላ ነው፡፡ በአንድ የቁርአን አንቀጽ እንደተነገረን ንግግራቸው በልባቸው ውስጥ ያለውን ጥርጣሬና ጽልመት ያንጸባርቃል፡፡

*እነዚያ አላህንና መልዕክተኛውን የሚቃረኑ ወገኖች እነርሱ ከወራዶች ናቸው፡፡ (አል–ቁርአን፣ ሱረህ አል–ሙጃደለህ፡20)*

በአማኞች ፊት ላይ የታማኝነታቸው ውጫዊ መገለጫ የሆነው ብርሃን፣ ታማኝነትና የሰላም ድባብ ምልክት አለ፡፡ ሆኖም የሙናፊቅ ፊት በልቡ ውስጥ ያለውን ክህደትና አለመቀበልን ያሳያል፡፡

*ግልጽና የተብራሩ የሆኑት አንቀጾቻችን በተነበቡላቸው ጊዜ በነዚያ በካዱት ላይ የጥላቻ ስሜት ታያለህ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሐጅ፡72)*

## ደስተኞች አይደሉም

ሙናፊቆች ከሚያሰራጩት እርጉምነት ጥቅም እናገኛለን ብለው ቢያስቡም ሐዘንንና ችግርን እንጂ ምንም ነገር አያገኙም፡፡ ወደነሱ የመጣውን ታላቅ ዕድል አስተባብለዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የአላህ (ሱ.ወ) ቁጣ አግኝቷቸዋል፡፡ መጥፎ ነገር ከፈጸሙ በኋላ ደስተኞች የሚሆኑ ቢመስላቸውም ዳሩ ግን በሙሉ ሕይወታቸው ውስጥ ደስተኛ ያለመሆን፣ ውሱንነት፣ ችግርና ተስፋ መቁረጥ፣ በተለይም በቀጣዩ ዓለምን ይከተሏቸዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ሙናፊቆች በሠሩት ሥራ የሚቀበሉትን ቅጣት በቀጣዩ አንቀጽ ገልጿል፡-

*ጥቂት ይሳቁ፡፡ በፈጸሙት ኃጢአት ሳቢያ ብዙ ያለቅሳሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡82)*

ሙናፊቆች ምንም ያህል ቢኮሩም፣ ምንም ያህል እራሳቸውን ከሌሎች የበላይ አድርገው ቢቆጥሩም፣ እንዲሁም በጥሩ ቦታ ላይ ያሉ ቢመስላቸውም በቁርአን አንቀጽ እንደተገለጸው የተመሰቃቀለ ሕይወት ይኖራሉ፡፡ ይህ አላህ (ሱ.ወ) ከሌላው እንዲለዩ የቀጣቸው ቅጣት ነው፡፡ ከዚህች ዓለም መስህብቶች ምንም ደስታን ስለማያገኙና ከቀጣዩ ዓለም ተስፋ ስለቆረጡ ደስታን መረዳት አይችሉም፡፡ እናም ሁሌም ማልቀስ ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ምናልባት ከጊዜ ወደጊዜ በውጫዊ ገጽታቸው የሚገለጸው ሐዘን ወይም እንደችግር፣ አለመርካትና በራስ ማዘንን የመሳሰሉ አሉታዊ ስሜቶችና ሁሌም ልባቸውን የሚቆጣጠረው ተስፋ መቁረጥ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## የተከፋፈሉ ናቸው

*የእርስ በርስ ሹኩቻቸው እጅግ የበረታ ነው፡፡ አንድ እንደሆኑ ታስባቸዋለህ፡፡ ግና ልቦቻቸው የተበታተኑ ናቸው፡፡ (ሱረህ አል-ሐሽር፡14)*

ምንም እንኳን እርስ በርስ ብቻ እንደ ጓደኛና ምስጢረኛ ቢተያዩም እርስ በርስ አይተማመኑም፡፡ የዚህ ምክንያቱ የራሳቸውን እስስት ባህሪይ ውስጠ

ሕሊናቸው ስለሚረዳው ከነሱ ጋር ያለው ሙናፊቅም እስስት ባህሪይ እንዳለው ይረዳሉ፡፡ ይህ እርስ በርስ ጥሩ ጓደኝነትን እንዳይመሠርቱ ያደርጋቸዋል፡፡

ሙናፊቆች በመሃከላቸው ታላቅ አንድነት እንዳለ ቢገምቱም በፍጹም ሞቅ ያለ ጓደኝነትን፣ ፍቅርና ወንድማማችነትን አያገኙም፡፡ ልባቸው እጅግ ቆሻሻና ደረቅ ስለሆነ የዚህ ዓይነት ስሜት ሊሰማቸው አይችልም፡፡ በትንሽ ችግር ምክንያት ያለ ምንም ማመንታት አንዱ በሌላው ላይ መጥፎ ነገር ሊያወራ ይችላል፡፡ እናም እርስ በርስ ሊጠማመዱ ይችላሉ፡፡ ለራሳቸው ጥቅም ብለው በአካባቢያቸው ያሉ ሁሉንም ሰው ማዋረድ ያስችላቸዋል፡፡

## በአላህ (ሱ.ወ) ላይ ያላቸው እምነት

የሙናፊቆች አንዱ መለያ ባህሪይ በአላህ (ሱ.ወ) ላይ ያላቸው እምነት በቃላት የተወሰነ መሆኑ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሙናፊቅ እምነት አለኝ፣ አላህን እፈራለሁ፣ በቀጣዩ ዓለምና በቂያማ አምናለሁ ይላል፡፡ ሆኖም ከአኗኗር ሥርዓታቸውና ከአስተሳሰባቸው እነዚህ አባባሎች ልባዊ አለመሆናቸውን እንረዳለን፡፡

የሙናፊቅን የእምነት ደረጃ ለመረዳት ቀጣዩ ነጥብ መብራራት አለበት፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) ማመን ማለት ምን ማለት ነው?

ሰዎች በአላህ (ሱ.ወ) ስለማመን ሲያስቡ አላህ (ሱ.ወ) መጀመሪያ ሁሉንም ነገሮች እንደፈጠረና ሰዎችን ለራሳቸው አስተሳሰብ እንደተዋቸው ያስባሉ (በርግጥም አላህ ከዚህ የላቀ ነው)፡፡ ሆኖም በአላህ (ሱ.ወ) ማመን አብዛኛው ሕዝብ ከተረዳው በላይ የጠለቀ ነገር ነው፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) ማመን በርካታ ውጤቶችን ያስገኛል፡፡ ለምሳሌ – እምነት ያለው ሰው የአላህን ልቅና፣ ገደብ የለሽ ኃይልና ፍትሕ፣ እንዲሁም በቀጣዩ የቁርአን አንቀጾች በተገለጸው መሠረት የርሱን የላቁ ስሞችን ያደንቃል፡፡

*ለአላህ መልካም ስሞች አሉት፡፡ (ሱረህ አል-አዕራፍ፡180)*

ከዚህም በተጨማሪ በአላህ (ሱ.ወ) የሚያምን ሰው የርሱን ገደብ የለሽ ኃይል ስለሚረዳ የርሱ ፍራቻ ይኖረዋል፡፡ ሆኖም እውነተኛ እምነትን የማይረዱ ሰዎች ከዚህ በፊት እንደገለጽነው በአላህ (ሱ.ወ) ላይ የተጣመመ እምነት አላቸው፡፡ በርግጥ ለነሱ ልዩ የሆነው ይህ የከሀዲያን ሞኛ ሞኝ እምነት በቁርአን አንቀጾች በቀጣዮቹ ቃላት ተገልጿል፡-

*ሰማያትና ምድርን ማን እንደፈጠረ ብትጠይቀዋቸው "አላህ ነው" ይሉሀል፡፡ ምስጋና ለአላህ ይሆን በል፡፡ ግና ብዙዎቹ ይህን አያውቁም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ሉቅማን፡25)*

*ሰማያትንና ምድርን ማን እንደፈጠረ ብትጠይቃቸው "አላህ ነው" ይሉሀል፡፡ በላቸው፡- ከአላህ ውጪ የምታመልኳቸውን ጣዖታት አያችሁን? አላህ አንዳች ጉዳት ሊያደርስብኝ ቢከጅል እነርሱ ከጉዳቱ ይታደጉኛልን? ወይንም እዝነቱን ሊያሰፍንብኝ ቢሻ እነርሱ እዝነቱን ያስቀሩታልን? በላቸውም፡- አላህ በቂዬ ነው! የሚመኩት በርሱ ብቻ ይመካሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አዝ-ዙመር፡38)*

ከነዚህ የቁርአን አንቀጾች መረዳት እንደሚቻለው ሰዎች አላህ (ሱ.ወ) ሰማያትና ምድርን እንደፈጠረ ያውቃሉ፡፡ ይህን እውነታ፣ እንዲሁም ሁሉንም ነገሮች ሁልጊዜ በራሱ ቁጥጥር ሥር እንዳደረገና ገደብ የለሽ ኃይል እንዳለው ባለመረዳት በአግባቡ አይቀበሉም፡፡

ከከሀዲያን አንድ ቡድን የሆኑት ሙናፊቆች ይህን እምነት አላቸው፡፡ ከከሀዲያን የሚለያቸው አንዱ ነገር ልባቸው የበለጠ ደረቅ መሆኑ ነው፡፡ ይህም የሆነው አንዴ እምነት ነበራቸው፡፡ ሆኖም አሁን ወደ ክህደት ሄደዋል፡፡ በዚህም ምክንያት አላህ (ሱ.ወ) ልባቸውን እውነትን እንዳይረዱ ዘግቶታል፡፡

*ይህ የሆነው እነርሱ (ለይስሙላ) ያመኑ ከዚያም የካዱ በመሆናቸው ነው፡፡ ልቦቻቸው ታሽገዋል፡፡ ስለዚህ ጽድቅን አይረዱም፡፡ እውነትን አይገነዘቡም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙናፊቁን፡3)*

እዚህ ጋ ግልጽ ሆኖ የምናየው ነገር ሙናፊቆች የአላህ (ሱ.ወ) ፍራቻ እንደሌላቸው ነው፡፡ ከአማኞች ጋር በነበሩበት ጊዜ የሃይማኖት የሥነ-ምግባር እሴቶችን የሚያውቁና በአላህ (ሱ.ወ) ስሞች የበላይነትና ኃይል ተጠርተው ሳለ ሙናፊቆች የአላህን ትዕዛዝ አለማክበራቸው የአላህ (ሱ.ወ) ፍራቻ እንደሚያንሳቸው ያሳያል፡፡

ሙናፊቆች "በሁኔታ ላይ የተመሠረቱ ወይም የደህና ጊዜ" ሙስሊሞች ናቸው፡፡ አባባሉ እንደሚገልጸው ዓላማቸው ሁከትን በማስፋፋት ጥቅማቸውን ማግኘት በመሆኑ እንዲሁም ከሁሉም በላይ አላህ (ሱ.ወ) እንደሚገባው ስለማይፈሩት በትንሽዬ ችግር አስቀያሚ ገጽታቸውን ይገልፃሉ፡፡ የሙናፊቆች እምነት ጥራዝነጠቅ መሆኑን አላህ (ሱ.ወ) ለሙእሚኖች በቀጣዩ የቁርአን አንቀጽ ይነግራቸዋል፡-

*ከሰዎች መካከልም "በአላህ አምነናል" የሚሉ አሉ። ግና በአላህ መንገድ ሲታገሉ አንዳች ችግር ሲደርስባቸው ሰዎች የሚያደርሱባቸውን ፈተና የአላህ ቅጣት እንደሆነ አድርገው ይወስዱታል። ከጌታህ የሆነ ውዴታ የመጣልህና ድልን በተጎናጸፍክ ጊዜ "እኛ ከናንተው ጋር ነበርን" ይላሉ። አላህ ከዓለማት ከፍጡራኑ ልቦች ውስጥ ያሉ ምስጢራትን ሁሉ ከማንም ይበልጥ ዐዋቂ አይደለምን? (ሱረህ አል-ዐንከቡት፡10-11)*

አሁን የሙናፊቅን በአላህ (ሱ.ወ) ላይ ያለውን አመለካከት፣ የራቀ እምነትንና አላህን ያለ መፍራት ምክንያትና ውጤት ማየቱ ተገቢ ነው።

## በአላህ (ሱ.ወ) ላይ በምኞቶች ይያዛሉ

ሙናፊቆች የአላህን ኃያልነት በአግባቡ ማድነቅ ስለማይችሉ ስለርሱ በርካታ የተሳሳቱ አመለካከቶች አሏቸው። ከዚህ በፊት እንደተገለጸው አደጋ ሲገጥማቸው አላህን በመርሳት ማንኛውም የሚከሰት ነገር ከአላህ (ሱ.ወ) ቁጥጥር ውጪ መሆኑን ያስባሉ (በርግጥም አላህ ከዚህ የላቀ ነው)። ማንኛውም እውነተኛ አማኝ በአላህ (ሱ.ወ) ላይ መቼም በማያንጸባርቀው ሽብር ይያዛሉ። አላህ (ሱ.ወ) ይህንን ችግር እንዳደረሰባቸው ባለመረዳት በቅጽበት ወደአመጽ ይሄዳሉ። ቁርአን ሙናፊቆች ከመልዕክተኛው ጋር ወደጦርነት ቦታ ሄደው ከመሳዳት ወይም ከሞት ጋር ፊት ለፊት የተጋጠሙ ጊዜ በአላህ (ሱ.ወ) ላይ የያዙትን እምነት ይገልፃል፡-

*ከበላያችሁም፣ ከበታቻችሁም በመጡባችሁ፣ ዓይኖችም በተጭበረበሩና ልቦችም ማንቁርት በደረሱ፣ አላህንም በተለያዩ ጥርጣሬዎች በጠረጠራችሁት ጊዜ የሆነውን አስታውስ። ወቅቱ አማኞች ተፈትነዋል። በብርቱ ድንጋጤና ጭንቀትም ተውጠዋል። መናፍቃንና እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ያለባቸው ወገኖች "አላህና መልዕክተኛው የገቡልን ቃል ባዶ ቅዠት ነበር" ባሉ ጊዜ የሆነውንም አስታውስ። (ሱረህ አል-አሕዛብ፡10-12)*

ከላይ እንደተመለከትነው ችግር ሲገጥማቸው ቀድመው ጠንካራ ነው ብለው የተናገሩትን እምነታቸውን ያጣሉ። እናም የአላህን ታላቅነትና ኃይል ይረሳሉ። ይህ በእምነታቸው በፍጹም ጠንካራ እንዳልነበሩና በፍጹም ምሉዕ እምነት እንዳልነበራቸው ያሳያል። አንድ ሰው በማንኛውም ዓይነት ሁኔታና ቦታ ውስጥ ቢገባ በአላህ (ሱ.ወ) ላይ እውነተኛ እምነት ያለው ሰው የአላህን ኃይል መርሳትና ለደስታ ቢስነት እጅ መስጠት ወይም በርሱ ላይ ሌላ ሐሳብ ማሰቡ ከጥያቄ ውጪ ነው። ከልብ በሆነ እምነት ወደ አላህ (ሱ.ወ) የተጠጉ ሰዎች የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ አላህ (ሱ.ወ) ባሮቹን በክፉና በጥሩ እንደሚፈትን ያውቃሉ።

# አንዳንድ ጊዜ ብቻ አላህን ያስታውሳሉ

*ከመጽሐፉም በራዕይ የተገለጸልህን አንብብ። ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ። ሶላት ከጸያፍና እኩይ ነገር አድራጎቶች ትጠብቃለችና። አላህን ማስታወስ ከሁሉም ነገር በላጭ ነው። አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ያውቃል። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ዐንከቡት፡45)*

የላይኛው አንቀጽ እንደሚገልጸው አላህን ማስታወስ እጅግ ወሳኝ ሃይማኖታዊ ተግባር ነው። እምነት ያላቸው ሰዎች እያንዳንዱን ደቂቃ አላህ (ሱ.ወ) በሰጣቸው ጸጋ እንደሚማሩ ያምናሉ። እናም በተከታታይ አላህን ያመሰግናሉ። ከአላህ (ሱ.ወ) የሚመጡ መልካም ነገሮችን ፈላጊ መሆናቸውንና በሚሠሩት ሥራም በቀጣዩ ዓለም እንደሚጠይቃቸው ይረዳሉ። እንዲሁም እርሱ ከፈቀደ ብቻ ጀነት እንደሚገቡ ያውቃሉ። አላህ (ሱ.ወ) ሁሌም በምላሳቸውና በልቦቻቸው ውስጥ አለ። በሁሉም ቦታ እርሱን ያስታውሳሉ። እናም ይህን ላሉበት ሌላ ሳይፈልጉ የሰጣቸውን ጸጋዎችና በርሱ ስለተፈጠረው የፍጥረተ ዓለም ሚዛን ያወራሉ።

በሌላ በኩል ሙናፊቆች ይህ እምነት በልባቸው ውስጥ ስለሌለ አላህን ማስታወስ የሚገባቸውን ያህል አያወሱትም። የዚህም ምክንያት ለርሱ ከልብ ያደሩ አለመሆናቸውና በርሱ ላይ ጥልቅ እምነት ስለሌላቸው ነው። ስለዚህ እርሱን ለማስታወስ ፈቃደኛ አይደሉም። ምክንያቱም ይህን ከሠሩ የማያምኑባቸውን ነገሮች እየደጋገሙ ነው፣ አልያም እነሱ ለመሥራት ኃላፊነት ያለባቸው ሆኖም ያልሠሯቸውን ነገሮች እየደጋገሙ ነው። ሕሊናቸው ውስጥ ተጽዕኖ ስላለው ይህ ሊጎዳቸው ይችላል። ምንም እንኳን አማኞችን በማስመሰል የአላህን ስም ከልብ ለማስመሰል ቢሞክሩም እራሳቸውን ያጋልጣሉ። እናም በሚሰሟቸው ሰዎች ልብ ላይ ምንም ተጽዕኖ የላቸውም።

ስለዚህ አማኞች መሃል ሆነው አንዳንዴ ላይ በላይ በሆነ ሁኔታ አላህን በማስታወስ ትኩረትን ይስባሉ። በርግጥ በልባቸው ውስጥ ያለውን በሽታ የሚገልጸውን ይህን ወሳኝ ምልክት በቁርአን አንቀጽ ውስጥ አላህ (ሱ.ወ) ገልፆታል፡-

*መናፍቃን አላህን ሊያታልሉ ይሞክራሉ። ግና እርሱ ነው አታላያቸው። ለሶላትም የሚቆሙት እየታከታቸውና ለመታየት ሲሉ ብቻ ነው። አላህንም ጥቂትን እንጂ አያወሱትም። (ሱረህ አን-ኒሳእ፡142)*

*ሰይጣን ተቆጣጥሯቸዋል። አላህን ማስታወስንም አስረስቷቸዋል። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙጃደለህ፡19)*

## በአላህ (ሱ.ወ) ላይ ያጋራሉ

ከአላህ (ሱ.ወ) ውጪ ባሉ አካላት ኃይል ማመን፣ በፍጥረተ ዓለሙ ውስጥ ሚና ይጫወታሉ፣ በፍጥረተ ዓለሙ ሂደት ላይ ውሳኔ መስጠት ይችላሉ ብሎ ማሰብ ከሙናፊቆች መለያ ባህሪያት አንዱ ነው፡፡ የሰው ልጆች ከአላህ (ሱ.ወ) ውጪ ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡ እናም በርሱ ላይ ያጋራሉ፡፡ ምንም ያህል እርሱን ቢክዱትም በልባቸው ውስጥ ያለውን በሽታ የሚገልጸው አላህ (ሱ.ወ) በብቸኝነት እንደሚመለክ አለመፈለጋቸው ነው፡፡ አላህን ማመስገን ያለባቸውን ያህል እርሱን ማስታወስ አይችሉም፡፡ ይህ ከሚያጋልጣቸው ባህሪያቸው ውስጥ አንዱ ነው፡፡

> *እንዳይረዱትም ከልባቻቸው ላይ ሽፋን አለ፣ ከጆሮዎቻቸው ውስጥም ድንቁርና አደረግን፡፡ ቁርአን ውስጥ ጌታህን ብቻ ባወሰህ ጊዜ በሽሽት ወደኋላ ይዞራሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ኢስራእ፡46)*

> *አላህ ብቻ በተወሳ ጊዜ የነዚያ በመጪው ዓለም የማያምኑ ሰዎች ልቦች ይሸማቀቃሉ፡፡ ግና እነዚያ ከርሱ ሌላ ያሉት ሲወሱ በደስታ ይዋጣሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አዝ-ዙመር፡45)*

## አላህን ሳይሆን ሰዎችን ይፈራሉ

ሙናፊቆች አላህን እንደሚወዱ ያወራሉ፡፡ እንዲሁም ሁሉንም የሚሠሩትን ሥራ የአላህን ተቀባይነት ለማግኘት እንደሚሠሩ ይናገራሉ፡፡ ሆኖም በነዚህ ቃላት የአላህን ትዕዛዛትና ድንጋጌዎች የሚያስወግዱበትን መንገድ ይገልፃሉ፡፡

በአላህ (ሱ.ወ) ላይ ከልብ የሆነ እምነት ያለው ሰው አላህን ማፍቀር ብቻ ሳይሆን አክብሮታዊ ፍርሃትንም ይፈራዋል፡፡ በሌላ አባባል እጅግ አላህን የሚወድ ሰው በተመሳሳይ ሰዓት እርሱን እጅግ የሚፈራው ነው፡፡ ምክንያቱም መጀመሪያ ላይ አጽንኦት ለመስጠት እንደሞከርነው ፍራቻና ውዴታ የማይለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ አላህን ለመውደድ አንድ ሰው የርሱን ስሞች መለየት ያስፈልገዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ገደብ የለሽ ኃይሉን እንደሚገልጽና በሚቀጣው ቅጣት ፍትሕን እንደሚያሳይ ይረዳል፡፡

የአላህን ኃይል ማድነቅ የማይችሉ፣ አላህ (ሱ.ወ) እያንዳንዱን ሥራቸውን እንደሚያይ የማይረዱ እርሱን አይፈሩም፡፡ አንድ ሰው "አላህን እወዳለሁ፣ ሆኖም አልፈራውም" ካለ ወይም ይህን የመሰለ አመለካከት ካለው ከሐሳቡ እንደምንረዳው ያ ሰው ከልቡ አይደለም፡፡

በርግጥም የሙናፊቆችን ሕይወት ስንመለከት ይህ መንፈሳዊ ሁኔታ በባህሪያቸው ላይ ተሰራጭቶ እናገኘዋለን። ሙናፊቅ አላህን እፈራለሁ ይላል። ሆኖም የሚሠራውን ሥራ ስንመለከት አማኞችን መጉዳት እንደሚፈልግ እናያለን። ከእነርሱ በተቃራኒው እንደሚሠራና የነርሱን ስም ለማጥፋት አሉባልታ እንደሚያሰራጭ እንረዳለን። ከዚህ የምንገነዘበው ነገር ይህ ሰው አላህን እንደማይፈራው ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሙናፊቅ የራሱ የሆነ ሃይማኖታዊ ጽንሰ ሐሳብ ይሠራል። እናም የሌሎችን ተቀባይነት ለማግኘት በዚያ ሃይማኖት የተጣመሙ ሕጎች መሠረት ይኖራል።

በርግጥ ሁሉም ሰዎች ልዩ ችሎታ አላቸው ብሎ ያምናል። የእያንዳንዱን ሰው ውዴታና ተቀባይነት የማግኘት ግዴታ እንዳለበት ይሰማዋል። ሆኖም አንድ መረዳት የማይችለው እውነታ እያንዳንዱ ሰው በአላህ (ሱ.ወ) የተፈጠረ፣ የአላህ (ሱ.ወ) አገልጋይ መሆኑን ነው። እያንዳንዱ ሰው በአላህ (ሱ.ወ) ፍላጎት የተፈጠረና በርሱ ፍላጎት የሚሞት ነው። ሙናፊቅ ይህን መረዳት አይችልም። ወይም መረዳት አይፈልግም። ምክንያቱም በርሱ ሃይማኖት የሌሎችን ተቀባይነት ማግኘተግ ጠቃሚ ግዴታ ነው። የርሱ ፍርሃቶች በነዚያ መሠረቶች ላይ በእኩል የተገነቡ ናቸው። ሙናፊቆች ሰዎችን መፍራታቸውና የነርሱን ተቀባይነት መፈለጋቸው በችግር ጊዜ እራሱን ይገልፃል። መጀመሪያ ላይ በጦርነቱ እንደሚሳተፉ ቃል ገቡ። ሆኖም የጦርነት ትዕዛዝ ሲሰጣቸው ፍርሃታቸው እምነታቸውን ይዞ ይጠፋል።

*እነዚያን "እጆቻችሁን (ከውጊያ) ሰብስቡ፣ ሶላትንም በትክክል ስገዱ፣ ዘካንም ስጡ" የተባሉትን አላየህምን? ውጊያ ግዴታ በተደረገባቸው ጊዜ ከመካከላቸው ከፊሎቹ ሰዎችን እንደ አላህ ወይም ከዚያ በላይ መፍራት ያዙ። "ጌታችን ሆይ! ውጊያን ግዴታ ያደረግክብን ለምንድን ነው? እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ውጊያን ሳትደነግግብን ብታቆየን ኖሮ መልካም ነበር" ይላሉም። የዚህች ዓለም ጸጋዎች ኢምንት ናቸው። መጭው ዓለም አላህን ለፈሩ ሰዎች በላጭ ነው። ቅንጣት በደል አይደርስባቸውም በላቸው። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡77)*

## የአላህን ዲን ይከዳሉ

አላህን የማይፈሩትና በራሳቸው የተሳሳተ የሃይማኖት አረዳድ የሚኖሩት ሙናፊቆች ለአላህ (ሱ.ወ) ዲን ምንም ዓይነት ታማኝነት የላቸውም። የአላህ መልዕክተኛና አማኞች በቁርአን የሥነ-ምግባር እሴቶች ለመኖር በሚያደርጉት ትግል ሙናፊቆች ሁሌም እንደከዷቸው ነው። ክህደታቸው በቁርአን ውስጥ በቀጣዮቹ ቃላት ተገልጿል፡-

*ቃል ኪዳናቸውን በማፍረሳቸው ረገምናቸው፤ ልቦቻቸውንም ደረቅ አደረግን፡፡ የአላህንም መልዕክት ከትክክለኛው ቦታዎች ይለውጣሉ፡፡ ከተሰጣቸው መልዕክት ከፊሉን ዘነጉ፡፡ ከጥቂቶቹ በስተቀር በአብዛኞቹ ላይ የክህደት ምልክትን አሁንም ታያለህ፡፡ (ሱረህ አል-ማኢዳህ፡13)*

ሙናፊቅ ውሸታም መሆኑን ይረዳል፡፡ አላህን፣ የአላህን መልዕክተኛና አማኞችን ለማታለል ይህን ባህሪይ በማሳየት ቀጣይነት ባለው ክህደት ውስጥ ይኖራል፡፡ እያንዳንዱ ክህደት ወደሌላ ክህደት ያመራል፡፡ ሙናፊቅ ስለእራሱ ክህደት ስለሚረዳ እራሱን ከአማኞች ቢደብቅም እራሱን ከራሱ መደበቅ አይችልም፡፡ የራሱን ወንጀሎች ስለሚመለከት ጥሙቱ ይባስ ይጨምራል፡፡ መጀመሪያ ስለአላህ መልዕክተኛ የሆነ ነገር ይናገራል፡፡ እናም በዚህ ይደሰታል፡፡ ቆይቶ የአላህ መልዕክተኛ ላይ ሃሜት ያወራል፡፡ ይህም እንደዚያው ያስደስተዋል፡፡ ምክንያቱም በእውነተኛ ጓደኛው በሰይጣን መንገድ ላይ እየተጓዘ ነው፡፡

በመቀጠል የአላህ መልዕክተኛ ላይ ያሴራል፡፡ ወንጀሉ በመባዛት ይጨምራል፡፡ አላህን፣ መልዕክተኛውንና አማኞችን መክዳቱ ምንም እንደማይጠቅመው ከዚህ በተቃራኒው ወደጀሀነም እንደሚመራው አይረዳም፡፡ በዚህ ላይ ተመስርቶ ክህደት ውስጥ በቀላሉ ሊገባ ይችላል፡፡ እውነታው ግን እዚህ ምድር ላይ ከሚያጋጥመው ቅጣት በተጨማሪ ሙሉ ስቃይ ያለበት ቅጣት በቀጣዩ ዓለም ይጠብቀዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የሙናፊቆችን መጨረሻ በሌላ የቁርአን አንቀጽ ይገልፃል፡-

*አላህ የወንድም የሴትም መናፍቃንን፣ ከሀዲያንንም በገሀነም እሳት ሊቀጣ ዝቷል፡፡ ከውስጧም ዘወትር ይኖራሉ፡፡ እርሱው በቂያቸው ነው፡፡ አላህ ረግሟቸዋል፡፡ዘውታሪ ቅጣት ይጠብቃቸዋል፡፡ (ሱረህ አት-ተውባህ፡68)*

## ያለ ምንም ማስረጃ በአላህ (ሱ.ወ) ላይ ይከራከራሉ

*ከሰዎች መካከል ስለአላህ ያለ ዕውቀት፣ ያለቅን መመሪያና ያለ ተንታኝ መጽሐፍ እንዲሁ የሚከራከር አለ፡፡ (ሱረህ አል-ሐጅ፡8)*

የመጨረሻ ዓላማቸው ሰዎችን ከአላህ (ሱ.ወ) እና ከዲኑ በማዞር የሃይማኖት የሥነ-ምግባር እሴቶች ዓለም ላይ እንዳይሰራጩ ማደናቀፍ ነው፡፡ ስለዚህ ሰዎችን ለማደናገር በአላህ (ሱ.ወ) ላይ ይከራከራሉ፡፡ እናም ሰዎች በአላህ (ሱ.ወ) የራሳቸውን ምርመራ ላይ እንዲያደርጉ ይጋብዟቸዋል፡፡ ሁከትን የማሰራጨት አዝማሚያ ስላላቸው ሰዎች ለአላህ (ሱ.ወ) ያላቸውን ፍራቻና ክብር ለማስወገድ በጣም ይፈልጋሉ፡፡ ሆኖም ይህን እንቅስቃሴ በብልጣ ብልጥ መንገድ

ያደርጉታል፡፡ በሰይጣን አማካኝነት ተግባራዊ ከሚደረገው ጋር ተመሳሳይ ዘዴን በመጠቀም የሰዎችን ውስጠ ሕሊና በማናገር እነሱን ለማደናገር ይጥራሉ፡፡

ሆኖም መሥራት የሚችሉት ብቸኛው ነገር እነሱን የመሰሉ ሌሎች ሙናፊቆችን ማታለል ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ሙናፊቆች ሰዎችን ከርሱ መንገድ ለማስወጣት የሚያደርጉት ጥረት ወደእራሳቸው እንዴት እንደሚመለስ ገልጿል፡፡

> *ጎኑን ያጠፈ ሆኖ፡፡ ሰዎችን የአላህን መንገድ እንዲሰቱ ለማድረግ ይጥራል፡፡ ይህ ሰው የዚህች ዓለም ውርደት ይጠብቀዋል፡፡ በመጭው ዓለም አቃጣይ ቅጣትን እናቀምሰዋለን፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሐጅ፡9)*

## አላህ (ሱ.ወ) የማይቀበለውን የሥነ-ምግባር እሴት ይደግፋሉ

እስካሁን እንደተመከትነው ሙናፊቆች አላህን በማያስደስቱ ሁሉም ዓይነት ባህሪያት ላይ ይሳተፋሉ፡፡ የሁኔታቸውን መጥፎነት ሳይረዱ በአላህ (ሱ.ወ) በተመረጠውና በተወደደው ዲን፣ በእስልምና ላይ የተጣመሙ ሐሳቦችንና አሉታዊ አመለካከቶችን ይሰጣሉ፡፡ በራሳቸው የተበላሸ አመክንዮ የራሳቸውን ሐሳብ እንደጥሩ፣ እውነትን ደግሞ እንደአስቀየሚ ይቆጥራሉ፡፡

> *እውነትን አምጥተንላችሁ ነበር፡፡ ግና ብዙዎቻችሁ እውነትን ጠይዎች ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አዝ-ዙኽሩፍ፡78)*

በቁርአን እንደተገለጸው እነዚህ ሁለት ፊት ሰዎች "እነዚያ ጥመትን በቅንነት የሸመቱ" (ሱረህ አል-በቀራህ፡16) አላህ (ሱ.ወ) ያወረደውን መለኮታዊ ቃል አሻፈረኝ ብለዋል፡፡ እውነትን እንደ አስቀያሚ ይቆጥራሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ለአማኞች በቁርአን አማካይነት ያወረደላቸው ትዕዛዛት በፍጹም ተግባራዊ የማይሆን ይመስላቸዋል፡፡ እነሱ እራሳቸው በጥላቻና በቆሻሻነት የተሞሉ ስለሆነ ሌሎችም እንደነሱ ይመስሏቸዋል፡፡ እናም በእንደዚህ ዓይነት ተምሳሌት በፍጹም አይኖሩም፡፡

ይህ አስተሳሰብ ለራሳቸውና እነሱን ለመሰሉ ሌሎች ከህዲያን እንደሚሠራ ጥርጥር የለውም፡፡ ጥሩ የሥነ-ምግባር እሴቶችን አላህን በመፍራትና ለርሱ ትዕዛዛት በማደር ብቻ ተግባራዊ ማድረግ ይችላሉ፡፡ አንድ ሰው ጥሩ ፀባይ ሊኖረው የሚችለው በቀጣዩ ዓለም፣ በምጽዐት ቀንና በሒሳብ ሲያምን ብቻ ነው፡፡ በምጽአት ቀን እንደሚጠየቅ የረሳ ማንኛውም ሰው ትዕግስት እንዲያደርግም ሆነ ለሌሎች መስዋእትነት እንዲከፍል የሚያደርገው ነገር የለም፡፡ በነዚህ ሁኔታዎች ላይ መሳተፍ እንዳለበት የሚረዳው የራሱ ጥቅም እጥፍ ድርብ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ

ከሃይማኖት የሥነ-ምግባር እሴቶች ርቆ ለሚኖር ሰው አላፊ በሆነችው በዚህች ዓለም ላይ ሟች ለሆኑ ሰዎች ጥሩ ባህሪይ ማሳየት ትርጉም የለሽ ነው፡፡

ሙናፊቅ በዚህች ዓለምም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ምንም ዓይነት ሽልማት አያገኝም፡፡ በቁርአን እንደተገለጸው ለራሱ ጥቅም ሲል በሚያሳየው ማንኛውም ዓይነት ጥሩ ፀባይ አንድ ሰው የአላህን ትዕዛዛት ከጣሰ የሚሠራው ነገር ሁሉ ዋጋ ቢስ ይሆናል፡፡

*ይህ የሆነው አላህን ያስቆጠውን በመከተላቸውና አላህን የሚያስደስተውን በመጥላታቸው ነው፡፡ በመሆኑም ሥራዎቻቸውን ከንቱ አደርጓል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ሙሐመድ፡28)*

## ቁርአንን መጣሳቸው

መጀመሪያ ይህን ጉዳይ በበቂ ሁኔታ ለመረዳት ከሀዲያን በቁርአን ላይ ያላቸውን አመለካከት ማወቁ ጠቃሚ ነው፡፡ የከሀዲያን አንዱ መለያ ባህሪያቸው በአላህ (ሱ.ወ) እምነት ሳይሆን በአያቶቻቸው እምነት መኖራቸው ነው፡፡ በእነሱ ሃይማኖት በአፈ ታሪክ የተላለፉ መሠረት የለሽ ተግባራትን መፈጸም እንደ ሃይማኖታዊ አምልኮ ይቆጠራል፡፡ በነዚህ ባህሎች በመኖራቸው እራሳቸውን እንደ ፃድቅና ታዛዥ ይቆጥራሉ፡፡ ቁርአንን በማንኛውም ሁኔታ እንደ ቅድመ ሁኔታ አይወስዱም፡፡ የዚህ የድንቁርና ሃይማኖት ፍሬነገር ማሕበረሰቡ በለያቸው ባህሎች ላይ ይወሰናል፡፡

ይህም ጥሩነት ምንም ጥረት በማይደረግባቸው ነገሮች ይወሰናል፡፡ ይህን ጥሩ በመሆን ስም ይሠሩታል፡፡ ይህም ጥሩ የሚያደርጋቸው ይመስላቸዋል፡፡ ለምሳሌ - በመንገድ ላይ ላጋጠማቸው ለማኝ የተወሰኑ የሳንቲም መልሶችን መስጠት ወይም እራሳቸው በድጋሚ የማይለብሷቸውን ያረጁ ልብሶች መስጠት በእነሱ ዓይን እንደ ጥሩ ሥራ ይቆጠራል፡፡ ነገር ግን የጥሩነትና የፃድቅነት እውነተኛ ማብራሪያ በቁርአን ውስጥ ተጠቅሷል፡-

*መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደምሥራቅና ምዕራብ ማዞራችሁ አይደለም፡፡ ግና መልካም ሥራ በአላህ እና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጽሐፍትም፣ በነብያትም ማመናችሁ፣ ገንዘቦቻችሁን በእጅጉ እየፈለጋችሁት ለቅርብ ዘመዶቻችሁ፣ ለየቲሞች፣ ለድሆችና ስንቅ ላለቀበት መንገደኛ፣ ለለማኞችና ራሳቸውን ከባርነት ነፃ ማውጣት ለሚሹ ወገኖችም መለገሳችሁ፣ ሶላትን በተገቢው መልኩ መስገዳችሁና ዘካንም መስጠታችሁ፣ የገባችሁትን ቃል ኪዳን መሙላታችሁ፣ በችግርና መከራ ወቅት ታጋሾች፣ በውጊያ ወቅትም ጽኑ መሆናችሁ ነው፡፡ እውነተኞች፣ ጥንቁቆችም እነዚህ ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡177)*

እነዚህና ሌሎች ቅድመ መስፈርቶች በቁርአን ሲነገሩ የተዛባ እምነታቸውን ከመተው አሻፈረኝ ይላሉ።

*አላህ ባወረደው መልዕክትና የመልዕክተኛውን አስተምህሮ ተመሩ በተባሉ ጊዜ "አባቶቻችን ሲከተሉት ያገኘነው ጎዳና ይበቃናል" ይላሉ። አባቶቻቸው ምንም ነገር የማያውቁና ቅኑን መንገድ የሳቱ ቢሆኑ እንኳን? (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ማኢዳህ፡104)*

*ሴጋሪዎች ጸያፍ ተግባርን በፈጸሙ ጊዜ "አባቶቻችን ይህንኑ ሲፈጽሙ አግኝተናል። አላህም ይህን እንድንፈጽም አዞናል" ይላሉ። "አላህ በፀያፍ ድርጊት ሊያዝም። በአላህ ላይ የማታውቁትን ነገር ትናገራላችሁን?" በላቸው። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አዕራፍ፡28)*

የተለመዱትን "ማህበራዊ ሃይማኖት" በፍጹም መተው አይፈልጉም። በዚህም ምክንያት በአላህ (ሱ.ወ) አንቀጾች ውስጥ የእርስ በርስ ግጭቶችን ይፈልጋሉ። ሰዎችን ከአላህ (ሱ.ወ) መንገድ ለመከልከል ይጥራሉ። እነርሱ እነዚህ ናቸው፡-

*እነርሱ ከአላህ መንገድ የሚከለክሉና ጠማማ ይሆን ዘንድ የሚሹ ናቸው። መጭው ዓለምንም አስተባብለዋል። (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ሁድ፡19)*

ባጭሩ እነዚህ ሰዎች በልዩ ሁኔታ ለቁርአንና ለአላህ (ሱ.ወ) አናቅጽ ምንም ደንታ የላቸውም። እንዲሁም አመለካከታቸው በማንኛውም ወሳኝ መንገድ በፍጹም አይለወጥም።

እዚህ ጋ ነው ሙናፊቆችንና ከሀዲያንን የሚለየው ነጥብ የሚመጣው። ከከሀዲ በተቃራኒ ሙናፊቅ ቁርአንን ሙሉ ለሙሉ አይክድም። እንደማያምንበትና ለርሱ እንደማያድር አጽንኦት አይሰጥም። በተቃራኒው ይህን እውነታ በቻለው አቅም ለመደበቅ ይጥራል። ከአያቶቹ እንደተወረሱ ባህሎች ስለማይቆጥራቸው ከሀዲ በቁርአን ውስጥ ያሉ ትዕዛዘትን ተግባራዊ አያደርግም። ሆኖም ሙናፊቅ ከላይ ሲታይ በርካታ ትዕዛዛትን የሚሠራ ይመስላል።

ነገር ግን ከልቡ ለአላህ (ሱ.ወ) አናቅጽ አላደረም። የራሱ ምድራዊ ምኞቶች ሲነኩበት ሙሉ በሙሉ ስሜት አልባ ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ ምንም እንኳን ለአላህ (ሱ.ወ) እና ለመልዕክተኛው ማደር፣ የረሱልን ትዕዛዛት ከልብ መቀበልን የመሰሉ በርካታ አምልኮዎች መፈጸም ቢገባቸውም "የዕለት ተዕለት" ተግባራትን ብቻ ይፈጽማል። ከዚህም በተጨማሪ ከርሱ ዓለማዊ ጥቅም ጋር የሚጋጩ በጎ የሥነ-ምግባር እሴቶችን ይጥሳል።

ከነዚህ ዓለማዊ ጥቅሞች መካከል እነዚህን ጠቃሚ አመለካከቶች መከልከል፣ ሌሎችን መናቅና ራስን የበላይ ድርጎ ማሰብ ይገኙበታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የምጽዐት ቀንን የሚያስጠነቅቅበትና ሰዎችን ትክክለኛውን መንገድ የሚያሳይበት ቁርአንን በማውረዱ ከጀርባው ታላቅ ጥበብ ይገኛል፡፡ ሆኖም ጥቂቶች ብቻ በቁርአን አምነው ተገቢ በሆነ መልኩ በርሱ ይኖራሉ፡፡ እነዚህ አማኞች ናቸው፡፡

አማኞች በቁርአን ላይ ያሉ ደንቦችን እጅግ ያከብራሉ፡፡ እንዲሁም ለእነሱ ያድራሉ፡፡ አክብሮታቸው የመነጨው ለአላህ (ሱ.ወ) ካላቸው ጥልቅ አክብሮት ነው፡፡ ቁርአን በተነበበ ቁጥር በማዳመጥ በት በአንቀጾቹ ላይ ያስተነትናሉ፡፡ ቁርአን እምነታቸውን ይጨምራል፡፡ እንዲሁም ለልባቸው እርካታና እረፍት ይሰጣቸዋል፡፡ በአንድ የቁርአን አንቀጽ አላህ (ሱ.ወ) አማኞችን እንደሚከተለው ይገልጿል፡-

*እነዚያ አላህ ሲወሳ ልቦቻቸው በፍርሃት የሚርዱት፣ አንቀጾች በሚነበቡ ጊዜም እምነትን የሚጨምሩላቸው፣ በጌታቸው የሚመኩት ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አንፋል፡2)*

ሙናፊቆች በቁርአን ላይ ያላቸው ፀባይ እጅግ በጣም ሁለት ፊት ነው፡፡ የተወሰኑ የቁርአን አንቀጾችን ያከብራሉ፡፡ ሆኖም በሌሎች አይሠሩም፡፡ ቅድመ መስፈርታቸው ዓለማዊ ምኞታቸው ነው፡፡ ያለ ምንም ጸጸት በመልካም መንገድ ገንዘብን ማውጣትና የወንድማቸውን ምኞት ከራሳቸው አስበልጠው መመልከትን የመሰሉ፣ ለነዚያ ለሚከብዷቸው ደንቦች ፊታቸውን ያዞራሉ፡፡ ግዴታ የሆኑ በርካታ ደንቦችን ተግባራዊ ለማድረግ ወላዋይ ናቸው፡፡ እንዲሁም ማንም የማያያቸው ከሆነ ሌሎችን ተግባራዊ አያደርጉም፡፡

የላይኛው አንቀጽ እንደሚገልጸው ሙናፊቆች ቁርአንን ሲያነቡ ክህደታቸው ሲጨምር አማኞች እምነታቸው ይጨምራል፡፡ ይህ አንዱ የአላህ (ሱ.ወ) ተዓምር ነው፡፡ ምክንያቱም ተመሳሳይ የቁርአን አንቀጽን ቢያነቡም ሁለት ሙሉ ለሙሉ የተለያዩ መንፈሳዊ ሁኔታዎች ይከሰታሉ፡፡ ሙናፊቆች ሙሉ ለሙሉ መረዳት ሲያቅታቸው አማኞች በአንቀጾች ውስጥ ያሉትን ጥበብ ይረዳሉ፡፡ ሙናፊቆች መረዳት አለመቻላቸውን እንኳን ላይረዱ ይችላሉ፡፡ እናም ቁርአንን በጥሩ ሁኔታና በርግጥ የተረዱ ይመስላቸዋል፡፡ ይህ ተዓምር የሚከሰትበት ሁኔታ በቁርአን ውስጥ ተጠቅሷል፡-

*ቁርአንን ባነበብክ ጊዜ በአንተና በነዚያ በመጭው ዓለም በማያምኑት ሰዎች መካከል የማይታይ ግርዶ አደረግን፡፡ እንዳይረዱትም ከልቦቻቸው ላይ ሽፋን፣ ከጆሮዎቻቸው ውስጥም ድንቁርናን አደረግን፡፡ ቁርአን ውስጥ ጌታህን ብቻ ባወሰህ ጊዜ በሽሽት ወደኋላ ይዞራሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ኢስራእ፡45-46)*

# ቁርአንን በግልጽ አይክዱም

ሰይጣን እጅግ ምስጢራዊና ሊረዱት የማይችሉት አመክንዮ እንደያዘ ሁሉ ሙናፊቆችም ለራሳቸው ልዩ የሆነ እንግዳ አመክንዮ አላቸው፡፡

ይህ ሙናፊቆች የያዙት ሰይጣናዊ አመክንዮ ያለ ልዩነት በሁሉም ሁኔታ እራሱን ይገልፃል፡፡ ይህ አመክንዮ ቁርአን ላይ ባላቸው አመለካከት አይክዱትም ወይም ከልባቸው አያምኑበትም፡፡ ይህ እንግዳ ባህሪ ነው፤ ምክንያቱም እያንዳንዱ ጥሩ ሕሊና ያለው ሰው በአላህ (ሱ.ወ) መጽሐፍ መሠረት የመኖር አስፈላጊነትን ያውቃል፡፡ ለሌሎች የቁርአን አንቀጾች ተጠራጣሪ ሆኖ በጥቂት የቁርአን አንቀጾች መኖር አስደናቂ ባህሪይ ነው፡፡ ውስጠ ሕሊናቸው በቁርአን መኖር እንደሚገባቸው ሲነግራቸው ዓለማዊ ፍላጎታቸው ኩራት እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ያሳያቸዋል፡፡ የቁርአን አንቀጾችን በደንብ ቢያውቁም እነሱን ለመካድና ዓለማዊ ጥቅምን ለማግኘት ምክንያት ይደረድራሉ፡፡ በርግጥ የሚክዱበት ኩራት በቁርአን ውስጥ እንደሚከተለው ተገልጿል፡-

*ነፍሶቻቸው በጽኑ እያመኑ በማበልና በኩራት አስተባበሏቸው፡፡ የበካዮች ፍፃሜ እንዴት እንደሆነ ተመልከት፡፡ (ሱረህ አን-ነምል፡14)*

ሙናፊቆች በአላህ (ሱ.ወ) አንቀጾች ላይ ያላቸውን ወላዋይነት አይገልጹም፡፡ ይህን ከመሥራት እራሳቸውን ያግዳሉ፡፡ እነዚህን ኃጢአቶች እውስጣቸው ይደብቁታል ወይም ልክ እንደ እነሱ የተጣመመ አመክንዮ ላላቸው ሰዎች ይገልፃሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይህን የነርሱን የተጣመመ አመክንዮ ገልፆታል፡-

*አንዲት ምዕራፍ በወረደች ጊዜ "የሚያያችሁ ሰው አለን?" (በመባባል እርስ በርስ) ይተያያሉ፡፡ ከዚያም ይሄዳሉ፡፡ አላህ ልቦቻቸውን አዙሮታል፡፡ እነርሱ የማያውቁ ሕዝቦች ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡127)*

ሙናፊቆች በግልጽ ቁርአንን አይክዱም፡፡ ሆኖም የሚያምኑበት ያስመስላሉ፡፡ ይሰግዳሉ፡፡ እንዲሁም ከአማኞች ጋር አብረው ይኖራሉ፡፡ ሰደቃ ይሰጣሉ፣ ይፆማሉም፡፡ ቁርአንን ሙሉ ለሙሉ ቢክዱ እነዚህን ነገሮች አይሠሩም፡፡ እንዲሁም ከአማኞች ጋር አብረው ይኖራሉ፡፡ እንዲሁም ከሀዲያን አስተሳሰባቸውን እንዳጸኑት ሁሉ ሐሳባቸውን ያንጹ ነበር፡፡ ሆኖም አንዱ ጠቃሚ ነገር ምንም እንኳን ሙናፊቆች ቁርአንን ባይክዱም፣ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ተግባራትን የፈጸሙ ቢያስመስሉም ዓላማቸው ሌላ ነው፡፡ ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው እምነታቸው በምላሳቸው ላይ እንጂ በልባቸው ውስጥ የለም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሃይማኖታዊ ተግባራትን በሚፈጽሙበት ጊዜ የራሳቸውን ሃይማኖት ተግባራዊ እያደረጉ ነው፡፡ ለምሳሌ – ሶላታቸው ለታይታ የሚሰገድ የሙናፊቆች ሃይማኖት ሶላት ነው፡፡ እንዲሁም ምጽዋታቸው ያለ ፍላጎታቸው ለታይታ የተሰጠ ነው፡፡ እነዚህ በቁርአን አንቀጾች እንደተገለጸው በአላህ (ሱ.ወ) ዘንድ ተቀባይነት የላቸውም፡፡

## የቁርአንን ትርጉም ያዛባሉ

ከዚህ በፊት እንደተገለጸው የሙናፊቆች እጅግ ጠቃሚ ባህሪይ ሁከትና አለመስማማትን ለማሰራጨት የሚያደርጉት ጥረት ነው፡፡ ዓላማቸውን ለማሳካት በርካታ መንገዶችን ይጠቀማሉ፡፡

ለምሳሌ – ረሱልን (ሶ.ዐ.ወ) ባለማክበር አማኞችን ለመረበሽ ይሞክራሉ፡፡ እንዲሁም የውሸት ወሬዎችን በማሰራጨት በአማኞች መሃል ብጥብጥ ማስነሳት ይፈልጋሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁከት የሚያስነሱበት ጠቃሚ መንገድ አላቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይህ ከባድ አደጋ መሆኑን በመግለጽ አማኞችን አስጠንቅቋል፡፡

*(ሙሐመድ ሆይ!) መጽሐፉን ባንተ ላይ ያወረደው እርሱ ነው፡፡ ከውስጡ ግልጽና የማያሻማ ትርጉም ያላቸውን አናቅጽ ይዟል፡፡ እነኛህ ግልጽ አናቅጽ የመጽሐፉ መሠረቶች ናቸው፡፡ አሻሚ ትርጉም ያላቸው አንቀጾችንም አካቷል፡፡ እነዚያ ልቦናቸው ውስጥ የማፈንገጥ ባህሪይ ያላቸው ሰዎች ለጥመት ለመዳረግና ባሻቸው መልኩ ለመተርጎም ሲሉ፣ ከርሱ አሻሚ ትርጉም ያላቸውን አናቅጽ ይከተላሉ፡፡ የአሻሚ አንቀጾችን ብቸኛ መልዕክት ከአላህ ውጭ አንድም የሚያውቅ ኃይል የለም፡፡ ጥልቅ ዕውቀት ያላቸው ወገኖች "በርሱ አምነናል ሁሉም ከአላህ የተላለፉ ናቸው" ይላሉ፡፡ የሚረዱት ጥልቅ ግንዛቤ ያላቸው ወገኖች ብቻ ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ ኣል ዒምራል፡7)*

ይህ እንደሚገልጸው ሙናፊቆች የአላህን አናቅጽ በተዛባ መልኩ ይተረጉሙታል፡፡ ሰዎችን ለማታለል በመሞከራቸውና ስህተት ውስጥ በመጣላቸው ምስጋና የሚገባቸው ይመስላቸዋል፡፡ በርግጥም አያዎቹን በመግለጽ የተወሰኑ ለሁከት የሚጠቀሙባቸው የቁርአን አንቀጾችን ከህዲያን ሊረዷቸው እንደማይችሉ አላህ (ሱ.ወ) ገልጿል፡፡ ስለዚህ ሙናፊቆች ቁርአንን አዛብተው መተርጎማቸው በአማኞች ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ የለውም፡፡ በቁርአን ውስጥ እንደተገለጸው በዚህ ብልጣ ብልጥ የሙናፊቆች አቀራረብ አማኞች መሥራት ያለባቸው ነገር ለአላህ (ሱ.ወ) መጽሐፍ ሙሉ ለሙሉ ማደር ነው፡፡ አማኞች ይህን ካደረጉ ሙናፊቆች በእነሱ ላይ በማንኛውም መልኩ ምንም ዓይነት ጉዳት ማድረስ አይችሉም፡፡ የዚህ ምክንያት አማኞች በልዩ ሁኔታ ለአላህ (ሱ.ወ) አናቅጽ

ትኩረት መስጠታቸው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ለሰጣቸው የመረዳት ችሎታ ምስጋና ይግባውና "በልባቸው በሽታ ላለባቸው ሰዎች" እጅግ በጣም ንቁና ተጠባባቂ ናቸው፡፡ በቀጣዩ ዓለም ሙናፊቆች ስለተናገሩት እያንዳንዱ ቃል ይጠየቃሉ፡፡ በራሳቸው አመለካከት ስላመጡት የተጣመመ መረጃ ይጠየቃሉ፡፡ እንዲሁም የራሳቸው ወጥመድ በራሳቸው ላይ ሲመለስ ይመለከታሉ፡፡

## በአላህ (ሱ.ወ) ዲን ላይ ያላቸው አመለካከት

ሙናፊቆች እጅግ ልዩ አመክንዮ አላቸው፡፡ ቁርአንን ቢማሩም በሃይማኖታዊ እሴትና በቀጣዩ ዓለም ላይ ያላቸው አመለካከት ከቁርአን አመክንዮ ጋር ይጋጫል፡፡ ለእነሱ ሃይማኖታዊ እሴት በፍጹም ቦታ የለውም፡፡ ይህ እጅግ አስገራሚ አቋም ነው፡፡ ሙናፊቆች ከሃይማኖት የለሾዎች ይለያሉ፡፡ ልክ እንደነሱ በሃይማኖት አያምኑም፡፡ ነገር ግን እራሳቸውን ከሃይማኖትና ከአማኞች ማራቅ አይችሉም፡፡ የዚህ ቡድን አባላት በቁርአን በሚከተሉት ቃላት ተገልጸዋል፡፡

> *በሁለቱ መካከል ይዋልላሉ፡፡ የዚህኛውም፣ የዚያኛውም ወገኖች አይደሉም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡143)*

ሙናፊቆች በአንድ ሐዲሥ እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡-

> *የሙናፊቅ ምሳሌ በሁለት መንጋዎች መሃል እንደሚዋልል በግ ነው፡፡ አንዴ ወደአንዱ ይሄዳል፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደሌላኛው ይሄዳል፡፡*

በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ እጅግ የላሉ ሲሆኑ አምልኮአቸውን ለታይታ ብቻ ይተገብራሉ፡፡

> *እነዚያንም ያመኑትን በተገናኙ ጊዜ አምነናል ይላሉ፤ ወደ ሰይጣኖቻቸውም ባገለሉ ጊዜ እኛ ከናንተ ጋር ነን፤ እኛ (በነሱ) ተሳላቂዎች ብቻ ነን ይላሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡14)*

ሙናፊቆች ከአላህ (ሱ.ወ) ተቀባይነት ላይ እጅግ በራቀ መሠረት ላይ ይገኛሉ፡፡ ምንም እንኳን አንቀጾችን ቢያነቡም ሃይማኖት ምንም ተጽዕኖ አያሳድርባቸውም፡፡ እንዲሁም ከሃይማኖት የሥነ-ምግባር እሴቶች እጅግ የራቁ ናቸው፡፡ በጥልቅ ማሰብ፣ መረዳትና ማገናዘብ ስለሚሳናቸው የራሳቸውንና የአማኞችን ሁኔታ መረዳት አይችሉም፡፡ ለአላህ (ሱ.ወ) እንዴት መኖር እንዳለባቸው አያውቁም፡፡ ምክንያት ባይኖራቸውም በርሱ ላይ ጦርነት አውጀዋል፡፡

ስለዚህ ሙናፊቆች ምንም ጠንከር ያለ እምነት የላቸውም፡፡ ትንሽ ችግር ተስፋ ያስቆርጣቸዋል፡፡ እናም በአላህ (ሱ.ወ) ሃይማኖት ላይ የሚያንሳቸው

እውነተኛ እጅ መስጠት ሁሉም ሊያየው በሚችለው መልኩ ይጋለጣል፡፡ በችግር ጊዜ ከከሀዲያን ጋር ኃይላቸውን አንድ ያደርጋሉ፡፡ ሃይማኖታዊ ተግባራትንና የቁርአን ግዴታዎችን በተመለከተ ፍርሃት የሚያንሳቸው መሆኑን ይህ መረጃ ያጠናክረዋል፡፡

በሃይማኖት ላይ ያላቸው መላላት በርካታ ምልክቶች አሉት፡፡ ለምሳሌ – ሙናፊቆች አላህን ጥቂትን እንጂ አለማስታወሳቸው በሃይማኖት የሥነ–ምግባር እሴቶችና እምነት ላይ ያላቸው መላላት ወሳኙ ማስረጃ ነው፡፡ በድጋሚ በቁርአን ውስጥ ሶላትን ለመስገድ ፍላጎት እንደሌላቸውና ምጽዋትንም ለታይታ ብቻ እንደሚያወጡ እናያለን፡፡ አማኞችን ለማስደነቅና ለታይታ ብቻ የሚፈጽሚቸውን እነዚህን ሃይማኖታዊ ተግባራት በሙሉ ለብቻቸው ሲሆኑ አለመፈጸማቸው ምንም አያስደንቃቸውም፡፡ ለግል ጥቅማቸው ብለው የሚያደርጓቸውን ግዴታ የሆኑ ተግባራትን ለብቻቸው ሲሆኑ ይፈጽማሉ ተብሎ አይገመትም፡፡ ይህ ከእነሱ አመክንዮ ጋር ተስማሚ አይደለም፡፡ እንዲሁም እነሱ በሃይማኖት ላይ ካላቸው አመለካከት ጋር ይጋጫል፡፡ ሙናፊቆች የተብራሩባቸው የተወሰኑ አንቀጾች እንደሚከተለው ይነበባሉ፡–

*መናፍቃን አላህን ያታልላሉ፤ እርሱም አታላያቸው ነው (ይቀጣቸዋል)፤ ወደ ሶላትም በቆሙ ጊዜ ታካቾች፣ ሰዎችን የሚያሳዩ ሆነው ይቆማሉ፤አላህንም ጥቂትን እንጂ አያወሱም፡፡ (ሱረህ አን–ኒሳእ፡142)*

*ወዮላቸው ለሰጋጆች፤ ለነዚያ እነሱ ከሰግደታቸው ዘንጊዎች ለሆኑት፤ ለነዚያ እነሱ ይውልኝ ባዮች ለሆኑት፡፡ (አል–ቁርአን፣ ሱረህ አል–ማውን፡4–6)*

*እነዚያም ለሰዎች ይውልኝ ሲሉ ገንዘቦቻቸውን የሚሰጡ፣ በአላህና በመጨረሻውም ቀን የማያምኑ (ይቀጣሉ)፤ ሰይጣንም ለሱ ጓደኛው የሆነ ሰው ጓደኝነቱ ከፋ! (አል–ቁርአን፣ ሱረህ አን–ኒሳእ፡38)*

ሙናፊቆች ሃይማኖታዊ ተግባሮቻቸውን ሳይወዱ ይፈጽሙታል፡፡ እነሱ ሕይወታቸውን የሰጡበት ብቸኛው ርዕስ የሌሎች ሰዎችን ተቀባይነት ማግኘት ነው፡፡ ለነሱ በሌሎች መወደድ፣ መመስገንና ተቀባይነት ማግኘት በዚህች ዓለም ላይ የሚያገኙት ትልቅ ሽልማት ነው፡፡ እያንዳንዱን የሚሠሩት ነገር ይህን ምስጋና ለማግኘት ነው፡፡ ስለዚህ ከአማኞች ጋር በሚቆዩበት ጊዜ እያንዳንዱ የሚሠሩት ነገር ማታለልን የያዘ ነው፡፡ የራሳቸውን ስህተት ባለመረዳት አማኞችን፣ መልዕክተኛውንና አላህን እንኳን (አላህ ከዚህ የላቀ ሆኖ ሳለ) የሚያታልሉ ይመስላቸዋል፡፡ የሚሠሩት ማንኛውም ሥራ ከልባቸው ስላልሆነ በቀጣዩ ዓለም ሽልማትን አያገኙም፡፡

## እውነትን አይከላከሉም

በአማኞች መሃል በሚያሳልፉት ጊዜ ሙናፊቆች እራሳቸውን ለማመሳሰልና እንዳይለዩ ለማድረግ የአስመሳይነትን ሚና ይጫወታሉ፡፡ ሃይማኖታዊ ተግባራትን ለመመሳሰል ይፈልጋሉ፡፡ ሆኖም ዓለማዊ ጥቅማቸውን የሚጎዱትን አይጠጓቸውም፡፡ ለምሳሌ – ሰዎችን ወደተገቢው የሥነ–ምግባር እሴት መጥራትና ስለእውነት መናገር ተገቢ እንዳልሆኑ የሚቆጥሯቸው ኃላፊነቶች ናቸው፡፡ ሌሎች ይህን ሥራ ሲሠሩት ለመመልከት፣ እንዲሁም እራሳቸው ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁ አይደሉም፡፡ ስለዚህ እውነትን መከላከልን በመተው ረገድ ጠንቃቆች ናቸው፡፡

በማንኛውም ሁኔታ እዚህ ጋር ያለ መጽናት አለ፡፡ አላህን የማያስታውስ፣ ለሃይማኖት ከልብ የመነጨ ጥላቻ ያለውና ለአላህ (ሱ.ወ) እጃቸውን የሰጡ አማኞች ላይ ጥላቻ ያለው ሰው በፍጹም የቁርአን ትዕዛዛትንና ለአላህ (ሱ.ወ) መታዘዝ ያለውን ጥቅም ለሰዎች ማስተላለፍ አይችልም፡፡ እነዚህ ሰዎች በተገቢ የሥነ–ምግባር እሴቶች ስለማይኖሩ ይህን ለሌሎች ማብራራት አይችሉም፡፡ እንዲሁም በየትኛውም ዓይነት ሁኔታ ይህን የማድረግ ዓላማ የላቸውም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን ውስጥ እንደ ጠቃሚ ሃይማኖታዊ ግዴታ ያዘዘው መልዕክትን ማስተላለፍ በፍጹም ተግባራዊ የማያደርጉት ነገር ነው፡፡ በመልካም ማዘዝ፣ ከመጥፎ መከልከል፣ እንዲሁም በቁርአን ነፀብራቅ መሠረት ሰዎችን ማስታወስ ሙናፊቆች በፍጹም የማይሠራቸው ተግባራት ናቸው፡፡ እውነተኛ ዓላማቸው የሌሎችን ተቀባይነት ለማግኘት ስለሆነ ማንንም ማበሳጨት አይፈልጉም፡፡ እናም በፍጹም የሚያዩት ስህተት ውስጥ ጣልቃ አይገቡም፡፡

## ከትግል ወደኋላ ለመቅረት ምክንያት ይደረድራሉ

ከአማኞች ጋር በሚቆዩበት ጊዜ ከሙናፊቆች ዋነኛ ዓላማዎች መካከል አንዱ የራሳቸው ጥቅም መሆኑን አይተናል፡፡ ያለጥርጥር ከጥቅማቸው ጋር ከሚጋጩ ነገሮች አንዱ በአማኞች ላይ ግዴታ የተደረጉት የትግል ጊዜያት ናቸው፡፡ ሙናፊቆች ከግል ጥቅም አንፃር ምንም የማያመጣላቸውና ዓላማውንም የሚጠራጠሩበት ወይም ከልብ ያላመኑበት ትግል ውስጥ መግባት ምንም ጥቅም እንደሌለው ይረዳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ግንዛቤ ስለሚያጥራቸው ይህን ትግል በቀጣዩ ዓለም ሽልማት ያለው ሳይሆን ሕይወትና ንብረት የሚጠፋበት አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ለአላህ (ሱ.ወ) ሲሉ መስዋዕትነት መክፈልና ችግርን መቋቋም የመሳሰሉ የላቁ ሥነ–ምግባራትን መረዳት አይችሉም፡፡

በረሱል (ሶ.ዐ.ወ) ጊዜ ሙናፊቆች የጦርነት ትዕዛዝ ሲተላለፍ በፍጥነት መሸሽ ጀመሩ፡፡ እናም ወንጀላቸውን ለመደበቅ በርካታ ውሸቶችንና ምክንያቶችን ደረደሩ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የወረዱት ጥቂት አንቀጾች የሚከተሉት ናቸው፡፡

*እነርሱ "ኑ! በአላህ መንገድ ተዋጉ፤ ወይም ቢያንስ ተከላከሉ" በተባሉ ጊዜ "ውጊያ መኖሩን ብናውቅ ኖሮ በርግጥም እንከተላችሁ ነበር" አሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ ኣል ዒምራን፡167)*

*ጥቅሙ በቅርቡ የሚገኝና ጉዞውም ቀላል ቢሆን ኖሮ በተከተሉህ ነበር፡፡ ግና መንገዱ እሩቅ ሆነባቸው፡፡ "ብንችል ኖሮ ከናንተ ጋር እንወጣ ነበር" በማለት በአላህ ይምላሉ፡፡ ራሳቸውን ለጥፋት ይዳርጋሉ፡፡ ዋሾዎች መሆናቸውን አላህ ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ (ሱረህ አት-ተውባህ፡42)*

*እነዚያ የቀሩት ከመልዕክተኛው ተነጥሎ መቅረታቸው አስደሰታቸው፡፡ በአላህ መንገድ በገንዘቦቻቸውም በነፍሶቻቸውም መታገልን ጠሉ፡፡ "በዚህ ሞቃታማ ወቅት አትዝመቱ" ሲሉም ሰዎችን አሳነፉ፡፡ የገሀነም እሳት ይበልጥ ሊቃጣይ ነው በላቸው - ቢገባቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡81)*

*በአላህ እንዲያምኑና ከመልዕክተኛው ጋር በመሆን እንዲታገሉ የሚጋብዝ ምዕራፍ በወረደ ጊዜ ከመካከላቸው የሰፊ ሃብት ባለቤቶች ፈቃድ ይጠይቁሃል፡፡ "ከተቀማጮች እንሆን ዘንድ ተወን" ይሉሃል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡86)*

*ከነርሱም ውስጥ የተወሰኑ ቡድኖች "የየስሪብ ሰዎች ሆይ! ጥቃቱን መቋቋም አትችሉም፤ ስለዚህ ተመለሱ" አሉ፡፡ ከመካከላቸውም ከፊሎቹ "ቤቶቻችን ጠባቂ አልባ ናቸው" በማለት ፈቃድ ጠየቁ፡፡ ግና ጠባቂ አልባ አልነበሩም፡፡ ፍላጎታቸው ሽሽት ብቻ ነበር፡፡ (ሱረህ አል-አሕዛብ፡13)*

በትግል ጊዜ የሚጋለጠው ይህ ባህሪይ የሙናፊቆች አመክንዮ መገለጫ ጠቃሚ ማስረጃ ነው፡፡ እስካሁን ሲተገብሩት የነበረውን አማኞችን የማመሳሰል ድርጊታቸውን በመተው እውነተኛ ባህሪያቸውን ይገልፃሉ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ትግሎች ላይ አማኞች ተፈጥሮአቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ያሳያሉ፡፡

ሙናፊቆች ለወደፊት ትግሎች መዘጋጀት የሚያንሳቸው መሆኑ የባህሪያቸው መገለጨ ነው፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) መንገድ የመታገል ዓላማ ስለሌላቸው መዘጋጀት አስፈላጊ ነው ብለው አያስቡም፡፡ ሆኖም በተመሳሳይ ሰዓት ይህ የሚያቅዱት እንቅስቃሴ ማስረጃ ነው፡፡ ሆን ብለው ሃይማኖታዊ ተግባራትን ከመፈጸም ይታቀባሉ፡፡ እናም እነዚህን በእምነት ላይ የተመሠረቱ የወደፊት ዝግጅቶችን አያደርጉም፡፡ በአንድ አንቀጽ የሚከተለው ተገልጿል፡-

*መዝሙት ቢፈልጉ ኖሮ ዝግጅት ባደረጉ ነበር። ግና አላህ የነርሱን መንቀሳቀስ ጠላ። እናም ወደኋላ እንዲቀሩ አደረገ። "ከተቀማጮች ጋር ተቀመጡ" ተባሉ። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡46)*

## በአማኞች ላይ ያላቸው እምነት

ሙናፊቆች በአላህ (ሱ.ወ) ዲን ላይ ጦርነት አውጀዋል። መልዕክተኛውን ይቃወማሉ። እንዲሁም የአላህን አናቅጽ መስማት አይፈልጉም። ስለዚህ አንድ ሰው እነርሱ ለአማኞች ቀረቤታ ያሳያሉ ብሎ መገመት አይችልም። አማኞች ሙናፊቆች የሚቃወሟቸውን የሃይማኖት መስፈርቶች ተግባራዊ ማድረጋቸውና በአላህ (ሱ.ወ) አናቅጽ መኖራቸው በነርሱ ላይ ጠላትነት እንዲሰማቸው በቂ ምክንያት ነው። ሙናፊቆች እራሳቸውን ይደብቃሉ።ይህንም ለማድረግ በአማኞች ውስጥ ሚና በመጫወት በልባቸው የሌለ ቢሆንም እነሱም አማኞች ነን ይላሉ። ስለዚህ በመጀመሪያ ዕይታ በቁርአን አናቅጽ የተገለጸው በአማኞች ላይ በውስጣቸው የያዙትን ቁጣ መረዳት አስቸጋሪ ነው። ሆኖም ያለ ጥርጥር ይህ ቁጣ በበርካታ ምልክቶች ይጋለጣል።

## በልባቸው ውስጥ በአማኞች ላይ ጥላቻና ቁጣ ይሰማቸዋል

*ለናንተ ያላቸው ቁጣ በአፎቻቸው ተገለጸች። ልቦናዎቻቸው የደበቁት ደግሞ ከዚህ የከፋ ነው። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ ኣል ዒምራን፡118)*

ከቁርአን ጋር ያላቸው አያያዝና ከርሱ የሚወስዱት ተገቢ የሥነ-ምግባር እሴቶች የአማኞች ፍቅርና ክብር ወሳኙ አካል ነው። ሆኖም ይህ ለሙናፊቆች ሙሉ ለሙሉ ተቃራኒ ነው። እያንዳንዱ ከተገቢ ሥነ-ምግባር እሴቶች ጋር የተያያዘ ነገር ጥላቻቸውንና ቁጣቸውን ይጨምራል። ምክንያቱም ሃይማኖትና ሥነ-ምግባርን በተመለከተ የሚፈልጉት ዝቅጠትን ነው። ሃይማኖት እንደጥሩ ከሚቆጥረው ነገር ሁሉ በመራቅ ተቃራኒውን መሥራት ይፈልጋሉ። የአላህ (ሱ.ወ) መታወስ፣ የርሱ አናቅጽ መሰብሰብና የአማኞች ጥንካሬና ዕድገት እነሱ የሚቃወሙት ሥርዓትና ዕድገት ነው። ስለዚህ እነዚህ ሁሉ በልባቸው ውስጥ ያለውን ጥላቻ ይጨምሩታል። ይህ በልባቸው ያለው ቁጣ በበርካታ መንገዶች እራሱን ይገልፃል። የሚጠቀሟቸው በርካታ የጭቆና መንገዶች በአማኞች ላይ የሚያቅዱት፣ ዕቅድና መልዕክተኛውን ዒላማ ማድረጋቸው ጥቂቶቹ ናቸው። ሆኖም በቁርአን አንቀጾች እንደተገለጸው በልባቸው ውስጥ የያዙት ቁጣ ከሚጋለጠው ቁጣ እንደሚበልጥ አያጠራጥርም።

## ዋነኛ ዒላማቸው የአላህ መልዕክተኛ ናቸው

የጥላቻቸው ዋነኛ ምንጭ አማኞች ያለ ምንም መስፈርት አላህንና መልዕክተኛውን መታዘዛቸው፣ሁሌም አላህን ማስታወሳቸውና ቁርአንን ማንበባቸው፣ እንዲሁም ለእነሱ ምክር እጅ መስጠታቸው ነው። አማኞች ስለሞት አይቀሬነት፣ ስለቀጣዩ ዓለም እውነታና መዳን የሚገኘው አላህንና መልዕክተኛውን በመታዘዝ መሆኑን ይበልጥ በነገሯቸውና ባስጠነቀቋቸው ቁጥር ይበልጥ ጥላቻቸውና የበቀል ፍላጎታቸው ይጨምራል። በፍጹም ታዛዥ አይሆኑም፤ ምክንያቱም የአላህን መልዕክተኛ አያከብሩም፣ እንዲሁም በርሳቸው ላይ በሚያዩት የላቀ ሥነ-ምግባር ጥላቻቸው ይበልጥ ይጠነክራል።

በዚህም ምክንያት ዋነኛ ዒላማቸው የአላህ መልዕክተኛ ናቸው። እንዲሁም ትክክለኛ ትግላቸው በርሱ ላይ ነው። ሙናፊቆች ረሱልን (ሰ.ዐ.ወ) ለመዋጋት እንደሚጥሩ በቁርአን ውስጥ ተገልጿል፦

*ከተከራከሩህም አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነው በላቸው። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሐጅ፡68)*

በሁሉም የታሪክ ሂደቶች ጥረታቸው ፍሬ ቢስ ቢሆንም ሙናፊቆች እስከዛሬ በኖሩት መልዕክተኞች ላይ (ዐ.ሰ) ጦርነት አውጀው ነበር። እውነታው በሁሉም መልዕክተኞች (ዐ.ሰ) ላይ የተደረጉት ጥረቶች በሙሉ ፍሬ አልባ በመሆናቸው ሙናፊቆች ተስፋ ሲቆርጡ መልዕክተኞችና አማኞች ይበልጥ ጠንክረዋል።

## አማኞችን ማታለል ይፈልጋሉ

ሙናፊቆች የዚህ ዓይነት ሰው እንዲሆኑ ያደረጋቸው ዋነኛ መገለጫ ባህሪይ እምነት ሳይኖራቸው እራሳቸውን እምነት እንዳላቸው አድርገው መግለፃቸው ነው። እራሳቸውን ይመስላል ብለው ለሚያስቡት ሰው እውነተኛ ፊታቸውን የሚገልጹት እነዚህ ሰዎች በቀላሉ ከአማኞች ጋር በመሆን የተለያየ ሚና ይጫወታሉ። ነገር ግን ቁርአን ሙናፊቆች አማኞችን ለማታለል እንደሚፈልጉና ራሳቸውን እንጂ ማንንም እንደማያታልሉ ገልጿል።

*አላህንና እነዚያን ያመኑትን ሊያታልሉ ይሞክራሉ። ራሳቸውን እንጂ ሌላ ማንንም አያታልሉም። ግና አይገነዘቡም። (ሱረህ አል-በቀራህ፡9)*

ቁርአን በመልዕክተኞችና በነብያት (ዐ.ሰ) ጊዜ ይኖሩ የነበሩ ሙናፊቆች እውነተኛ እምነት ሳይኖራቸው "አምነናል" ማለታቸውንና አማኖች ሁሉ ከእነሱ እንዲጠነቀቁ አዟል።

*አንተ መልዕክተኛ ሆይ! በነዚያ ለክህደት በሚጣደፉት - ከነዚያ ልቦቻቸው ሳያምኑ በአፎቻቸው አምነናል ካሉትና ከአይሁዶች መካከል ሐዘን አይግባህ። ሐሰትን አዳማጮች ናቸው። ወዳንተ ፈጽሞ መጥተው የማያውቁ ሌሎች ሰዎችን ሳይቀር አዳማጮች ናቸው። ቃላትን ከቦታቸው ይለውጣሉ። "ይህን ከተሰጣችሁ ያዙት" ይላሉ። አላህ ሊፈትነው የፈለገውን ሰው አንተ ከአላህ ቅጣት አታድነውም። እነርሱ አላህ ልቦቻቸውን ሊያጸዳላቸው አልሻም። ለነርሱ በዚህች ዓለም ውርደት፣ በመጭው ዓለም ደግሞ ታላቅ ቅጣት ይጠብቃቸዋል። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ማኢዳህ፡41)*

ይህ የሙናፊቆች ባህሪይ ለክ/ዘመናት ሳይቀር ቆይቷል። በታሪክ ውስጥ እምነት አለን የሚሉ ሰዎች መኖራቸውን ቁርአን ነግሮናል። ሙናፊቆች ሁሌም ተመሳሳይ ባህሪይ ስላላቸው፣ እንዲሁም ተግባራቸው ከመልዕክተኞች (ዐ.ሰ) ተፃራሪ ስለሆነ ሥራቸውና በነርሱ ላይ የሚደርሰው አደጋ ሁሌም ተመሳሳይ ነበር። በአላህ (ሱ.ወ) ቃል ኪዳን መሠረት ወደ ተመሳሳይ መጨረሻ መምጣታቸውን ይቀጥላሉ። በአንድ የቁርአን አንቀጽ እንደሚከተለው ተገልጿል፡-

*"እነዚያን በአንተም ከአንተ በፊትም በተወረደው አምነናል" የሚሉትን ወገኖች አላየህምን? በርግጥ በርሱ እንዲክዱ የታዘዙ ሆኖ እያሉ የጣዖትን ዳኝነት ይሻሉ። ሰይጣንም ይበልጥ ሊያስታቸው ይሻል። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡60)*

## በአማኞች ጥንካሬ ይበሳጫሉ

በአማኞች ላይ የሚወስዱት እርምጃ አለመሳካቱ እንዲሁ የሙናፊቆችን ንዴት ይጨምረዋል። በተመሳሳይ መልኩ የአማኞች ከጊዜ ወደጊዜ የሚያድገው ጥንካሬም ያበሳጫቸዋል። የሚቀጥሉት አንቀጾች የሙናፊቆችን አስተሳሰብ ይገልፃሉ።

*መልካም ነገር ሲያገኛችሁ ይከፉቸዋል። ግና ከፉ ነገር ቢደርስባችሁ በእጅጉ ይደሰታሉ። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ ኣል ዒምራን፡120)*

*መልካም ነገር ሲያገኝህ ይከፉቸዋል። (ሱረህ አት-ተውባህ፡50)*

ከአማኞች ጋር እያሉ ሙናፊቆች አማኞችን ለራሳቸው ጥቅም መጠቀም ይፈልጋሉ። ነገር ግን ስሌታቸው ዋጋ ቢስ ነው። አማኞች ይበልጥ ሲጠነከሩ ተስፋ ያደረጉበትን ጥቅም ማግኘት አይችሉም። ይህ ጌታችን በዚህች ዓለም ላይ በርሱ ያመኑትን እንደሚረዳና በነርሱ ላይ በርካታ ጸጋዎችን እንደሚሰጣቸው በቁርአን የገለጸውና ቃል የገባው አላህ (ሱ.ወ) የማይቀር ሕግ ነው። ሙናፊቆችም ይህን በአግባቡ ይረዳሉ። ይሁን እንጂ በሚወስዱት ብልጣ ብልጥ እርምጃ ምክንያት በሰላምና በምቾት የተሞላው የአማኞች ሕይወት ለእነሱ የቁጣ ምክንያት ይሆናል። ሁሌም ሰላም ላይ ያሉት አማኞች የንፍቅና አመክንዮ ሊረዳው

የማይችለው ሃብት ይሰጣቸዋል፡፡ ለዚያም ነው የሚጠሉት የአማኝ ሕብረተሰብ ሁሌም ብስጭት ውስጥ እንዲሆን የሚመኙት፡፡

ለሙናፊቆች አላህ (ሱ.ወ) ለአማኞች የሚሰጠው ጸጋና እነሱ የሚኖሩበት የድሎት ሕይወት እጅግ መጥፎ የሆነው ቁጣቸው ምንጭ ሲሆን በአማኞች ላይ የሚደርሰው ማንኛውም ዓይነት ችግር ያስደስታቸዋል፡፡ የተበላሸው አስተሳሰባቸው በቁርአን ውስጥ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

*እናንተን ለመበከል ከመጣር አይቦዝኑም፡፡ የእናንተን መጎዳት ይመኛሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ ኣል ዒምራን፡118)*

አማኖች በአላህ (ሱ.ወ) ስለሚፈተኑ ከጊዜ ወደጊዜ ችግር የሚመስሉ ነገሮች ያጋጥሟቸዋል፡፡ ሆኖም እነዚህ ሁሉ ሙከራዎች ብቻ ናቸው፡፡ ችግር የትግል አቅማቸውን እንደሚያጠነክረውና ጀነትን ለማግኘት መንገድ መሆኑን ይረዳሉ፡፡ ይህን የመሰሉ ችግሮች ሙናፊቆችን ማበሳጨታቸው ለአላህ (ሱ.ወ) የመኖር ምስጢርን መረዳት ያለመቻላቸውና ይህች ዓለም የሙከራ ዓለም መሆኗን ያለመረዳታቸው ማረጋገጫ ነው፡፡ አማኞች እነዚህን ችግሮች ከጥሩ ጎን ሲመለከቷቸው ሙናፊቆች አማኞችን የማበሳጫ መንገድ፣ እንዲሁም ለራሳቸው ድል አድርገው ይወስዱታል፡፡ ተፈጥሮአቸው የአማኞችን የጥበብ ደረጃና የእምነታቸውን ጥንካሬ እንዳይረዱ ያደርጋቸዋል፡፡ አማኖች በሚያጋጥማቸው ችግር አዝነው አንድነታቸው በስተመጨረሻ ያለጥርጥር ሽባ ይሆናል ብለው ያስባሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ከፍተኛ ደስታና የወደፊት ግምት ይኖራቸዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ግምቶች ዋጋ ቢስ ናቸው፡፡

አማኞች ጥንካሬን ከማን እንደሚያገኙ ባለመረዳትና ለአላህ (ሱ.ወ) ማደራቸውን ባለማወቅ ከባድ ስህተት ውስጥ ይወድቃሉ፡፡

## አማኞችን ይፈራሉ

የአላህን ተቀባይነት ለማግኘት የአላህን ቃል እንደ ቅድመ መስፈርት የሚቆጥሩት የአማኞች ቆራጥነት ሙናፊቆችን ሁሌም ሰላም ይነሳቸዋል፡፡ የአማኞች የብርታትና የቆራጥነት ባህሪይ እምነታቸው እጅግ ኃይለኛ መሆኑንና ማንኛውም ነገር በእነሱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሌለው ይገልፃል፡፡ ይህ ሙናፊቆች እጅግ የሚጠነቀቁት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳን ጥረታቸው በጥንቃቄ የታቀደና የተወሰኑ ዓላማዎችን ለማሳካት የተወጠነ ቢሆንም ያሰቡትን ግን ውጤት አያስገኝም፡፡

በአማኞች አላህ (ሱ.ወ) ሙናፊቆች ላይ ፍርሃትን ያሳድራል፡፡ ምንም እንኳን በልባቸው ውስጥ ከፍተኛ ጥላቻ ቢኖርባቸውም ዕቅዳቸው ዋጋ ቢስ መሆኑና አማኞችን መፍራታቸው የረዳት አልባነታቸው ማረጋገጫ ነው፡፡ እነሱ በአንድ ሕብረተሰብ ላይ ወይም በአላህ (ሱ.ወ) በተጠበቀ በአንድ ግለሰብ ፊት እንኳን ደካማ መሆናቸውን ይረዳሉ፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) ላይ ምንም እምነት ስለሌላቸው አማኞች በነሱ ላይ በሚያደርጉት ትግል ይበልጥ በሚጨምረው ቀጣይነት ባለው ጥርጣሬና አለመመቸት ውስጥ ይኖራሉ፡፡ በቁርአን ውስጥ አላህ (ሱ.ወ) አማኞች በሙናፊቆች ላይ ጥብቅ ዘመቻ እንዲያካሄዱ አዟል፡-

*አንተ ነብይ ሆይ! ከሀዲያንንና መናፍቃንን ታገላቸው፡፡ ብርቱ ሁንባቸውም፡፡ መኖሪያቸው ገሀነም ናት፡፡ እጅግ አስከፊ መመለሻ! (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተሕሪም፡9)*

ይህን አላህን እንዲፈራ ሲነገረው የሚኮራው የሙናፊቅ ሕብረተሰብ በአላህ (ሱ.ወ) እርዳታ አማኞች በሚያደርጉት ትግል ፊት በፍርሃት ይዋጣል፡፡ ሌሎችን እጅግ በጣም ይፈራሉ፡፡ ምክንያቱም በቀጣዩ አንቀጽ እንደተገለጸው ጥልቅ የሆነ መረዳትን ስለማይረዱ ነው፡፡

*እናንተ ከልቦቻቸው ውስጥ ከአላህ የበለጠ ፍርሃትን ታሳድራላችሁ፡፡ ይህ የሆነው የማያውቁ ሕዝቦች በመሆናቸው ነው፡፡ (ሱረህ አል-ሐሽር፡13)*

## አላህ (ሱ.ወ) አማኞችን እንደሚጠብቅ አይረዱም

*አላህም ከሀዲያንን በአማኞች ላይ ፈጽሞ የበላይ አያደርግም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡141)*

ከላይ በተጠቀሰው የቁርአን አንቀጽ እንደወረደው እነዚህ ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ አይረዱም፡፡ እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ አላህ (ሱ.ወ) አማኞችን እንደሚጠብቅ አይረዱም፡፡ አላህን በአግባቡ የማይረዳ ሰው የዚህ ዓይነት እርዳታ ለአማኞች እንደሚሰጥ አለማወቁ ተገቢ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ምንም ውጤት እንደማይሰጣቸው ቢረዱ ኖሮ በአማኞች ላይ የሚያደርጉት ትግል ምንም ጥቅም እንደማይሰጣቸው ያውቁ ነበር፡፡ይህን አለመረዳታቸው የመረዳት ብቃት እንደሚያንሳቸው ያረጋግጣል፡፡ በዚህች ዓለም ሕይወታቸው ኃይላቸውን በሙሉ

አማኞችን ለመዋጋት ያውላሉ፡፡ሆኖም በቁርአን እንቀጾች እንደተገለጸው በዚህኛውም ሆነ በቀጣዩ ዓለም አላህ (ሱ.ወ) በፍጹም ምንም ዓይነት መሻሻልን እንዲያሳዩ አይፈቅድላቸውም፡፡ እናም አማኞችን ከሁሉም ዓይነት አደጋዎች ይጠብቃቸዋል፡፡ የአላህን አናቅጽ ቢያነቡም ይህ አለመረዳታቸው የንፍቅናቸው አንዱ ምልክት ነው፡፡ አማኞች ረዳት የለሽና ያልተጠበቁ ይመስላቸዋል፡፡ ሆኖም እውነታው በሁሉም ሁኔታዎች አማኞች ከሀዲያንን ድል ይመታሉ፡፡ አማኖች በአላህ (ሱ.ወ) እንደምርጥ ፍጥረት ይታያሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የላቁ ባህሪያት አሏቸው፡፡ሙናፊቆች ይህን መረዳት አለ-መቻላቸው ባዶና ፍሬ ቢስ ጥረታቸውን ይበልጥ ያብሰዋል፡፡ እናም ይደናገራሉ፡፡

## የራሳቸው ጥቅም ከተነካ አማኞችን ይተዋሉ

ከዚህ በፊት እንደተገለጸው ሙናፊቆች ከአማኞች ጋር ለመሆን የሚፈልጉበት ዋነኛ ምክንያት ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ነው፡፡ በችግር ወይም በመከራ ጊዜ ምቾታቸውን የሚያበላሽ አልያም በጥማቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያለው ነገር ሲያጋጥማቸው በቅጽበት ፊታቸውን በማዞር አማኞችን ይተዋቸዋል፡፡ እነዚያ ጊዜያት የችግርና የመከራ ጊዜያት ናቸው፡፡ ሕይወታቸውን በሙሉ የሚኖሩት የአላህን ተቀባይነት ለማግኘት ስላልሆነ በችግር ጊዜ በሃይማኖት የሥነ-ምግባር እሴቶች ስለመኖር አይረዱም፡፡ ሙናፊቆች ችግር ሲፈጠር አማኞችን የተውበት አንዱ ምሳሌ የነብዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) ጎሳ ነው፡፡

ለጦርነት በተንቀሳቀሱበት ዕለት እውነተኛ ተፈጥሮአቸው ተገለጸ፡፡ ከጦርነቱ አመለጡ/ሸሹ፡፡ እንዲሁም በአላህ መልዕክተኛ ላይ ክብር የለሽ ባህሪን አሳዩ፡፡

> *ሙሳ ሆይ! እነርሱ ከውስጧ እስካሉ ድረስ ፈጽሞ አንገባትም፡፡ አንተና ጌታህ ሂዱና ተዋጉ፡፡ እኛ ከዚህ እንቀመጣለን አሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ማኢዳህ፡24)*

በበርካታ ሰበቦች ምክንያት እነዚህ በአላህ (ሱ.ወ) የማያምኑትና አንቀጹን የሚክዱት ከአማኞች ጋር መኖራቸው በጣም ይደንቃል፡፡ ለእነዚህ ሰዎች ከፍተኛ ዋጋ ያለው ነገር የራሳቸው ጥቅም ነው፡፡ የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ከአማኝ ሕብረተሰብ ጋር ለተወሰነ ጊዜ መቆየት ይችላሉ፡፡ ይህን ለግል ጥቅም ሲባል የሚደረግ አብሮነትን ጥቅማቸው እስኪነካ ድረስ ተግባራዊ ያደርጉታል፡፡

ነገር ግን ጥቅማቸው መነካቱን ሲረዱ የመሄጃ ጊዜያቸው ነው፡፡ በችግር ጊዜያት የአላህን ተቀባይነት ለማግኘት በሚደረግ ትግል ውስጥ ባለመሳተፍ ለአላህ (ሱ.ወ) ውዴታ እንዳልኖሩና እንዳላደሩ ይገልፃሉ፡፡ ጥቅማቸው ለተነካ ለነዚህ ሰዎች ከአማኞች ጋር የመቆያ ሌላ ምክንያት የላቸውም፡፡ ሙናፊቆች ከአማኞች

ለማግኘት የሚፈልጓቸውን ጥቅሞች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በቀጣዮቹ ምዕራፎች እንመለከተዋለን፡፡

## በአላህ (ሱ.ወ) ላይና በአማኞች ላይ የሚያደርጉት ትግል

## ሰዎችን ከቀጥተኛው ጎዳና ለማስወጣት ይፈልጋሉ

አላህ (ሱ.ወ) በአማኞች ላይ ግዴታ ካደረጋቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ በጥሩ ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል፣ እንዲሁም የቁርአንን የሥነ-ምግባር እሴቶች ለዓለም እንዲያውጁ ነው፡፡ ሰዎች የዘነጓቸውን ወሳኝ ነገሮች በማንሳት ሰዎችን በማስጠንቀቅ በቀጣዩ ዓለም ዘላለማዊ ሕይወታቸው መድህን እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ ኃላፊነታቸው ትልቅ ሲሆን የሚሠራው ሥራም ሰፊ ነው፡፡ ለአንድ አማኝ አንድ ሰው እምነት እንዲኖረው ማድረግ የአላህን ተቀባይነት ለማግኘት እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

ሆኖም የሙናፊቆች ባህሪይ መሆን ከሚገባው ሙሉ ለሙሉ ተቃራኒ ነው፡፡ ሰዎችን ወደ አላህ (ሱ.ወ) ከመጥራት ይልቅ በሰይጣን ተምሳሌት እንዲሠሩ በማሳየት ሰዎችን ከአላህ (ሱ.ወ) መንገድ ያርቃሉ፡፡ የሙናፊቆች ዋነኛ ዓላማ ሰዎች እምነት እንዲያገኙ ምክንያት ከመሆን ይልቅ ልክ እንደሰይጣን ሰዎችን ከአላህ (ሱ.ወ) መንገድ ማስወጣትና ሌሎችን ወደሙናፊቆች ደረጃ መሳብ ነው፡፡

> *ከሰዎች መካከል ስለአላህ ያለ ዕውቀት፣ ያለቅን መመሪያና ያለተንታኝ መጽሐፍ የሚከራከር አለ፡፡ ጎኑን ያጠፈ ሆኖ፡፡ ሰዎች የአላህን መንገድ እንዲስቱ ለማድረግ፡፡ ይህ የዚህች ዓለም ውርደት ይጠብቀዋል፡፡ በመጭውም ዓለም አቃጣይ ቅጣትን እናቀምሰዋለን፡፡ (ሱረህ አል-ሐጅ፡8-9)*

ሙናፊቆች በርካታ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ ይህንም በሚያደርጉበት ጊዜ ዋነኛ ባህሪያቸው ብልጠት ነው፡፡ በመሃከላቸው ሲሆኑ ሁለት ፊት አቀራረብን በመቅረብ አማኞችን ለማደናቀፍ ይሞክራሉ፡፡ ይህ ያለ ጥርጥር በቀጣዩ ዓለም "የበታች ሁሉ በታች" የሚሆኑበት ዋነኛ ምክንያት ነው፡፡

## የአማኞችን ወሬ ለከሀዲያን ያቀብላሉ

*በናንተም ውስጥ ለነሱ አዳማጮች አሏቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ)*

የሙናፊቆች ዋነኛ ዓላማ የአማኞች ህብረተሰብ ወድቆ መመልከት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ኃይለኛ ናቸው ብለው ከሚገምቷቸው ከሀዲያን ጋር አንድ ይሆናሉ፡፡ እናም በአማኞች ላይ የብልጠት ትግል ያውጃሉ፡፡ የተባበረ የአማኝ

ህብረተሰብ ለእነሱ ከፍተኛ አደጋ ነው፡፡ ስለዚህ ከሁሉም በፊት ይህን አንድነት ለማስወገድ ይፈልጋሉ፡፡ የተቻለውን ሁሉ ጉዳት ለማድረስ ያልማሉ ወይም ይጥራሉ፡፡ በአማኞች መሃል በመቆየት በነሱ ላይ ምስጢራዊ ትግልን ማድረግ ይቻላል ብለው በማሰብና መረጃና ዜና መውሰድ ይቻላል ብለው በማሰብ በአማኝ ህብረተሰብ ውስጥ መኖራቸውን እንደጠቃሚ ይቆጥራሉ፡፡ ሆኖም እያንዳንዱ የሚወስዱት እርምጃ ምንም ግብ ሳይመታ ወደራሳቸው እንደችግር ይመለሳል፡፡

ከአማኞች ጋር ሆነው ከከሀዲያን ጋር ትብብር የሚጀምሩት የነዚህ ሰዎች ዓላማ የአማኞችን ዘዴ ተምሮ ለከሀዲያን ማስተላለፍ ነው፡፡ እዚህ ነጥብ ላይ አንድ ሁኔታ ስሌት ውስጥ ይገባል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ከአማኞች በተቃራኒ የሚመሠረትን ማንኛውም ነገር በፍጹም አይፈቅድም፡፡ በታሪክ ውስጥ በሙናፊቆች የታቀዱ ሁሉም ወጥመዶች ውድቅ ሆነዋል፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) ቃል ኪዳን መሠረት ይህ ወደፊት ይቀጥላል፡፡ እናም እያንዳንዱ የሚሠሩት ነገር ውድቅ ይሆናል፡፡

## በምስጢር ያንሾካሽካሉ

ሙናፊቆች በአማኞች መሃል እያሉ ኃጢአትን፣ ጥላቻንና አመጽን ለማበረታታት በምስጢር ይነጋገራሉ፡፡

*የነዚያ ምስጢራዊ ንግግር እንዳያደርጉ የተከለከሉት፣ ወደተከለከሉት የሚመለሱትና በኃጢአት፣ በጥላቻ፣ መልዕክተኛውንም በመቃረን ምስጢራዊ ውይይት የሚያደርጉት ሁኔታ አያስገርምህምን? (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙጃደላህ፡8)*

በአማኝ ህብረተሰብ ውስጥ እያሉ እርስ በርሳቸው ምስጢራዊ ህብረት ይፈጥራሉ፡፡ እናም በአማኞች ላይ ዕቅድ ያወጣሉ፡፡ የዚህ አንዱ ምሳሌ በረሱል (ሶ.ዐ.ወ) ጊዜ ታይቷል፡፡

*እነዚያም ምእምናንን ለመጉዳት፣ ክህደትንም ለማበረታታት፣ በምእመናንም መካከል ለመለያየት ካሁን ፊት አላህንና መልዕክተኛውንም የተዋጋውን ሰው ለመጠባበቅ መስጊድን የሠሩት፣ መልካምን ሥራ እንጂ ሌላ አልሻንም ሲሉም በርግጥ ይምላሉ፡፡ አላህም እነሱ በርግጥ ውሸታሞች መሆናቸውን ይመሰክራል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡107)*

የዚያ ጊዜ ሙናፊቆች ከረሱል (ሶ.ዐ.ወ) እና ከሶሓቦች (ረ.ዐ) በመራቅ እነሱ ይሠሩት የነበረውን ለመማርና ለነርሱ ወጥመድ ለማዘጋጀት ከአማኞች የተለየን ቦታ በምስጢር ይዘው ነበር፡፡ ቁርአን ይህን የሙናፊቆች ባህሪይ ይገልፃል፡፡ ይህን የሚሠሩት ሙናፊቆች አንድ ነገርን ከአማኞች በመደበቅና

ምስጢራዊ ዕቅድን በማቀድ ውጤታማ የሚሆኑ ይመስላቸዋል፡፡ ሆኖም እውነታው በቀጣዩ አንቀጽ እንደተገለጸው አላህ (ሱ.ወ) የሚሠሩትን በሙሉ ያያል፡፡

*አላህ ድብቅ ምስጢራዊ ውይይታቸውንም የሚያውቅና ሩቅ ምስጢሮችንም ዐዋቂ መሆኑን አላወቁምን? (ሱረህ አት-ተውባህ፡78)*

ይህ ባህሪይ የመነጨው ይህን ጠቃሚ ምስጢር መረዳት ካለመቻላቸው ነው፡፡ በአማኞች ላይ እምነት የለሽ አቀራረብ ከመቅረባችም በላይ በአላህ መልዕክተኛ ላይ አመጽን ያንሾካሽካሉ፡፡ ሆኖም በቀጣዩ ዓለም የሠሩት ሥራ በሙሉ ሲቀርብላቸው የሠሩት ሁሉ ምስጢር እንዳልነበረ ይረዳሉ፡፡ እንዲሁም የአማኞች ረዳት አላህ (ሱ.ወ) በእነሱ ላይ የተዘጋጀውን ዕቅድ ያውቃል፡፡ ሙናፊቆች ከሌሎች ሰዎች የሚደብቁትን ይህን ባህሪያቸውን አላህ (ሱ.ወ) ያጋልጥናል ብለው አያስቡም፤ ምክንያቱም በድጋሚ እነሱ የሚፈሩት የሰው ልጆችን ነው፡፡

ሆኖም እውነታው የሠሩትን ሥራ ሁሉ በቀጣዩ ዓለም ይጠየቁበታል፡፡ እንደ ምስጢር የቆጠሩዋቸውና በፍጹም አይጋለጡም ብለው ያሰቧቸው ተግባሮቻቸው አንዳንድ በአንድ ይቀርቡላቸዋል፡፡

## መጥፎን ያቀናጃሉ

አማኞች ሕይወታቸውን ሃይማኖታዊ ተግባራትን ለአላህ (ሱ.ወ) በመሥራትና በርሱ መንገድ ላይ ከፍተኛ ጥረትን በማድረግ ያሳልፋሉ፡፡ በዚህ ዓላማ ነጸብራቅ እያንዳንዱን የሕይወታቸውን ቅጽበት መልካምን በመፈለግ ያሳልፋሉ፡፡ ይህ የሆነው የሚሞቱትን ጊዜ ባለማወቃቸው ነው፡፡ ሆኖም ልክ እንደሌሎች ጉዳዮች በዚህ ጉዳይ ላይም ሙናፊቆች ሙሉ ለሙሉ ከአማኞች ተቃራኒ የሆነን ባህሪን ያሳያሉ፡፡ በእያንዳንዷ የሕይወታቸው ቅጽበት ኃጢአትን ይፈልጋሉ፡፡ አማኞችን ሆን ብለው ለመጉዳት በማሴር ወይም ለአማኞች ወጥመድ በማዘጋጀት አማኞችን መጉዳት ይፈልጋሉ፡፡ ሁሉም ጥረታቸው አማኞች ላይ ነው፡፡ የጥረታቸው ዋነኛ ምክንያት በአማኞችና በአላህ (ሱ.ወ) አናቅጽ ላይ ያላቸው ቅሬታ ነው፡፡ በቁርአን እንደተገለጸው እያንዳንዱ የሚሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ጥላቻቸውን በመጨመር የበቀል ፍላጎታቸውን ያነሳሳዋል፡፡

*አስጠንቃቂ ቢመጣላቸው ከየትኛውም ሕዝብ ይበልጥ የተቀኑ እንደሚሆኑ በአላህ በመማል ተናገሩ፡፡ ግና አስጠንቃቂ በመጣላቸው ጊዜ ሽሽትን እንጂ አልጨመረላቸውም፡፡ ምድር ላይ ኩራትንና መሠሪነትን ጨመሩ፡፡ መሠሪነትም ራሳቸውን እንጂ ሌላ ማንንም አይጎዳም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ፋጢር፡42-43)*

ይህ የሚሰማቸው ጥላቻ በርካታ ነገሮችን እንዲሠሩ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ መልዕክተኞች (ዐ.ሰ) የሚመጡት መልካምነትንና ጥሩነትን፣ እንዲሁም የአላህ (ሱ.ወ) አናቅጽን እንዲያነቡ ሊያስታውሷቸው ስለሆነ ቁጣቸው በመጨመር የብልጠት ተግባራትን እንዲፈጽሙ ይመራቸዋል፡፡

በዚህም ምክንያት በአማኞች ላይ መጥፎ ነገርን ማቀድና ማደራጀት ይጀምራሉ፡፡ የአማኞችን እንቅስቃሴ ለማደናቀፍና በመካከላቸው አለመስማማትን ለመፍጠር ያቅዳሉ፡፡ ለአማኞች የተሰጧቸውን ትዕዛዛት ለመጠምዘዝ፣ እንዲሁም መልዕክተኛው ላይ ማመጽን ተገቢ እንደሆነ ለማሳየት ይፈልጋሉ፡፡ መልዕክተኛው የከለከሏቸውን ተግባራት በመፈጸም ያምፃሉ፡፡ እንዲሁም ድጋፍ ማከማቸት ይፈልጋሉ፡፡ የሚሠሩት ሥራ ሁሉ ዓላማው የተስተካከለውን ማበላሸትና የአማኝ ህብረተሰብን ማዳከም ነው፡፡

ቁርአን እንደሚያስተምረን እነዚህ ጥረቶች ሁሉ ምንም ዓይነት ውጤት አይኖራቸውም፡፡ በሁሉም የታሪክ ዘመናት በአላህ (ሱ.ወ) ሥርዓት ላያ ያሴሩ ሁሉ ድል ተመተዋል፡፡ ማንኛውም አላህን በአግባቡ መረዳት የማይችል ይህን ታላቅ እውነታ ስለማይረዳ በነዚህ ጥረቶቹ ይቀጥላል፡፡ ሆኖም እውነታው በቁርአን እንደተገለጸው እያንዳንዱ ሴራ ያሴረውን እንጂ ማንንም አይጎዳም፡፡

## አማኞች ላይ ያላግጣሉ

ሌላኛው የሚሠሩት ሥራ ላግጣ ነው፡፡ በአማኖች ጥንካሬ ምክንያት ሙናፊቆች የሚሣቀዩበት ሁኔታ የበታችነታቸውና ጭንቀታቸው በማላገጥ ግልጽ ይሆናል፡፡ ገደብ በሌለው ቁጣቸው ምክንያት የአማኞችን በጎ አስተሳሰብ በመጠቀም በሌሎች ክብር በማንኳሰስ ሊንቋቸው ይፈልጋሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይህን በራሳቸው ቃላት ያሳውቀናል፡፡

*ወደ ሰይጣኖቻቸው ባገለሉ ጊዜ "እኛ ከናንተ ጋር ነን፡፡ እየተሳለቅን ነበር" ይላሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡14)*

ሆኖም እውነታው በአማኞች ላይ ምንም ጉዳት ማድረስ አይችሉም – በላግጣቸውም ሆነ በሌሎች የጭቆና ዘዴያቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ሁሉንም ባህሪያቸውን ያየዋል፣ እንዲሁም ይረዳዋል፡፡ በቁርአን ሙናፊቆች እራሳቸው የሚላገጥባቸውና የሚናቁ መሆናቸ-ውን ይገልፃል፡፡

*አላህ በነርሱ ይሳለቅባቸዋል፡፡ በጥመታቸው እንዲደናበሩ ዕድሉን ይሰጣቸዋልም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡15)*

ሙናፊቆች አማኞችን ስለሚመቅኙ ሁሉም ባህሪያቸው ይህን ጥላቻ ላለማውጣት ያለመ ነው፡፡ ከአማኞች የተወሰኑ ጥቅሞችን ስለሚፈልጉ ጥላቻቸው ግልጽ እንዳይሆን ከባድ ሕመምን ይቀበላሉ፡፡ ሆኖም በውስጠ ሕሊናቸው ይህ ጥላቻ እውነተኛ ፊቱን ያሳያል፡፡ ማላገጥ ሙናፊቆች በልባቸው የሚሰማቸው፣ እንዲሁም በንግግራቸው፣ በዕይታቸውና በፊት ገጽታቸው የሚጋለጠው የቁጣና የጥላቻ ምስጢራዊ ምልክት ነው፡፡

የቁርአን አንቀጾች አማኞች እምነት ስላላቸው ብቻ ሙናፊቆች የሚያሳዩዋቸውን ባህሪያት በግልጽ አስቀምጠዋል፡፡ እራሳቸውን የበላይ አድርገው ስለሚቆጥሩና ከቀጣዩ ዓለም የራቁ አድርገው ስለሚቆጥሩ ለቀጣዩ ዓለም ብለው ሌሎች የሚሠሩት ሥራ ምንም ጥቅም የለውም ብለው ያስባሉ፡፡ ስለዚህ ለቀጣዩ ዓለም የተሰጠ ሕይወት ላይ ሊያላግጡ ይችላሉ፡፡

*እነዚያ ያመጹት በነዚያ ባመኑት ላይ በርግጥ ይስቁ ነበር፡፡ በነሱም ላይ ባለፉ ጊዜ ይጠቃቀሱ ነበር፡፡ (ሱረህ አል-ሙጠፍ-ፊፊን፡29-30)*

አላህ (ሱ.ወ) የዚህ ዓይነት ባህሪይ በቀጣዩ ዓለም ምን እንደሚያጋጥመውም ገልጿል፡፡

*ዛሬ (በፍርዱ ቀን) እነዚያ ያመኑት በከሀዲዎቹ ይስቃሉ፡፡ (ሱረህ አል-ሙጠፍ-ፊፊን፡34)*

ሙናፊቆች በሰይጣን ብልጣ ብልጥ ጉብዝና ስለሚመሩ በሙእሚኖች ላይ ይህን ጸባያቸውን በግልጽ አያሳዩም፡፡ ይህን ለመደበቅ እጅግ ጠንቃቃ ናቸው፡፡ ሆኖም የኋላ ኋላ ተንኮላቸው ሲገለጽና አላጋጭነታቸው ፊታቸው ላይ ሲታይ ንፍቅናዊ አመክንዮአቸው እራሱን ይገልፃል፡፡ ታማኝነታቸውን ለማረጋገጥ የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ፡፡

*ብትጠይቃቸው "እየተጫወትንና እየቀለድን ነው" ይሉሀል፡፡ በላቸው፡- በአላህ፣በአንቀጾቹና በመልዕክተኛው ታፌዙላችሁን? (ሱረህ አት-ተውባህ፡65)*

## የአማኞችን ስም ያጠፋሉ

*በአላህ ላይ ከቀጠፈ ወይም አንቀጾቹን ካስተባበለ ይበልጥ በዳይ ማን ነው? እነሆ! በዳዮች መዳንን አይጎናጸፉም፡፡ (ሱረህ አል-አንዓም፡21)*

መልዕክተኛውንና ሙእሚኖችን ማዳከም ስለሚፈልጉና የሃይማኖት የሥነ-ምግባር እሴቶች እንዳይስፋፉ መከልከል ስለሚፈልጉ መልዕክተኛው ላይ እንደሚያደርጉት ሁሉ በአማኞች ላይ መሠረት የለሽ ክሶችን ይመሰርታሉ፡፡

ሙናፊቆች አማኞችን ከሚያጠቁበት ዋነኛ መንገዶች አንዱ የነሱን ስም ማጥፋት ነው፡፡

በዚህም መንገድ እራሳቸውን ከአማኞች የተለየ አድርገው ማቅረብ እንደሚችሉና እውነት እነሱ ጋር እንዳለ ማሳየት የሚችሉ ይመስላቸዋል፡፡ በዚህ አስተሳሰባቸው እራሳቸውን ነፃ በማድረግ አማኞችን በሌሎች ዓይን ክብር እንዲያጡ ያደርጋሉ፡፡ ሆኖም እውነታው ስም ማጥፋታቸው አማኞችን አይጎዳቸውም፡፡ እንደውም ከዚህ በተቃራኒ ስም ማጥፋቱን የፈጸሙ ሰዎችን ይጎዳል፡፡

*ሰዎችን ያለ ዕውቀት ቅኑን መንገድ ለማሳት በአላህ ላይ ከቀጠፈ ይበልጥ በዳይ ማን ነው? አላህ በዳዮችን አያቀናም በላቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አንዓም፡144)*

የነዚህ ሀሜቶች ወሳኝ መገለጫ በአጠቃላይ በመልዕክተኛው ላይ የታለሙ መሆናቸው ነው፡፡ ከዚህ በፊት በቁርአን ውስጥ የተጠቀሱ ተመሳሳይ ዘዴዎችን የተጠቀሙ በርካታ ክሶች በታሪክ ውስጥ ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በቁርአን ውስጥ ስማቸው የተጠቀሰውና ሁሌም ሲኖሩ የነበሩት ከሀዲያን ወደ እነሱ የተላኩ መልእክተኞችን እብድና ጠንቋይ ብለው ከሰዋል፡፡ ምንም እንኳን በርካታ ክፍለ ዘመናት ቢያልፉም ተግባሮቻቸው ሳይቀየሩ ቆይተዋል፡፡ ክሶቻቸው ሁሌም በተመሳሳይ መንገድ ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ ግና ማንኛውም ዓላማቸው ግቡን አልመታም፡፡

## ክፍፍል በመፍጠር አማኞችን መጉዳት ይፈልጋሉ

*ከሀዲያን እስረኛ ሊያደርጉህ፣ ሊገድሉህ ወይም ሊያስወጡህ ባሴሩ ጊዜ፡፡ እነርሱ ያሴራሉ፡፡ አላህም ያቅዳል፡፡ የአላህ ዕቅድ ምንጊዜም ተፈፃሚ ነው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አንፋል፡30)*

አማኞች ላይ ውስጠ ሕሊናዊ ጥላቻን በመያዝ ሙናፊቆች አማኞችን ለመጉዳት፣ በመካከላቸው ሁከትና ክፍፍልን መፍጠር ይፈልጋሉ፡፡

ከዚህ በፊት እንደተገለጸው የአማኞችን ህብረተሰብ ከፋፍሎ በማዳከም አማኞች በሃይማኖት የሥነ-ምግባር እሴቶች እንዳይኖሩ ማድረግ ይቻላል ብለው ስለሚያስቡ ዋነኛ ዓላማቸው አማኞችን መከፋፈል ነው፡፡ በርግጥም አማኞች በመካከላቸው ያለ አንድነት ከፍተኛ ድጋፍና ጥንካሬ ይሰጣቸዋል፡፡ ነገር ግን እውነተኛ ጥንካሬያቸውን የሚያገኙት ከአላህ (ሱ.ወ) ነው፡፡ እርስ በርስ ባላቸው አንድነት አማኞች በርካታ በእነሱ ላይ ያሉ ኃላፊነቶችን ይወጣሉ፡፡ አላህን ያስታውሳሉ፡፡ እንዲሁም በከሀዲያን ላይ የጋራ ትግል ያደርጋሉ፡፡ አማኞች እውነተኛ

ጥንካሬያቸውን ከአላህ (ሱ.ወ) እንደሚያገኙ መረዳት የሚያዳግተው የንፍቅና አስተሳሰብ ክፍፍል በመፍጠር ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ ይመስለዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የእነሱ አተያያቸው ውጤት ብቅ ይላል፡፡ እጅግ ጠቃሚ ነው ብለው በሚያስቡት ጥረት ላይ ከፍተኛ ኃይልን ያባክናሉ፡፡ ሆኖም ጥረታቸው ሁሉ ፍሬ አልባና ባዶ ነው፡፡ በነሱ አተያይ ይህ ጥንካሬና አንድነት ያለውን ህብረተሰብ ለማዳካም እጅግ ውጤታማው መንገድ ነው፡፡ በመካከላቸው ስንጥቅን ከፈጠሩ በኋላ በአማኞች ላይ ሁከትን ለማስነሳት ጥረታቸውን ይቀጥላሉ፡፡

ከዚህ በፊት እንደታየው በአማኞች መካከል ብጥብጥን ለመፍጠር የብልጠት ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ "ከእናንተ ለመለየት ስንጥቅን እንፈጥራለን" በማለት በፍጹም ስንጥቅን አይፈጥሩም፡፡ ከዚህ በተቃራኒ በምድር ላይ እውነትን ማሰራጨት የሚሹ ታማኝ ሰዎች እንደሆኑ ያሳያሉ፡፡ በዚህ የብልጠት ባህሪይ ታማኝነትን ለማሳየት ይፈልጋሉ፡፡ እንዲሁም ግልጽ ሳያደርጉ ሁከትን ይፈጥራሉ፡፡ ይህን እንደ ትልቅ ዕድል ይቆጥሩታል፡፡ ሆኖም እንደሁል ጊዜው ጥረታቸው ሁሉ ዋጋ ቢስ ነው፡፡

*ማስከፋትን እንጂ ፈጽሞ አይጎዷችሁም፡፡ (ሱረህ ኣል ዒምራን፡111)*

## በቀጣዩ ዓለም ላይ ያላቸው እምነትና ይህችን ዓለም መምረጣቸው

ለአንድ አማኝ የጥረቱ ሁሉ ግብ ቀጣዩ ዓለም ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ዓለም ላይ የሚደረግ እያንዳንዱ ዝግጅት የቀጣዩ ዓለም ሕይወትን በጥሩ አኳኋን ማግኘት ነው፡፡ በቀጣዩ ዓለም ጉዳይ ላይ የተረጋገጠ እምነትና የተወሰነ ዕውቀት ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰዎች በእነሱ እምነት ምናባዊ ነው ብለው ያሰቡትንና ሙሉ ለሙሉ ያላመኑበትን ነገር መኖር ችላ ይላሉ፡፡ በማንኛውም መልኩ የጥቂት አማኞች መኖርና የሙናፊቆች መኖር የዚህ አስተሳሰብ ውጤት ነው፡፡ የሚጠብቃቸው የተረጋገጠና የተወሰነ እውነታ ቢሆንም በርካታ ሰዎች ቀጣይነት ባለው ጥርጣሬ ውስጥ ይኖራሉ፡፡

እንዲሁም በቁርአን አንቀጾች ጥልቅ ገለፃው ቢኖርም ከዚህም በተጨማሪ እነሱ እራሳቸው የሚያዩዋቸው ቁጥር ስፍር የሌላቸው ማረጋገጫዎች ቢኖሩም ይጠራጠራሉ፡፡ የጥርጣሬያቸው ምክንያት በምድራዊ ምኞቶቻቸው ምክንያት በቁርአን ውስጥ የነበቧቸውን የቀጣዩን ዓለም እውነታዎች ለማስተንተን ቸልተኛ መሆናቸው ነው፡፡ ማንኛውም በቀጣዩ ዓለም ያለጥርጥር ያመነ ሰው ይህች ዓለም ከቀጣዩ ዓለም ጋር ስትወዳደር ምንም ዋጋ እንደሌላት ይረዳል፡፡ እንዲሁም ለዚህች ዓለም አታላይ ጌጦች ጀርባውን ይሰጣል፡፡ በሌላ በኩል ለሙናፊቆች ይህች ዓለም የእነሱ

ዋነኛ ዓላማ ናት፡፡ በዚህም ምክንያት በቀጣዩ ዓለም ላይ እራሳቸውን ያውራሉ፡፡ ገጽታቸው በቁርአን አናቅጽ በቀጣዮቹ ቃላት ተገልጿል፡፡

*በእውነቱ ስለወዲያኛው ዓለም ኢምነት ዕውቀት የላቸውም፡፡ እንዲያም መከሰቷን ይጠራጠራሉ፡፡ እነርሱ በዚህ ረገድ እውሮች ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ነምል፡66)*

ቀጣዩን ዓለም እንዲጠራጠሩ ያደረጋቸው ዋነኛ ምክንያት የእምነታቸው ድክመትና ዓለማዊ ፍላጎቶቻቸው ናቸው፡፡ በአንድ የቁርአን አንቀጽ እንደተገለጸው ስለቀጣዩ ዓለም ለማሰብ ፈቃደኛ ስላልሆኑ የማይቀር መሆኑን መረዳት አይችሉም፡፡

*ተጠያቂ እንደሚሆኑ ቅንጣት አይጠብቁም ነበር፡፡ (አን-ነበእ፡27)*

ለሠሩት ሥራ ለመጠየቅ መቅረብ በፍጹም የማይጠብቁት ነገር ነው፡፡ ፍላጎታቸውን የተቆጣጠረው ንፍቅና በዚህ እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ላይ እራሱን ይገልፃል፡፡ የዚህ ዋነኛ ምክንያት የቀጣዩን ዓለም መገኘት አለመረዳታቸው ነው፡፡ የቂያማ ቀንን፣ ቀጣዩ ዓለምንና ሞትን በአዕምሮአቸው ውስጥ ማሰብ አይፈልጉም፡፡ እነዚህን ታላላቅ እውነታዎች ባለማሰባቸው በዚህች ዓለም አታላይ ተፈጥሮ እያወቁ ተሸውደዋል፡፡ ባለማሰብ የተጠቀሙ ይመስላቸዋል፡፡ እራሳቸውን ከዚህ ጥቅም ያገኙ ስለሚመስላቸው ዘላለማዊውን ጀነት እያጡ ናቸው፡፡

## ለዚህች ዓለም ሕይወት ከልብ የተሰጡ ናቸው

*ይህች ዓለም ቀልድና ጨዋታ እንጂ ሌላ አይደለችም፡፡ ሕይወት የመጪው ዓለም ሕይወት ነው፡፡ ዐዋቂዎች ቢሆኑ ኖሮ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ዐንከቡት፡64)*

አላህ (ሱ.ወ) ለሰው ልጆች በቁርአን ውስጥ እንዳወረደው ይህች ዓለም እንደ ጊዜያዊ ማረፊያ ተፈጥራለች፡፡ እውነተኛ ቤታችን እውነተኛ ሕይወታችንን የምንኖርበት ቀጣዩ ዓለም ነው፡፡ ከዚህም በላይ ይህ እውነተኛ ሕይወት እንዲሁ በ60 እና በ70 ዓመታት የተገደበ አይደለም፡፡ ሰዎች እዚያ ለዘላለም ይኖራሉ፡፡ ይህ እያንዳንዱ ሰው ሊያስበው የሚገባው ታላቅ እውነታ ነው፡፡ በዚህች ዓለም ሰዎች ከሞት በኋላ ለሚሄዱበት እውነተኛ ቤት መዘጋጀት አለባቸው፡፡ ሆኖም በርካታ ሰዎች ይህን አይረዱም፡፡ በግልጽ ለማስቀመጥ ስለሱ ለማሰብ ፍላጎት የላቸውም፡፡ ሕይወታቸውን በዚህች ዓለም ላይ መኖር በመፈለግ ይህን የሚጎዳ ማንኛውንም ሐሳብ ማስወገድ ይፈልጋሉ፡፡

የቀጣዩ ዓለም መኖር በዓለማዊ ጉዳያቸው ላይ ያላቸው ጉጉት ላይ ከባድ እንቅፋት ይሆናል፡፡ ስለዚህ ይህን መቀበል ስለማይፈልጉ የቀጣዩን ዓለም ሐሳብ

ከእራሳቸው በቻሉት ያህል ማራቅ ይፈልጋሉ፡፡ በዚህ መልኩ መሥራት ያለባቸውን ነገር ይዘነጉታል፡፡

ለዚህች ዓለም እጅግ ከፍተኛ በሆነ ሁኔታ እጅ የመስጠታቸው ምክንያት ሞትን ያለማሰባቸው ነው፡፡ ስለዚህ የሞት ርዕስ ሲነሳ በቅጽበት ርዕሱን ለመቀየር ይሞክራሉ፡፡ ምክንያቱም ሞት የያዙትን ሁሉ ይወስደዋል – ገንዛቸውን፣ ሰውነታቸውን፣ ዕቃዎቻቸውን፣ ውበታቸውን፣ ደረጃቸውንና ያለቡትን፡፡

ሆኖም እውነታው ምንም ያህል ለማስወገድ ቢፈልጉም ሞት ታላቅ እውነታ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው አላህ (ሱ.ወ) ስለፈለገው ነው የተፈጠረው፡፡ እናም በአላህ (ሱ.ወ) የተወሰነለትን ውሳኔ ይኖራል፡፡ ከዚያም የተመደበለት ጊዜ ሲያልቅ ከተወሰነለት ቀደር ጋር ይሞታል፡፡ እያንዳንዱ የሚያስብ የሰው ልጅ ይህን በከፍት አዕምሮ መመልከት አለበት፡፡ በመሆኑም ከርሱ የሚጠበቀውን ኃላፊነት መወጣት አለበት፡፡ ይህ ኃላፊነት ለአጭሩና አላፊ ለሆነችው የዚህች ዓለም ኑሮ እራስን አለመስጠትና አላህ (ሱ.ወ) ባስቀመጠው ገደብ መሠረት መኖርን ያጠቃልላል፡፡

ነገር ግን ለሙናፊቆች የደረቀ ልብ የሰው ልጆችን ለመፈተን ሲባል የዚህች ዓለም ሕይወት በበርካታ ርካሽ ጌጦች የተዋበ በመሆኑ ሕይወት ብርሃናማና አስደሳች ትመስላቸዋለች፡፡ በዚህ ከሀዲያንም ይታለላሉ፡፡ ሆኖም እምነት ያላቸው ሰዎች እነዚህ መጌጫዎች አታላይ መሆናቸውን ይረዳሉ፡፡ እናም የዚህች ዓለም ሕይወት በዓይን እርግብግቢት እንደሚያልቅና እንደሚጠፋ ይረዳሉ፡፡ ሙናፊቆች ይህን እውነታ አይቀበሉትም፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳን የቀጣዩን ዓለም እውነታ በአግባቡ ቢያውቁትም ችላ ብለውት ለዚህች ዓለም ሕይወት ብቻ ራሳቸውን ይሰጣሉ፡፡

እነዚህ ሰዎች ቁርአንን ይማራሉ፣ የነገሮችን እውነተኛ ተፈጥሮ ይረዳሉ፡፡ እንዲሁም ከዚህች ዓለም ተፈጥሮ ጋር ይስማማሉ፡፡ ሆኖም በፍጹም አይተዋትም፡፡ ምክንያቱ በአንድ አንቀጽ እንደተገለጸው የዚህችን ጠፊ ዓለም ሕይወት መርጠዋልና፡፡

*. . . የዚህችን ዓለም ሕይወት ከመጭው ዓለም የመረጡ፤ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ኢብራሂም፡3)*

ሙናፊቆችን የዚህች ዓለም ፍቅር አፍዟቸዋል፡፡ እውነትን እንዳይቀበሉ አድርጓቸዋል፡፡ ስለዚህ ሙናፊቆች የማይሞቱ በሚመስሉ መልኩ በዓለማዊ ስሌቶች ይያዛሉ፡፡ ማለቂያ የለሽ ዕቅዶችን ያዘጋጃሉ፡፡ እንዲሁም በሙስሊሞች ላይ የሚያዘጋጁት ብልጣ ብልጥ ወጥመድ በዚህ ዓለማዊ ስሌታቸው አውታር ውስጥ

ይገኛል፡፡ ሆኖም በዚህች ዓለም ሕይወት መጌጫዎች መያዝና ቀጣዩን ዓለም መርሳት ምንም አይጠቅማቸውም፡፡ ከዚህ ተቃራኒ በችግር፣ በበታችነትና በከፋ ስቃይ የተሞላ ዓለማዊ ሕይወት ይጠብቃቸዋል፡፡

በእነሱ አመለካከት ሞትን፣ የቂያማ ቀንን፣ ቀጣዩን ዓለም፣ ጀነትና ጀሀነምን በመሳሰሉ ወሳኝ ነገሮች ላይ ላለማስተንተን በቂ ምክንያት አላቸው፡፡ ለእነሱ ምድራዊ ሕይወት መጨረሻ ያላት አትመስላቸውም፡፡ እንዲሁም ወደቀጣዩ ዓለም ከሄዱ ጥሩ ሽልማትን የሚያገኙ ይመስላቸዋል፡፡ በቁርአን ውስጥ የተጠቀሰው የወይን ተክል ባለቤት የዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡

*ነፍሱን በዳይ ሆኖ ወደ አትክልት ሥፍራው ገባ፡፡ አለም፡- ይህች ትጠፋለች ብዬ ፈጽሞ አልገምትም፡፡ ትንሳኤ ትከሰታለች ብዬ አልገምትም፡፡ ወደ ጌታዬ ብለመሰም እንኳን የተሻለ መመለስን በርግጥ አገኛለሁ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ከህፍ፡35-36)*

አንድ ሰው ጀነትን ለማግኘት በሃይማኖት ሥነ-ምግባር እሴቶች እንዳይኖር፣ ወደ አላህ (ሱ.ወ) እንዳይመለስ፣ አላህ (ሱ.ወ) በሚፈልገው ነፀብራቅ እንዳይኖር የሚያደርገው ዋነኛ አጋጅ ዓለማዊ ፍላጎቱ ነው፡፡ በሌላ አባባል ለዓለም ያለው ፍቅር ነው፡፡ ሆኖም የሁሉም ዓለማዊ ፍቅሮች አንዱ መገለጫ ሰዎችን ከአላህ (ሱ.ወ) እና ከርሱ መንገድ ማራቃቸው ነው፡፡ ነገር ግን ወሳኙ ነገር ቆይቶም ይሁን አሁን ዓለማዊ ፍቅሮቻቸው ለብቻቸው ይተዋቸዋል፡፡ ሞት ሲመጣ ማንኛውም ያከበሩት ጸጋ ምንም ጥቅም እንደሌለው ይረጋገጣል፡፡ እዚህች ዓለም ላይ ቅድሚያ የሰጡትን ነገር በሙሉ ወደኋላ ትተው ለብቻቸው ወደአላህ (ሱ.ወ) ይሄዳሉ፡፡

## ይህች ዓለም ጊዜያዊ መሆኗን መገንዘብ ያዳግታቸዋል

*ከአንዳች ነገር የተሰጣችሁት የዚህች ዓለም መጠቀሚያና ጌጥ ነው፡፡ ከአላህ ዘንድ ያለው በላጭና ዘላለማዊ ነው፡፡ አታስተውሉምን? (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ቀሰስ፡60)*

ሙናፊቆች ቁርአንን ይማራሉ፡፡ ከአንቀጾቹም ይህች ዓለም አታላይ መሆኗን ይረዳሉ፡፡ እውነተኛ ሕይወት የቀጣዩ ዓለም ሕይወት እንደሆነና እዚያ አሸናፊዎችና ተሸናፊዎች እንደሚኖሩና አሸናፊ ለመሆን አንድ ሰው በአላህ (ሱ.ወ) መጽሐፍ መሠረት መኖር እንዳለበት ይረዳሉ፡፡ ይህ ሁሉ ቢሆንም ይህችን ዓለም ይመርጣሉ፡፡

ለምንድን ነው ሙናፊቆች ትርፋማ ለሚያደርጋቸው መንገድ ጀርባቸውን የሚሰጡት? መጨረሻው እሳት የሆነን መንገድ ለምን መረጡ? ከተባለ የዚህ አስገራሚው የሙናፊቆች መልስ በቁርአን ውስጥ ተሰጥቷል፡፡

*እርሷ የዚህች ዓለም ሕይወት ብቻ ናት፡፡ እንሞታለን፤ ሕያው እንሆናለን፡፡ ከጊዜ ውጭ ሌላ የሚያጠፋን ነገር የለም ይላሉ፡፡ በዚህ ላይ ምንም ዕውቀት የላቸውም፡፡ እነርሱ የሚጠራጠሩ እንጂ ሌላ አይደሉም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ጃሲያ፡24)*

የዚህ ዋነኛ ምክንያት እራሳቸውን ከቀጣዩ ዓለም ነፃ የሆኑ አድርገው መቁጠራቸው ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው በአስተሳሰባቸው በመኖሩ ሙሉ በሙሉ የማያምኑበት የቀጣዩ ዓለም ሕይወት ቢኖርም እንኳን እዚያም አስደሳች ሕይወት እንኖራለን ብለው ያስባሉ፡፡ ስለዚህ ልባቸው በዓለማዊ ፍቅር እንዳይያዝ አያደርጉም፡፡ ከውጪ ሲታይ እምነት ያላቸው ቢመስሉም ዓለማዊ ፍላጎቶቻቸውን ልባቸው ውስጥ ደብቀዋል፡፡ ዓይናቸውን በዚህች ዓለም ፍቅር ላይ ተክለዋል፡፡ እናም ዓለማዊ ፍቅራቸው ምኞታቸውን ይመራዋል፡፡ ለሙናፊቆች የዚህች ዓለም ሕይወት አጭርና አላፊ የመሆኑ እውነታ ባዶና ትርጉም የለሽ ነው፡፡ ገዳይ በሽታ ሰውነትን እንደሚበክለው ሁሉ ዓለማዊ ፍቅር ማንነታቸውን በክሎታል፡፡

## ዓለማዊ ውበቶችን ያጠፋሉ

*እነዚያም የካዱት በእሳት ላይ በሚጋፈጡ ቀን "ጣፋጮቻችሁን በአነስተኛይቱ ሕይወታችሁ አሳለፋችሁ፤ በርሷም ተጣቀማችሁ፤ ስለዚህ በምድር ላይ ያለ አግባብ ትኮሩ በነበራችሁትና ታምጹ በነበራችሁት ዛሬ የውርደትን ቅጣት ትመነዳላችሁ" (ይባላሉ)፡፡ (ሱረህ አል-አሕቃፍ፡20)*

ምንም እንኳን የሚኖሩት ለዚህች ዓለም ሕይወት ቢሆንም እነዚህ ሰዎች በፍጹም መርካትና ዓለማዊ ጸጋዎችን መጠቀም አይችሉም፡፡ አንድ ሰው ይህን ለማድረግ ከልቡ ወደ አላህ (ሱ.ወ) ሊመለስ ይገባል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የአገልጋዮቹን ታላቅነት፣ ውበት፣ ጤና፣ ጥበብ፣ ሃብትና ውጤታማነት ይጨምራል፡፡ እናም ወደእሱ ከልብ የሚመለሱትን ሌሎች በርካታ ጸጋዎችን ይሰጣቸዋል፡፡ እውነተኛ መንፋሳዊና አካላዊ ውበት ያላቸው አማኞች ብቻ ናቸው፡፡ አማኝ ከዚህች ዓለም ምንም አይጠብቅም፡፡ ነገር ግን በዚህች ዓለም ላይ ስላሉ ውበቶች ይረዳል፡፡

ነገር ግን እያወቁ የአላህን አናቅጽ የካዱት የሙናፊቆች ጸጋዎች በተከታታይ በመቀነስ ይጠፋሉ፡፡ ይህንም ያመጡት በራሳቸው እጅ ነው፡፡ አጋጣሚዎች እያሉ ፊታቸውን አዙረው ሆን ብለው ከጸጋዎች እራሳቸውን አሸሹ፡፡ ሁሉም ግምታቸው ዓለማዊ ነው፡፡ ነገር ግን እራሳቸውን የሰጡላቸውን ዓለማዊ ጥቅሞች አላህ (ሱ.ወ) ካልፈለገ በስተቀር አያገኙም፡፡

አላህ (ሱ.ወ) ለማይገባቸው ሰዎች ምንም ዓይነት ዓለማዊ ጥቅሞችን አይሰጥም፡፡ እነሱ እንደ የበላይነት መገለጫ የሚቆጥሩትን ማንኛውንም ዓለማዊ

ጥቅም ካገኙ እጅግ የሚደሰቱ ይመስላቸዋል፡፡ ሆኖም እውነታው ሁሉም የሚሰጧቸው ዓለማዊ ውበቶች ዓላማ በሌላ አንቀጽ እንደተፈገለጸው አንድና አንድ ብቻ ነው፡፡

*ገንዘቦቻቸውም፣ ልጆቻቸውም አይድነቁህ፡፡ አላህ የሚሻው በዚህች ዓለም ውስጥ በነርሱ ሊቀጣቸው ነው፡፡ ነፍሶቻቸውም እነርሱ ከሀዲ ሆነው እንዲወጡ ሊያደርግ ነው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡55)*

እነሱ ከሚገምቱት በተቃራኒ የዚህች ዓለም ሕይወት የደስታና የምቾት ቦታ አይደለችም፡፡ በዚህች በሚኖሩባት ዓለም አላህ (ሱ.ወ) በርሱ ላይ በግልጽ ጦርነት ላወጁት ሰዎች ጥሩ ነገሮችን አይሰጣቸውም፡፡ ይህች ዓለም ብቸኛ ዓላማቸው ናት፡፡ እናም እዚህ ይጥራሉ፡፡ ሆኖም አላህ (ሱ.ወ) በቀጣዩ አንቀጽ እንደሚነግረን የሚያገኙት ነገር በሙሉ ባዶ ነው፡፡

*እነዚያ በዚህች ዓለም ሕይወት ውስጥ ሥራን ያሳመሩ የሚመስላቸው ግና ሥራዎቻቸው ሁሉ ከንቱ የሆኑባቸው ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ከህፍ፡104)*

## የቂያማ ቀንን ይረሳሉ

የትንሳኤ ቀን ዓለም የምታበቃበትና በሽብር የተሞላ ቀን ነው፡፡ እንደ ቁርአን አንቀጾች ገለፃ ፀሐይ በጨለማ ትጠቀጠቃለች፡፡ ከዋክብት በመደብዘዝ በተከታታይ ወደመሬት ይወድቃሉ፡፡ ባህሮች እርስ በርስ ይደበላለቃሉ፡፡ ሰማያት ይከፋፈታሉ፡፡ የሰው ልጆች በሙሉ ከተቀበሩት ይቀሰቀሳሉ፡፡ ቁርአን በዚያ ቀን ሕፃናት ሽበታም እንደሚሆኑና እርጉዝ ሴትም ከመፍራቷ የተነሳ እንደምትጨነግፍ ገልጿል፡፡ ከትንሳኤ በኋላ ሰዎችን የቂያማ ቀን ይጠብቃቸዋል፡፡

አማኞች በቂያማ ቀን በሚመረመሩበት ዕለት ላለመዋረድና ምርመራቸውን በቶሎ ጨርሰው ጀነት ለመግባት ተስፋ በማድረግ የትንሳኤ ቀን የሚያስነሳውን ስጋት ከወዲሁ ይፈራሉ፡፡ ሙናፊቅም የቂያማ ቀንንና ባህሪያቱን ያውቃል፡፡ ቁርአንን ስለሚያነብ የዚያ ቀን ዝርዝር ሁኔታው ተገልፆለታል፡፡ ሆኖም የሙናፊቅ አንዱ ባህሪይ ምንም እንኳን መረጃን ከማያጠራጥረው የቁርአን ምንጭ ቢያገኝም አሁንም ቀጣዩን ዓለም በተመለከተ ጥርጣሬን ይዟል፡፡ ስለዚህ ሕይወቱን ከዚህ የእውነታዎች ሁሉ ታላቅ እውነታ አንፃር አይመራም፡፡ በርግጥም ለአፍታ እንኳን ስለዚህ እውነታ በንጹሕ አዕምሮ ባለማሰብ ለመርሳት ይሞክራል፡፡

*ይልቅ እነሱ ሰዓቷን አስተባበሉ፡፡ ሰዓቷን ለሚያስተባብል አቃጣይ ቅጣትን አዘጋጅተናል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ፉርቃን፡11)*

# የሙናፊቆች በራስ መብቃቃት

አላህን የሚፈሩ ሰዎች ሁሌም የአላህን እርዳታና ተቀባይነት ለማግኘት ይተጋሉ። ለምሳሌ – በነብዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) አንደበት የሚከተለው እንደተነገረ ከቁርአን እንማራለን፡–

*እርሱም አጠጣላቸው። ከዚያም ወደጥላው ተመለሱ። "ጌታዬ ሆይ! የምታወርድልኝን መልካም ነገሮች ሁሉ ፈላጊ ነኝ" አለም። (አል–ቁርአን፣ ሱረህ አል–ቀሰስ፡24)*

አማኞች በእያንዳንዱ ሁኔታ ጌታቸው እንደሚያስፈልጋቸው ይረዳሉ። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ፀባያቸው ሙሉ ለሙሉ ከአማኞች በተቃራኒ የሆነው የሙናፊቆች ባህሪይ የሚገለጸው። ይኸውም ሙናፊቆች ራሳቸውን ከአላህ (ሱ.ወ) የተብቃቁና የአላህ (ሱ.ወ) እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው አያውቁም። ቁርአን ምንም ዓይነት እርዳታ እንደማያስፈልጋቸው የሚያስቡ ሰዎችን ለመግለጽ "ኢስተግና" (በራስ መርካት፣ በራስ መብቃቃት) የሚለውን ቃል ይጠቀማል።

ሆኖም ቃሉ የሚያገለግለው ለአላህ (ሱ.ወ) ብቻ ነው። ምክንያቱም አላህ (ሱ.ወ) ማንንም አይፈልግም። የሰው ልጆችና ሌሎች ሁሉም ነገሮች በአላህ (ሱ.ወ) የተፈጠሩና ለመኖር የአላህን እርዳታ የሚሹ ረዳት የለሽ ፍጥረታት ናቸው። አላህ (ሱ.ወ) የሰው ልጆች ይህን ረዳት አልባነታቸውን እንዲረዱ እንደሚከተለው ይነግራቸዋል።

*የሰው ልጆች ሆይ! እነሆ ምሳሌ ተሰጥቷልና አዳምጡ። እነዚያ ከአላህ ሌላ የምታመልኳቸው ዝንብን እንኳን መፍጠር አይችሉም – ለዚህ ተግባር ቢሰባሰቡም። ዝንብ አንዳች ነገር ቢነጥቃቸውም የማስጣል አቅም የላቸውም። ፈላጊዎቹም ተፈላጊዎቹም ደካሞች ናቸው። (አል–ቁርአን፣ ሱረህ አል–ሐጅ፡73)*

በሌላ በኩል ሙናፊቆች ከአላህ (ሱ.ወ) የሚፈልጉ መሆናቸውን አይረዱም። በውስጣቸው ከሰይጣን ጋር የተመሳሰለ ትዕቢትን ይዘዋል። ምንም እንኳን አላህ (ሱ.ወ) ዘንድና አማኞች ዘንድ የተናቁ ቢሆንም ሰዎችን ማታለል የሚችሉ ይመስላቸዋል። እናም እራሳቸውንም እንደ ብልህና የበላይ አድርገው ይቆጥራሉ።

ጉድለትና ስህተት ሊኖርባቸው እንደሚችል ፍጹም ባለመቀበል ሁሌም በእውነተኛ መንገድ ላይ ያሉ ይመስላቸዋል። እነዚህ ሁሉ "በራስ መብቃቃት"

የተባለው በሽታ ምልክቶች ናቸው፡፡ በርግጥም አላህ (ሱ.ወ) ሙናፊቆች ሁለት ፊት በመሆናቸው ብቻ የሚጨምር በሽታ በልባቸው ውስጥ እንዳለባቸው ገልጿል፡፡

*ከሰዎች መካከል "በአላህ እና በመጭው ዓለም መኖር አምነናል" የሚሉ አሉ፡፡ ፈጽሞ አማኞች አይደሉም፡፡ አላህንና እነዚያን ያመኑትን ሊያታልሉ ይሞክራሉ፡፡ ራሳቸውን እንጂ ሌላ ማንንም አያታልሉም፡፡ ግና ይህን አይገነዘቡም፡፡ ልቦናቸው ውስጥ በሽታ አለ፡፡ አላህ በሽታን ጨመረላቸው፡፡ ይዋሹት በነበረው ሰበብ አሳማሚ ቅጣት ይጠብቃቸዋል፡፡ (አል-ቁርአን ሱረህ፣ አል-በቀራህ፡8-10)*

የራስ መብቃቃት በሽታ በታሪክ ውስጥ በሁሉም ከህዲያን ላይ ታይቷል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በበርካታ የቁርአን አንቀጾች ሰዎችን በቀጥታ ወደ ገሀነም የሚመራው በሽታ ይህ እንደሆነ ገልጿል፡፡

ይህ በሽታ በሰይጣን ተጀመረ፡፡ እራሱን ከተፈጠሩ ነገሮች በሙሉ የበላይ አድርጎ የቆጠረው ሰይጣን የመጀመሪያው የራስ መብቃቃት ምልክት የታየበት አላህ (ሱ.ወ) ቢያዘውም ለነብዩ አደም (ዐ.ሰ) ሱጁድ አልወርድም ማለቱ ነው፡፡ ለዚህ ባህሪው ሰይጣን የሰጠው ማብራሪያ ነብዩ አደም (ዐ.ሰ) ከመሬት እንደተፈጠሩና እርሱ ግን ከእሳት መፈጠሩን ነው፡፡ ስለዚህ ዓለም ከተፈጠረች ጀምሮ የነበረ እያንዳንዱ ከህዲ ከሰይጣን ጋር ተመሳሳይ ተፈጥሮን ስለሚጋራ ይህን ተመሳሳይ ባህሪይ ይዟል፡፡

የሙናፊቆች በራስ መብቃቃት መጀመሪያ ላይ በሰይጣን ከተገለጸው ባህሪ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ቁርአን እንደሚያስቀምጠው የመጀመሪያው በራስ መብቃቃት ምልክት ሰውዬው በልቡ ውስጥ በሽታ እንዳለ አልቀበልም ሲል ነው፡፡ በርግጥም ሙናፊቆች ይህን አይቀበሉም፡፡ ይህም በሽታው ይበልጥ እንዲጨምር ያደርገዋል፡፡ ትዕቢተኛና ራሱን እንደ ምሉዕ የሚቆጥር ሰው ኃጢአትንም ሆነ እርጉምነትን ማስወገድ እንዳለበት አይሰማውም፡፡ በርግጥም አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን ውስጥ እራሳቸውን እንከን የለሽ አድርገው የሚቆጥሩ ሰዎች ድንበሮችን እንደሚያልፉ ገልጿል፡፡ በአንድ የቁርአን አንቀጽ ቀጣዩ ተገልጿል፡-

*በእውነቱ የሰው ልጅ ወሰንን ያልፋል፡፡ የዚህ ምክንያቱ ራሱን የተብቃቃ አድርጎ መመልከቱ ነው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ዐለቅ፡6-7)*

ሙናፊቆች የያዙት በራስ መብቃቃት በቁርአን አንቀጾች በጥልቅ የተብራሩ ሲሆን አንድ በአንድ ሲገለጹ ደግሞ ይበልጥ ግልጽ የሚሆኑ በርካታ ምልክቶችና ውጤቶች አሉት፡፡

## (1) ለቁርአን አንቀጾች ምንም ግምት አይሰጡም

የቁርአን አንቀጾች እንደማይመከቷቸው የሚያስቡ አካላት፣ ወይም በሌላ አባባል አንቀጾቹ እነሱ ላይ ተግባራዊ እንደሚደረጉ ከማይረዱ የከሀዲያን ቡድኖች መካከል አንዱ የሙናፊቆች ቡድን ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ቁርአንን ቢያነቡም የበርካታ አንቀጾች ግዴታዎች ከእነሱ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ይመስላቸዋል፡፡ ለምሳሌ – የጀሀነም ሙብራራት የአማኝን ፍርሃት ይጨምረዋል፡፡ ምክንያቱም ሁሌም የአላህን ተቀባይነት ያለ ማግኘትና ወደ ጀሀነም የመግባት አጋጣሚው ይኖራልና፡፡ ሆኖም ሙናፊቆች እራሳቸውን ለጀነት የተወሰኑ አድርገው ስለሚቆጥሩ እነዚህ አያዎች እነሱ ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ የላቸውም፡፡

ስለዚህ በርካታ እነሱን የሚመለከቱ አንቀጾችን ማየትና መረዳት አይችሉም፡፡ አማኝ በቁርአን አያዎች ሲታወስ እንዲሁም እነሱ ተጠቅሰው ምክር ሲሰጠው ፍራቻው ይጨምራል፡፡ እናም ልዩ የሆነ እጅ መስጠትን በማሳየት በእነሱ ይኖራሉ፡፡ ሆኖም ሙናፊቅ በእነሱ ሲመከር የቁርአን አንቀጾችን እንዳልሰማ ይሆናል፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) ጥበብ በማስተንተን ምክር አይወስድም፡፡

*ከማስጠንቀቂያ መሸሻቸው ለምን ይሁን? (ሱረህ አል–ሙደሥር፡49)*

ሌላኛው የሙናፊቆች መለያ ባህሪይ ለሃይማኖት ያላቸው ከበሬታ በቃላት የተገለጸ መሆኑ ነው፡፡ ሐሰታቸው በቁርአን አንቀጾች መሠረት ሕይወታቸውን ከመምራት አንፃር ይጋለጣል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በበርካታ የቁርአን አንቀጾች ለእነዚህ ትኩረት እንደማይሰጡና ከትዕዛዛቸውም እንዴት እንደሚርቁ ገልጿል፡፡

*እነዚያን "በአንተም ከአንተ በፊትም በተወረደው መልዕክት አምነናል" የሚሉትን ወገኖች አላየህምን? በርሱ እንዲክዱ በርግጥ የታዘዙ ሲሆኑ ወደ ጣዖት መፋረድን ይፈልጋሉ፡፡ ሰይጣንም ይበልጥ ሊያስታቸው ይሻል፡፡ "አላህ ወዳወረደውና ወደ መልዕክተኛው ኑ" በተባሉ ጊዜ መናፍቃን ከአንተ ሲሸሹ ታያለህ፡፡ (አል–ቁርአን፣ ሱረህ አን–ኒሳእ፡60–61)*

*ከመጽሐፉ የተወሰነ ክፍል የተሰጣቸውን ወገኖች ሁኔታ አላስተዋልክምን? ወደ አላህ መጽሐፍ – በመካከላቸው ብይን ይሰጥ ዘንድ – ሲጋበዙ ከመካከላቸው ከፊሎቹ ያፈገፍጋሉ፡፡ እነሱ መሸሽ ባህሪያቸው የሆኑ ናቸው፡፡ (አል–ቁርአን፣ ሱረህ አል ዒምራን፡23)*

## (2) እራሳቸውን እጅግ ብልህ አድርገው ይቆጥራሉ

ምንም እንኳን እውነተኛ ጥበብ የሌላቸው ቢሆኑም ሙናፊቆች በራሳቸው ብልህነት እጅግ ይረካሉ፡፡ የራሳቸውን አሰቃቂ ተፈጥሮአዊ ገጽታ መመልከት አይችሉም፡፡ እያንዳንዱ ሥራቸውና እያንዳንዱ ውሳኔያቸው እጅግ ጥሩ መስሎአቸው

ይኖራሉ፡፡ በተለይ በሃይማኖት ጉዳይ እራሳቸውን በራሳቸው ላይ ብቸኛ ኃይል እንዳላቸው ያስባሉ፡፡ በተጣመመው ምክንያታዊነታቸው ሳቢያ አማኞች በተሳሳተ መንገድ ላይ ያሉ ይመስላቸዋል፡፡ ሎጂካል ያልሆነው አስተሳሰባቸው በቀጣዩ አንቀጽ ተገልጿል፡፡

*መናፍቃንና እነዚያ ከልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ያለባቸው ወገኖች "እነኚህ ሰዎች ሃይማኖታቸው አታሏቸዋል" ባሉ ጊዜ የሆነውን አስታውስ፡፡ በአላህ የተመካ እርሱው በቂው ነው፡፡ አላህ አሸናፊም ጥበበኛም ነውና፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አንፋል፡49)*

ከአንቀጹ እንደምንረዳው እነሱ ብቻ በቀጥተኛው ጎዳና ላይ ያሉ ስለሚመስላቸው የአማኞችን ጥበብ አይቀበሉትም፡፡ ሆኖም እውነታው አማኞች አላህ (ሱ.ወ) እውነተኛ ጥበብን የለገሳቸው በምድር ላይ ያሉ ብቸኛው ህብረተሰቦች ናቸው፡፡ ይህም ሆኖ ሙናፊቆች እራሳቸውን ከሁሉም በላይ አድርገው ያስባሉ፡፡ እናም ሁልጊዜ ሙእሚኖች በእነሱ ብልህነት አለመደነቃቸውን ይገልፃሉ፡፡ ይህ በአማኞች ላይ ያላቸው የተሳሳተ ሐሳብ በቀጣዩ አንቀጽ እንደተገለጸው ሙናፊቆችን ወደ አሳዛኝ ደረጃ ይመራቸዋል፡፡

*"ሌሎች እንዳመኑት እመኑ" ሲባሉ ጊዜ "ቂሎች እንዳመኑት እኛም ልናምን ነው?" ይላሉ፡፡ አዋጅ! ቂሎች እነርሱ ናቸው፡፡ ግና ያሉበትን አያውቁም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡13)*

በአንቀጹ ላይ እንደተገለጸው ሙናፊቆች "ቂሎች" ናቸው፡፡ ምክንያቱም በጣም የሚያስጠሉ ውሸቶችን ይናገራሉ፡፡ እንዲሁም ያለ ምንም ምክንያት ወጥመድ የሚያዘጋጁ ቢሆንም አማኞች አይደርሱበትም፣ መልዕክተኛውም ይህን ዕቅድ አያጋልጡም ብለው ያስባሉ፡፡ ሆኖም ጊዜው ሲደርስ አላህ (ሱ.ወ) ለራሳቸውና ለሌሎች ሰዎች ያሉበትን አዋራጅ ደረጃ ያሳያቸዋል፡፡

*ከናንተ ውስጥ ወደኋላ የሚቀር አለ፡፡ አንዳች ችግር ሲያጋጥማችሁ "ከነርሱ ጋር ባለመገኘቴ አላህ ውለታ ውሎልኛል" ይላል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡72)*

ለአላህ (ሱ.ወ) እና ለመልዕተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ባለማደር፣ በለጋስነት ገንዘብን ባለማውጣት ወይንም በርካታ አምልኮዎችን ባለመፈጸም ሙናፊቆች የሚጠቀሙ ይመስላቸዋል፡፡ እንዲሁም እነዚህን ሃይማኖታዊ ተግባራትን መፈጸምን ጎጂ አድርገው ይመለከታሉ፡፡ ስለዚህ የአላህን ተቀባይነት ስለማይፈልጉና እራሳቸውን እንከን የለሽ አድርገው ስለሚቆጥሩ እነዚህን አምልኮዎች መፈጸም እጅግ አስቸጋሪ ተግባር ይመስላቸዋል፡፡

ሙናፊቆች ወደኋላ በመሸሽ እራሳቸውን መሪ አድርገው የሚቆጥሩባቸውን ጥቂት ነገሮች መመልከት እንችላለን፡፡

## (ሀ) ከመታገል ይታቀባሉ

ለዚህች ዓለም ሕይወት የተሰጡ ስለሆነ ሙናፊቆች ከፍተኛ የሞት ፍራቻ አላቸው፡፡ ሞትን ማሰብም ሰላም ይነሳቸዋል፡፡ ሞት የአላህ (ሱ.ወ) ትዕዛዝ መሆኑን አያስተነትኑትም ወይም ሃይማኖታዊ ተግባራቸውን ሞታቸው እስኪደርስ መቀጠል እንዳለባቸው አይረዱም፡፡ በርግጥ በረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ጊዜ ይኖሩ የነበሩ ሙናፊቆችን ሁኔታ አላህ (ሱ.ወ) ገልፆልናል፡፡ ወደ ጦርነት አለመሄድ ከሞት አደጋ የሚያድናቸው ይመስላቸዋል፡፡ እናም ወደ ጦርነት ቦታ ላለመሄድ ምክንያት መደርደርን እንደ ጤናማ አስተሳሰብ ይቆጥሩታል፡፡ በቁርአን ውስጥ አላህ (ሱ.ወ) ሙናፊቆች ከጦርነት በመቅረታቸው የሚሰማቸውን ደስታ ተናግሯል፡፡

*እነዚያ የቀሩት ከመልዕክተኛው ተነጥሎ መቅረታቸው አስደሰታቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡81)*

ሆኖም እውነታው ሞት ማንኛውንም ሰው በማንኛውም ሰዓት ሊወስደው ይችላል፡፡ ሙናፊቆች የሚያስቡት በጥራዝ ነጠቅ ላይ ላዩን ስለሆነ ይህን ነጥብ ወደ አዕምሮአቸው አያመጡትም፡፡ ከአደጋ ሸሽቶ ቤቱ የተቀመጠ ሰው ሞት እንዳይመጣ የሚያደርግ ምንም ዓይነት ማረጋገጫ የለም፡፡ ሆኖም መጀመሪያ ላይ እንደተገለጸው ሙናፊቆች የራሳቸውን በጥልቀት ያለ ማሰብ መረዳት ያንሳቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ማንኛውም ጊዜያዊ መድህን ወይም ለአጭር ጊዜ ሞት መተላለፉ የጨዋታው መሪ የሚያርጋቸው ይመስላቸዋል፡፡

## (ለ) ከአማኞች ጋር አብረው አይኖሩም

አላህ (ሱ.ወ) የአማኝ ህብረተሰብን በጥሩና በመጥፎ እንደሚፈትን ገልጿል፡፡ አማኞች የቀጣዩን ዓለም ስኬታማነት ለማግኘት ይፈተናሉ፡፡ ስለዚህ በርካታ ሁኔታዎችን ያያሉ፡፡ ጥቂቶቹ በውስጣቸው መልካምን የያዙ ይመስላሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ አይመስሉም፡፡ ነገር ግን አላህ (ሱ.ወ) ሁሉንም ለአማኞች ጥቅም እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል፡፡ እነሱ የተጋለጡበትን የሙከራ ምስጢር ስለሚረዱ የአላህን ተቀባይነት ለማግኘት ተመሳሳይ ጥረትና ጉጉት ያሳያሉ፡፡ በፍጹም ተስፋ አይቆርጡም፡፡ አይፈሩምም፡፡ ሆኖም በምእምናን ህብረተሰብ ውስጥ የሙከራ ምስጢርን የማይረዳና የሁኔታዎችን ውጫዊ ገጽታ ብቻ የሚያይ ሌላ ቡድን ይገኛል፡፡ ከዚህ በፊት እንደተወሳው ሙናፊቆች እራሳቸውን በቻሉት ያህል ከችግር

ማራቅ ይፈልጋሉ፡፡ ሁኔታዎች ከተመቻቹ አማኞች ላይ የሚደርሰውን ፈተና/አደጋ መቀበል ስለማይፈልጉ ከአማኝ ህብረተሰብ እጅግ ይርቃሉ፡፡ በርግጥም አላህ (ሱ.ወ) በበርካታ ያለፉ ጊዜያት ምሳሌዎች ለጦርነት ልዩ ቦታን በመስጠት ሙናፊቆች የቻሉትን ያህል ርቀው አማኞችን መመልከት እንደሚልጉ ገልጿል፡፡

*የከሀደት ሠራዊት አልሄደም ብለው ያስባሉ፡፡ ሠራዊቱ ቢመጣ ገጠር ውስጥ ከዘላኖች ጋር ሆነው ስለናንተም ወሬን እየጠየቁ መኖርን ይመኛሉ፡፡ ከናንተ ጋር ቢገኙም ጥቂትን እንጂ አይዋጉም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አሕዛብ፡20)*

ሌላ የቁርአን አንቀጽ በሚደርሱት አደጋዎች ላለመነካት ከአማኞች ርቀው መኖር የሚፈልጉት ሙናፊቆች እንዴት እራሳቸውን የተጠቀሙ አድርገው እንደሚቆጥሩ ይገልፃል፡፡

*መልካም ነገር ሲያገኝህ ይከፋቸዋል፡፡ አንዳች ችግር ሲደርስብህ "እኛ ድሮውንም የሚበጀንን እርምጃ ወስደናል" ይላሉ፡፡ በደስታ ተውጠው ይሸሻሉም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡50)*

## (ሐ) የአላህ መልዕክተኛን አይታዘዙም

ለአላህ መልዕክተኛ መታዘዝ ማለት ከሁሉም ነገር በላይ አላህንና መጽሐፉን መያዝ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን የሚለውን መታዘዝ ማለት ስለሆነ ነው፡፡ አላህን የሚታዘዙና ለአላህ (ሱ.ወ) ከልብ ያደሩ አማኞች ተመሳሳይ ታዛዥነትና ቅንነት ለመልዕክተኛው ያሳያሉ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከሕይወታቸውና ከምኞታቸው በላይ እነሱ ዘንድ ዋጋ አላቸው፡፡ ቁርአን በሕይወታቸው ዋጋ የአላህን መልዕክተኛ የተከላከሉ፣ ከእርሳቸው ጋር ወደ ጦር ሜዳ የሄዱ፣ እንዲሁም እሳቸውን ከራሳቸው በላይ ስለያዙት ሰዎች ይናገራል፡፡

የጊዜው ሙናፊቆች ወደ ጦር ሜዳ አይሄዱም ነበር፡፡ ነገር ግን ረሱልን (ሰ.ዐ.ወ) እንዲጠብቁ ስላልተገደዱ ከፍተኛ ጥቅም እንዳገኙና ብልህ እንደሆኑ እራሳቸውን አሰበዋል፡፡ ወታደሮችን ከተቀላቀሉ በኋላ ፈርተው የተመለሱ ሙናፊቆች የነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ጥሪ እንኳን ሳያዳምጡ ወደኋላ ላይመለከቱ ሸሽተዋል፡፡

*ማንንም ዞራችሁ ሳታዩ በወጣችሁና መልዕክተኛውም ትመለሱ ዘንድ በጠራችሁ ጊዜ የሆነውን አስታውስ . . . (አል-ቁርአን፣ ሱረህ ኣል ዒምራን፡153)*

መሸሻቸው እራሳቸውን የሚያድኑበት መንገድ ይመስላቸዋል፡፡ ሆኖም እውነታው የረሱልን (ሰ.0.ወ) ትዕዛዝ ባለማክበር ትልቅ ስህተት ሠርተዋል፡፡ የአላህን ቁጣ በማግኘታቸው ለዘላለም ስቃይ ተዳርገዋል፡፡

## (መ) በጎ ዓላማ አለን ብለው ይናገራሉ

ሙናፊቆች በሁከትና በብጥብጥ እርስ በርስ ይፎካከራሉ፡፡ ነገር ግን አማኞችን ስለሚፈሩ ምንጊዜም እርጉምነታቸው ሲጋለጥ "በጎ ዓላማ" እንዳላቸውና አስታራቂ ዓላማ እንደያዙ በመማል አማኞችን ማሳመን ይፈልጋሉ፡፡ የእርጉምነታቸው ክፋት ወደ አላህ መልዕክተኛ (ሰ.0.ወ) በመሄድ በጎ ዓላማቸውን ሊያሳምኗቸው ትልቅ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የዚህን ግልጽ ምሳሌ በቁርአን ውስጥ መመልከት ይቻላል፡፡

*እጆቻቸው ባስቀደሙት ሳቢያ አንዳች ነገር በገጠማቸው ጊዜ እንዴት ይሆናሉ? ያንቆ "እኛ ከአንተ ለመሸሽ ያቀድነው ለመልካም ዓላማና ስምምነትን ለመሻት እንጂ ለሌላ አይደለም" ሲሉ በአላህ በመማል ከአንተ ዘንድ ይመጣሉ፡፡ እነዚያ እነሱ አላህ ከልቦቻቸው ውስጥ ያሉትን ክፉ ሐሳቦች ያውቅባቸዋል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡62-63)*

እንዴታ! በቁርአን አንቀጹ እንደተገለጸው አላህ (ሱ.ወ) እየዋሹ እንደሆነና በልባቸው ውስጥ የደበቁትን ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ እናም በፈለገው ሰዓት ያጋልጣቸዋል፡፡ መልዕክተኛውንም የእነሱን ሁኔታ እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፡፡

## (ሠ) እራሳቸውን በማመስገን ከትችት ነፃ ማድረግ ይፈልጋሉ

*እነዚያን ራሳቸውን ንጹሕ አድርገው የሚገምቱትን ሰዎች አላየህምን? በፍጹም፣ አላህ የሚሻውን ያጸዳል፡፡ የተምርን ፍሬ ክርንም ያክልም በደል አይደርስባቸውም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡49)*

ለሙናፊቆች የሌሎች ሰዎችን ተቀባይነት ማግኘት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸናል፡፡ በርግጥም ከላይ ባለው አንቀጽ እንደተገለጸው የሌሎችን ተቀባይነትን ለማግኘት ሁሌም እራሳቸውን ያመሰግናሉ፡፡ ስህተታቸው ሲጋለጥ ሁሉንም ስህተታቸውን በመደበቅ ምኞታቸውን ፍትሐዊ ማድረግ ይፈልጋሉ፡፡

አማኝ ባይሆኑም እራሳቸውን እንደ እውነተኛ አማኝ ለመግለጽ ሕመምን ይወስዳሉ፡፡ ነገር ግን ጥረታቸው እነሱን በመሰሉ ሰዎች ላይ ብቻ ነው የሚሳካው፡፡ ብዙ ጊዜ ሳያልፍ አማኞች የእነሱን የሁለት ፊት ባህሪይ በመለየት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳሉ፡፡

## ምክር መቀበል አይችሉም

በዚህ መጽሐፍ ላይ አጽንኦት እንደተሰጠበት የሙናፊቆች አንዱ ባህሪይ ሰይጣናዊ ኩራታቸው ነው፡፡ እጅግ ትዕቢተኛ በመሆናቸው ምንም ዓይነት ጉድለት እንዳለባቸው ወይም በማንኛውም መልኩ ስህተት ውስጥ መውደቃቸውን አይቀበሉም፡፡ ስለነዚህ ጉድለቶች ወይም ስህተቶች ምክር ከተሰጣቸው ይህን ምክር የሚሰጣቸው ሰው ላይ ከፍተኛ ጥላቻን ያሳድራሉ፡፡

ሆኖም የአማኞችና የመልዕክተኞች (ዐ.ሰ) መሠረታዊ ባህሪይ በጥሩ ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል ነው፡፡ በሌላ አባባል አማኞች ሁሌም እርስ በርስ ምክርን ይሰጣጣሉ፡፡ አንዱ የሌላውን ጉድለትና ስህተት ማጽዳት ይፈልጋል፡፡ ሙናፊቆች በአማኞች ህብረተሰብ ውስጥ ስለሚገኙ አማኞች የአላህን ተቀባይነት ለማግኘት በሚያካሂዷቸው ሃይማኖታዊ ተግባራት ላይ በተከታታይ ይገኛሉ፡፡

በነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጊዜ ይኖሩ የነበሩ ሙናፊቆችን በሚገልጹት በቀጣዮቹ አንቀጾች እራሳቸውን እንደ እንከን የለሽ ይቆጥሩ የነበሩ ሙናፊቆች በተሰጣቸው ምክር እንዴት ይናደዱ እንደነበር እንመለከታለን፡፡ በአንድ የቁርአን አንቀጽ ቃላት እንደተገለጸው ከቁርአን ለተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ የሰጡት ምላሽ ድንበር ያለፈ ነው፡፡፡

> *እነሆ እነዚያም የካዱት ሰዎች ቁርአኑን በሰሙ ጊዜ በዓይኖቻቸው ሊጥሉህ (ሊያጠፉህ) ይቃረባሉ፤ እርሱም በርግጥ እብድ ነው ይላሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ቀለም፡51)*

በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የሚሰማቸውን ጥላቻና ቁጣ መደበቁ አስፈላጊ ስላልመሰላቸው ግልጽ አደረጉት፡፡ ይህ ምላሻቸው የመነጨው ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ምክር ስለሰጧቸው መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የሞትን አይቀሬነት፣ በጀሀነምና በቀጣዩ ዓለም ያለው ቅጣትና የስቃይ ደረጃን፣ እንዲሁም ቁርአንን የሚቃወሙት በዚህችም ሆነ በቀጣዩ ዓለም የሚኖራቸው ደረጃ ባይነግሯቸውና ከዚህ ይልቅ ቢያመሰግኑዋቸው ኖሮ ምንም ዓይነት ጥላቻ አይሰማቸውም ነበር፡፡ ነገር ግን በማይለወጠው የአላህ (ሱ.ወ) ሕግ መልዕክተኞች (ዐ.ሰ) ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ይቀጥላሉ፡፡ የሚነገረው ሰው ማንም ይሁን ማን፣ ጥሩን እንዲሠራና መጥፎን እንዲከላከል ያዛሉ፡፡

## የማይቀጡ ይመስላቸዋል

*በልቸውም "አላህ በምንለው ነገር ለምን አይቀጣንም" ይላሉ። የሚማገዱባት ገሀነም በቂያቸው ናት። እጅግ አስከፊ መመለሻ! (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙጃደላህ፡8)*

ሙናፊቆች የሚሠሩትን መጥፎ ተግባር የሚቀጥሉትና እንቅስቃሴያቸውን ከማቆም አሻፈረኝ የሚሉበት ምክንያት አደጋ ይደርስብናል ብለው ስለሚያስቡ ነው። ነገር ግን የአላህ (ሱ.ወ) ሕግ እጅግ የተለየ ስለሆነ ይህ የራሳቸው አመለካከት ነው።

አላህ (ሱ.ወ) ከፈለገ አደጋዎችን በፍጥነት ያደርስባቸዋል ወይም ለጥቂት ጊዜ ያስተላልፉቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ከሚገምቱት በተቃራኒ ሙናፊቆች እራሳቸው የማይረዱት በርካታ ችግር ውስጥ ይገባሉ። ለምሳሌ - ብልሹ ከሆነው አነጋገራቸው፣ ባህሪያቸውና ማሰብ ካለመቻላቸው በተጨማሪ ቀጣይነት ባለው ጭንቀት ውስጥ ይኖራሉ። ውበት ካላቸው ነገሮች ደስታን ማግኘት አይችሉም። እንዲሁም ስለጸጋዎች ዋጋ ዕውቀት ያንሳቸዋል። አላህ (ሱ.ወ) ክህደታቸው እንዲጨምር ጊዜ ለመስጠት የጥቂቶቹን ሞት ያስተላልፈዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ዕድሜያቸው በጨመረ ቁጥር የጀሀነም ስቃያቸው በተመጣጣኝ መልኩ ይጨምራል።

*ገንዘቦቻቸውም ልጆቻቸውም አይድነቁህ። አላህ የሚሻው በዚህች ዓለም ውስጥ በነርሱ ሊቀጣቸው፣ እነርሱም ከሀዲዎች ሆነው ነፍሶቻቸው እንዲወጡ ሊያደርግ ነው። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡85)*

## ዓለማዊ ጸጋዎቻቸው የሚጠብቋቸው ይመስላቸዋል

የነዚህን ሰዎች ዓለማዊ ጸጋዎች ተጽዕኖ ተመልክተናል። እራሳቸውን እንዴት የበላይ አድርገው እንደሚቆጥሩ፣ እንዲሁም ከፍተኛ የራስ መተማመናቸውን አይተናል። ቤተሰባቸውና ጸጋቸው እጅግ ከሚተማመኑባቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው።

በቀጣዩ ዓለም ቤተሰባቸውና ቁሳዊ ሃብታቸው ይጠብቀናል ብለው በማሰብ እራሳቸውን ዘና ያደርጋሉ። በዚህች ዓለም ላይ ያሉ እጅግ ስመጥርና ኃይለኛ ሰዎች እንኳን በአላህ (ሱ.ወ) የተወሰነን አደጋ እንደማይከላከሉላቸው አይረዱም። በዚህም ምክንያት መሠረት የለሽ ኩራትን ያሳያሉ።

ሆኖም እውነታው ሁሉም ነገር አንድ በአንድ ሲጠፉ ይመለከታሉ። በቂያማ ቀን በቤተሰባቸውም ሆነ በየትኛውም የዚህች ዓለም ጸጋ አይታደጉም።

ከዚህ በተቃራኒ ብቸኛና ረዳት የለሽ ይሆናሉ፡፡ ከአላህ (ሱ.ወ) በሚደርስባቸው በርካታ መቅሰፍቶች እነዚህ ሃብቶች በዚህች ዓለምም ምንም ጥቅም እንዳልሰጧቸው ይረዳሉ፡፡

ከዚህ በፊት እንደተወሳው ሃይማኖታዊ የሥነ-ምግባር እሴቶችን ባለመቀበልና ለአማኞች ህብረተሰብ ጀርባቸውን በመስጠት የሚጠቀሙ ይመስላቸዋል፡፡ በዚህም መንገድ እንደ ዓለማዊ ምኞታቸው በምቾት መኖር የሚችሉ ይመስላቸዋል፡፡ ነገር ግን እውነታው ከዚህ ተቃራኒው ነው፡፡ ችግርና ሐዘን ሁሌም ይከተሏቸዋል፡፡ በርግጥም አላህ (ሱ.ወ) በዚህችም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ለሃይማኖት ጀርባቸውን የሚሰጡ ሰዎችን ችግር እንደሚደርስባቸው በመግለጽ ለአማኞች ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል፡፡

*ግና ከመልዕክቴ ያፈገፈገ ሕይወቱ ጭንቅ የበዛት ይሆናል፡፡ በትንሳኤ ቀንም ዕውር አድርገን እንቀሰቅሰዋለን፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ጧሃ፡124)*

## ለጀነት የተወሰኑ ይመስላቸዋል

የሙናፊቆች አንዱ መለያ ባህሪይ በቀጣዩ ዓለም ላይ ያላቸው እምነት ደካማና የተዛባ መሆኑ ነው፡፡ አብዛኞቹ ከሞት በኋላ በዚህች ዓለም ላይ ስለሠሩት ወንጀል እንደሚጠየቁ አያምኑም፡፡ ቢያምኑም እንኳን ወደ ጀነት መግቢያ መስፈርቱን ሁሉ ሠርተው ያሟሉና እራሳቸውን ለጀነት የተወሰኑ አድርገው ይቆጥራሉ፡፡ የዚህ ጎዶሎ አስተሳሰብ ምሳሌዎች በቁርአን ውስጥ ተጠቅሷል፡፡

*ትንሳኤ ትከሰታለች ብዬም አልገምትም፡፡ ወደ ጌታዬ ብመለስም እንኳን የተሻለ መመለስን በርግጥ አገኛለሁ፡፡ (ሱረህ አል-ከህፍ፡36)*

እንደ እነሱ ጎዶሎ አስተሳሰብ በአማኞች መሃል በመኖራቸው የተለያዩ ሥራዎችን ለጥሩም ሆነ ለመጥፎ ሠርተው ይሆናል፡፡ ይህ ስለሆነም በቀጣዩ ዓለም ሽልማትን በማግኘት ያለ ጥርጥር ጀነት እንገባለን ብለው ያስባሉ፡፡ ከዚህ የከፋው ደግሞ በጀሀነም እሳት ተቃጥለው ወደ ጀነት ስለመግባታቸው ማሰባቸው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይህን የተዛባ አስተሳሰብ በቁርአን ውስጥ ገልፆታል፡፡

*የዚህ ሰበቡ "እሳት የሚያገኘን ለተወሰኑ ቀናት ያክል ብቻ ነው" ማለታቸው ነው፡፡ በሃይማኖታቸው ላይ መቅጠፋቸው አሞኛቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ ኣሊ ዒምራን፡24)*

የቁርአን አንቀጹ እንደሚነግረን ይህ ሙናፊቆች በእምነታቸው እራሳቸውን የሚያሞኙበት ፈጠራ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው የቁርአን አንቀጽ ቀጣይ የሆነውና

ከዚህ ቀጥሎ ያለው አንቀጽ ሙናፊቆችን የሚጠብቃቸውን የመጨረሻ ዕጣ ፋንታ ይገልፃል፡፡

*መከሰቱ ቅንጣት በማያጠራጥረውና እያንዳንዷ ነፍስ ቅንጣት ሳትበደል የሥራዋን ዋጋ በምታገኝበት ቀን እንዴት ሊሆኑ ነው? እነርሱም አይበደሉም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ ኣሊ ዒምራን፡25)*

# በራስ መብቃቃት በሽታ የሚመጡ ጉዳቶች

*አላህን በክፉ የጠረጠሩትን መናፍቃንና መናፍቃት፣ ወንዶች አጋሪዎችንና ሴቶች አጋሪዎችን ሊቀጣ፣ እነርሱም ክፉ ከባቢ አለባቸው፡፡ አላህ በነርሱ ተቆጥቷል፡፡ ረግሟቸዋልም፡፡ ገሀነምም አዘጋጅቶላቸዋል፡፡ እጅግ አስከፊ መመለሻ ናት፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ፈትሕ፡6)*

በራስ መብቃቃት እራሱ ለሙናፊቅ የችግር መንስኤው ነው፡፡ ነገር ግን ባለፉት አንቀጾች እንዳየነው ሙናፊቆች አብዛኛውን ጊዜ ይህን አይረዱም፡፡ እጅግ በጣም በራሳቸው የተብቃቁና ትዕቢተኛ ስለሆኑ ቀጣዩን ጥያቄ እንኳን መጠየቅ ያስችላቸዋል፡፡

*በነፍሶቻቸውም ውስጥ (ነብይ ከሆንክ) አላህ በምንለው ነገር አይቀጣንም ኖሮአልን? ይላሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙጃደለህ፡8)*

ከላይ አጽንኦት እንደተሰጠበት ከሚጠብቁት መከራ ይልቅ መንፈሳዊና አካላዊ ጉዳቶችን አጠቃሎ በርካታ መቅሰፍቶች እየወረዱባቸው እንደሆነ አይረዱም፡፡ ቁርአን ሙናፊቆች በአላህ (ሱ.ወ) እና በአንቀጾቹ በመኩራታቸው የሚሰቃዩትን ጉዳት ጠቅሷል፡፡ አሁን እነዚህን አንድ በአንድ እንመልከት፡፡

## (1) ብልህ አይደሉም

ጥበብ የሰው ልጅ ሊይዛቸው ከሚችላቸው ታላላቅ ሃብቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ብልህ ያልሆነ ግለሰብ አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለው፡፡ ብልህ ባይሆንም አለመሆኑን እንኳን አይገነዘብም፡፡ የዚህ ዓይነቱ ሰው ጥበብና ብልህነትን እርስ በርስ ያምታታል፡፡ እናም የተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ይደርሳል፡፡

ተመሳሳይ ነገር የተወሰነ የማሰብ ደረጃን ለሚያገኘው ሙናፊቅም ያገለግላል፡፡ ነገር ግን አላህ (ሱ.ወ) ለአማኞች ብቻ በሚሰጠውና ትክክለኛውን ከተሳሳተው እንዲለዩ በሚያስችላቸው ጥበብ መደሰት አይችልም፡፡ ስለዚህ ሙናፊቆች ከታላላቅ ጸጋዎች ውስጥ አንዱን አጥተዋል፡፡

ጥበብ ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ በእያንዳንዱ የሕይወት ሂደት አንድ ሰው ትክክለኛውንና የተሳሳተውን መረዳት መቻል አለበት፡፡ እንዲሁም እራሱን ከኃጢአት መጠበቅ አለበት፡፡ ሙናፊቅ ለዚህች ዓለም ያለው ከልብ እጅ የመስጠት ሁኔታው ብልህ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ ጥበብን በሚጠይቁ ቀላል ጉዳዮች ላይ እንኳን ውጤት አልባ ነው፡፡ የሙናፊቆች የጥበብ ማነስ ትልቁ ማረጋገጫ የሚሠሩትን አላህ (ሱ.ወ) አያይም ብለው ማሰባቸው ነው (በርግጥም አላህ ከዚህ ሁሉ የጠራ ነው)፡፡ ስለዚህ አማኞችን ማታለል ይፈልጋሉ፡፡ እናም በማታለል ሳይቀጡ የሚቀሩ ይመስላቸዋል፡፡ በቁርአን ውስጥ በቀጣዮቹ ቃላት ተገልጸዋል፡፡

*አላህ የሚደብቁትንና የሚገልጹትን የሚያውቅ መሆኑን አያውቁምን? (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ:77)*

ሌላኛው የሚናገሩት ጥበብ የሌለው ነገር አላህ (ሱ.ወ) ኃጢአታቸውን አለማወቁን ነው፡፡ ሆኖም በቂያማ ቀን አላህ (ሱ.ወ) ዓለም ከተፈጠረች ጀምሮ ይኖሩ የነበሩ ሙናፊቆችን በመከበብ ይቀጣቸዋል፡፡ ከቂያማ ቀን በፊትም በዚህች ዓለም ላይ ያዋርዳቸዋል፡፡

## (2) የቁርአን አንቀጾችን መረዳት አይችሉም

በቁርአን ውስጥ እንደተጠቀሰው ሙስሊሞች፡-

*እነዚያም በጌታቸው አንቀጾች በተገሠጹ ጊዜ (የተረዱ ተቀባዮች ሆነው እንጂ) ደንቆሮዎችና ዕውሮች ሆነው በርሷ ላይ የማይደፉት ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ፉርቃን:73)*

ስለሆነም ሙስሊሞች ለአላህ (ሱ.ወ) አናቅጽ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ ሁሉም አማኞች ሁሉም የቁርአን አንቀጾች በቀጥታ እንደሚመለከቷቸው ስለሚያምኑ እራሳቸውን ከእነሱ አርቀውም ሆነ እንደማይመለከታቸው በማሰብ መቆየት አይችሉም፡፡ ሆኖም የዚህ ዓይነት አስተሳሰብን ለመያዝ አንድ ጠቃሚ ቅድመ መስፈርት አለ፡፡ ይኸውም ግለሰቡ እጅግ ትሁትና እራሱን ከማንኛውም ጉድለትና ብልሽት ነፃ አድርጎ የሚቆጥር መሆን የለበትም፡፡ አንድ ሰው ይህ ከልብ መስጠትና መተናነስ ሲኖረው ነው አላህ (ሱ.ወ) የአንቀጾቹን ትርጉም ልቡ ላይ የሚያሰፍርለት፡፡

በሌላ በኩል ሙናፊቆች እጅግ በጣም ኩራተኛና ለአላህ (ሱ.ወ) እጅ ከመስጠት የራቁ ናቸው፡፡ በራሳቸው በመብቃቃታቸው ምክንያት የዚህ ዓይነት

መረዳትን ማግኘት አይችሉም፡፡ የአላህ መልዕክተኛን ምክር የሚሰሙ ቢሆንም የሚሉትን አንድ ቃል እንኳን መረዳት ያንሳቸዋል፡፡ መረዳት የሚያንሳቸው መሆኑ በቁርአን ውስጥ ተጠቅሷል፡፡

*አንተም ሙታንን አታሰማም፤ ደንቆሮዎችም ዟሪዎች ሆነው በሸሹ ጊዜ ጥሪን አታሰማም፡፡ አንተ ዕውሮችንም ከጥመታቸው የምታቀና አይደለህም፤ በአንቀጾቻችን የሚያምኑትን ሰዎች እንጂ ሌላን አታሰማም፡፡ እነሱም ታዛዦች ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አር-ሩም፡52-53)*

በራስ በመብቃቃታቸው ምክንያት ሙናፊቆች በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.0.ወ) ቃላት ምንም ተጽዕኖ እንዳላደረሰባቸው ቁርአን ይነግረናል፡፡

*በጌታውም አንቀጾች ከተገሠጸና ከርሷ ከዞረ፣ እጆቹም ያስቀደሙትን ከረሳ ሰው ይበልጥ በዳይ ማነው? እኛ በልቦቻቸው ላይ እንዳያውቁት ሺፋኖችን፣ በጆሮዎቻቸውም ውስጥ ድንቁርናን አደረግን፤ ወደ መመራትም ብትጠራቸው ያን ጊዜ ፈጽሞ አይመሩም፡፡ (ሱረህ አል-ከህፍ፡57)*

በድጋሚ ውስጣቸው ባለው የራስ መብቃቃትና የአላህን መጽሐፍ መረዳት ባለመቻላቸው የርሱን በርካታ አናቅጽ በተሳሳተ መልኩ ይረዱታል፡፡ የዚህ ምክንያቱ ኩራታቸውና በራሳቸው ውስን ጥበብ ላይ ያላቸው መሠረት የለሽ እምነት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ቀድሞውኑ ሙናፊቆች እንዴት በአማኝ ህብረተሰብ ውስጥ ሁከትን መፍጠር እንደሚፈልጉ በመንገር በሙናፊቆች ላይ ስላለው በሽታ አስጠንቅቋል፡፡

*እርሱ ያ ባንተ ላይ መጽሐፉን ያወረደ ነው፤ ከርሱ (ከመጽሐፉ) ግልጽ የሆኑ አንቀጾች አሉ፤ እነሱ የመጽሐፉ መሠረቶች ናቸው፡፡ ሌሎችም ተመሳሳዮች አሉ፡፡ እነዚያማ በልቦቻቸው ውስጥ ጥመት ያለባቸው ሰዎች ማሳሳትን ለመፈለግና ትችቱን ለመፈለግ ከርሱ የተመሳሰለውን ይከታተላሉ፡፡ (ትክክለኛ) ትችቱንም አላህ ብቻ እንጂ ሌላ አያውቀውም፡፡ በዕውቀትም የጠለቁት በርሱ አምነናል፤ ሁሉም ከጌታችን ዘንድ ነው ይላሉ፡፡ የአዕምሮ ባለቤቶችም እንጂ (ሌላው) አይገሠጽም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ ኣል ዒምራን፡7)*

## (3) አላህ (ሱ.ወ) በርካታ መንፈሳዊ ችግሮችን ይፈጥርባቸዋል

አላህ (ሱ.ወ) በርሱ ፊት ትዕቢተኛ የሆነንና ራሱን እንደ ተብቃቃ የሚቆጥርን ሰው በርካታ መንፈሳዊ ጉዳቶችን ያደርስበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚህች ዓለም ሕይወቱን ጠባብና ጨለማ ያደርገዋል፡፡ ሙናፊቆች የሚደርሱባቸውን መንፈሳዊ ችግሮች መንስኤ መረዳት ስለማይችሉ በብዥታ ውስጥ ይኖራሉ፡፡

በመጀመሪያ ምንጩን በማያውቁት ምክንያት ምቾት አይሰማቸውም፡፡ ነገር ግን የዚህ ምክንያቱ ግልጽ ነው፡፡

በሁሉም ሰው ነብስያ ላይ መጥፎ ነገር አለ፡፡ ሆኖም አንድ አማኝ ይህን ስለሚረዳ እንዴት እንደሚያስወግደው ያውቃል፡፡ ምክንያቱም ከታች በተጠቀሰው የቁርአን አንቀጽ እንደተገለጸው አላህ (ሱ.ወ) በሰው ነብስያ ላይ ኃጢአትንና መጥፎ ነገርን ሲያደርግ የማስወገጃ መንገዱንም ለሰው ልጆች ሰጥቷል፡፡

*በነፍስም፣ ባስተካከላትም፤ አመጽዋንና ፍርሃትዋንም ባሳወቃት (ጌታ እምላለሁ)፤ ከኃጢአት ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በርግጥ አገኘ፡፡ (በኃጢአት) የሸፈናትም ሰው በውነት አፈረ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አሽ-ሽምስ፡7-10)*

ከላይ እንደተመለከትነው አንደኛው የነብስያ ገጽታ ወደ እርጉምነት እንደሚጠራው ሁሉ አንድ ሰው ሁሌም ወደጥሩነት የሚመራው ሕሊና አለው፡፡ የነብስያ ጥሪ የሰይጣን ጥሪ ሲሆን የአንድ ሰው የሕሊና ጥሪ ደግሞ የእውነት ጥሪ ነው፡፡ ሁሌም ሕሊናቸው የሚያዛቸውን ባለመቀበል ሙናፊቆች እርጉምነትን ወደነብስያቸው ያመጣሉ፡፡ እዚህ ነጥብ ላይ መንፈሳዊ ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የማያቋርጥ ሰላም ማጣት ውስጥ ይኖራሉ፡፡

ምክንያቱን ከማያውቁት ከዚህ ሰላም ማጣት በተጨማሪ ዕረፍት ማጣት፣ ጥርጣሬና ፍርሃት ይሰማቸዋል፡፡ የዚህ ሁሉ ፍርሃት ምንጭ ከአላህ (ሱ.ወ) መራቃቸውና ሁሉም ነገሮች በእሱ ቁጥጥር ሥር መሆናቸውን አለመረዳታቸው ነው፡፡ ሁኔታዎች በነሱ ቅጥጥር ሥር ያሉ ስለሚመስላቸው እያንዳንዱን የሕይወታቸውን ውጣ ውረድ ማስላት ያለባቸው ይመስላቸዋል፡፡

ልክ እንደ ከሀዲያን ሙናፊቆችም እንዴት እንደሚኖሩ፣ ሌሎችን እንዴት ማስደሰት እንደሚቻል፣ ጥሩ ጤንነትን በመጠበቅ እንዴት እራስን ከበሽታ ማዳን ይቻላል በሚሉ ዓለማዊ ጉዳዮች የተጠመዱ ናቸው፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ይህ የጉዳዩ መጨረሻ አይደለም፡፡ ሁኔታዎች እነሱ በፈለጉት መንገድ እየሄዱ እንዳልሆነ ሲመለከቱ ይሸበራሉ፡፡ እናም የዚህች ዓለም ነገሮችን ይበልጥ ማሳደድ ይጀምራሉ፡፡ ይህ ጉዳይ እስኪሞት ድረስ ይቀጥላል፡፡

ለአላህ (ሱ.ወ) ስለማያድሩና ጉዳያቸውን ለአላህ (ሱ.ወ) ስለማይሰጡ ቀጣይነት ባለው ጭንቀትና ዕረፍት ማጣት ውስጥ ይኖራሉ፡፡ የሥነ-ልቦና ሁኔታቸው በቁርአን ውስጥ በቀጣዮቹ ቃላት ተገልጿል፡፡

*ጩኸትን ሁሉ በነሱ ላይ ነው ብለው ያስባሉ፡፡ (አል-ሙናፊቁን፡4)*

ከዚህ በተጨማሪ እራሳቸውን ታዋቂ ለማድረግ መጣራቸውና ሌሎችን ለማስደሰት መጣራቸው ያልተመቻቸ ሁኔታቸውን ያብሰዋል፡፡ ምክንያቱም ሁሌም መጥፎ የሚሠሩትና እራሳቸውን በኃጢአት ያጨቀዩት ሙናፊቆች በአብዛኛው ሰዎች ዘንድ አይወደዱም፡፡ የአማኞችን ጥላቻ እንደሚያገኙት ሁሉ የሌሎችንም ጥላቻ ያገኛሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ለሌሎች ሰዎች የሚያስጠሉ አስመስሎ ያቀርባቸዋል፡፡ በዚህም ከሚያጋጥሟቸው የከፉ ጉዳቶች አንዱ የሆነውን ጉዳት በእነሱ ላይ ያደርሳል፡፡ ይህም አለመወደድ ነው፡፡ እናም በዚህ ዓለምም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ብቸኛና ጓደኛ አልባ ያደርጋቸዋል፡፡

እነዚህ ሰዎች አላህ (ሱ.ወ) እንደማይወዳቸው ሁሉ በሌሎች ዘንድም የተጠሉ ናቸው፡፡ ምንም ክብር ባይኖራቸውም ከፍተኛ ክብር እንዳላቸው ለማሳየት ይሞክራሉ፡፡ እናም እጅግ የተዋረደ ደረጃ ላይ ይወድቃሉ፡፡ በእነሱ ዙሪያ ባሉ ሰዎች በመናቅ በፍጹም እውነተኛ ክብርን አያገኙም፡፡ ለሐሳባቸውም ምንም ዋጋ አይሰጣቸውም፡፡ በዚህችና በቀጣዩ ዓለም መዋረዳቸው በቁርአን ውስጥ ተጠቅሷል፡፡

*ለነርሱ በቅርቢቱ ዓለም ውርደት አላቸው፤ ለነርሱም በመጨረሻይቱ አገር ታላቅ ቅጣት አላቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡114)*

*በመጽሐፉ ከፊል ታምናላችሁን? በከፊሉም ትክዳላችሁን? ከናንተም ይህንን የሚሠራ ሰው ቅጣት በቅርቢቱ ሕይወት ውርደት እንጂ ሌላ አይደለም፤ በትንሳኤ ቀንም ወደ ብርቱ ቅጣት ይመለሳሉ፤ አላህም ከምትሠሩት ሥራ ሁሉ ዘንጊ አይደለም፡፡ (ሱረህ አል-በቀራህ፡85)*

## (4) በስተመጨረሻ ምሕረት የሚደረግላቸው ይመስላቸዋል

*የዚህን የቅርቡን ጠፊ ጥቅም ይይዛሉ፤ ብጤውም ጥቅም ቢመጣላቸው የሚይዙት ሲሆኑ (በሠራነው) ለኛ ምሕረት ይደረግልናል ይላሉ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል አዕራፍ፡169)*

ውስጣቸው በሚገኘው የራስ መብቃቃት ምክንያት ሙናፊቆች አላህ (ሱ.ወ) ለእነሱ ትልቅ ውዴታ ያለው ይመስላቸዋል፡፡ እናም ያለጥርጥር ጥሩ ነገሮችን የሚሰጣቸው ይመስላቸዋል፡፡ ሁሉም ሰይጣናዊ ተግባሮቻቸው በጥሩ ሐሳብ የተሠሩ ይመስላቸዋል፡፡

ከላይ በቁርአን አንቀጹ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ባህሪን ያሳያሉ፡፡ "መጥፎን ብንሠራ መሀርታን እናገኛለን" ይላሉ፡፡ ይህ የመነጨው አላህን ካለማወቃቸው ወይም የእሱን ፍትሕ ካለመረዳታቸው ነው፡፡

ሆኖም አላህ (ሱ.ወ) እርሱ መጥፎ የሠራን የሚቀጣ ነው፡፡ በዚህች ዓለም ላይ በሠሩት ሥራ ምክንያት ሙናፊቆች በቀጣዩ ዓለም ይከፋሉ፡፡ ከአማኝ ህብረተሰብ ጋር አማኝ መስለው በርካታ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ልባቸው ውስጥ ያለው በሽታ ምክንያት በዚህች ዓለም ላይ የሠሩት ሥራ ሁሉ ምንም እንደማይጠቅማቸው ያያሉ፡፡ ሆኖም በራስ መብቃቃታቸው በዚህች ዓለም ላይ ሳሉ ይህን ከማየት ያቅባቸዋል፡፡ በቀጣዩ ዓለም የሚኖራቸው ቦታ በቁርአን አንቀጾች በቀጣዮቹ ቃላት ተገልጸዋል፡-

*በሥራዎች በጣም ከሳሪዎቹን እንንገራቸውን? በላቸው፡፡ እነዚያ እነሱ ሥራን የሚያሳምሩ የሚመስላቸው ሲሆኑ በቅርቢቱ ሕይወት ሥራቸው የጠፋባቸው ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ከህፍ፡103-104)*

## (5) በራስ በመብቃቃተቸው ምክንያት የሚደርስባቸው አካላዊ ጉዳቶች

የሙናፊቆች ተግባር የሚያመጣውን ውጤት አጽንኦት ሰጥተንበታል፡፡ ይህ ጉዳት ያደርስብናል ብለው ከማሰብ ይልቅ የቁርአን አንቀጹ እንደሚነግረን ጥሩ ሥራ እየሠሩ ይመስላቸዋል፡፡ ወደ እነሱ በመጡ ማስጠንቀቂያዎችና ማስታወሻዎች ይደነቃሉ፡፡ ከእነሱ ጋር ያሉት አማኞች የተሳሳተ ባህሪይ እያሳዩ እንደሆነና ሙሉ ለሙሉ ታማኝ የሆኑ ሰዎችን ያለ አግባብ እያስጠነቀቁ መሆኑን ይረዳሉ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እና አማኞች የማያውቋቸው ይመስላቸዋል፡፡ ነገር ግን አማኞች፣ በተለየ ሁኔታ ደግሞ መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) በልባቸው ውስጥ ያለውን በሽታ በውጫዊ ገጽታቸውና በብልሹ አነጋገራቸው መረዳት ይችላሉ፡፡ በርግጥም መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ሙናፊቆችን መለየት እንደሚችሉ አላህ (ሱ.ወ) ገልጿል፡፡

*በሻንም ኖሮ እነሱን ባሳየንህና በምልክታቸውም በርግጥ ባወቅሃቸው ነበር፤ ንግግርንም በማሸሞራቸው በርግጥ ታውቃቸዋለህ፡፡ አላህም ሥራዎቻችሁን ያውቃል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ሙሐመድ፡30)*

ሆኖም ከመጀመሪያው ጀምሮ እንደገለጽነው የራስ መብቃቃት በሽታ ከፍተኛ ጉዳት ያደርስባቸዋል፡፡ ውስጣዊ ጨለማቸው፣ ብልጣ ብልጥ መንፈሳዊ ደረጃቸው በውጫዊ ገጽታቸው ላይ ተጽዕኖ አለው፡፡ ንፍቅናቸውን በተመለከተ ግልጽ የሆኑ ማረጋገጫዎች በንግግራቸውና በአካላዊ ገጽታቸው ላይ ይታያሉ፡፡ ሆኖም ከዚህ በፊት እንዳስቀመጥነው የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ብቻ ናቸው የተወሰኑ መለያዎችን መስቀመጥ የሚችሉት፡፡

በሳቸው ገለፃ ላይ ተመሥርተው በሱ ዙሪያ ያሉት አማኞች ውስጣዊ ጨለማቸው በውጫዊ ገጽታቸው እንዴት እንደሚጋለጥ ያያሉ፡፡ የአነጋገር ስልታቸውና የፊት ገጽታቸው ብልሹ የመሆኑ እውነታ፣ በፊታቸው ላይ የሚታየው ጭለማዊ ገጽታ፣ እጅግ ቀላል የሆኑ ጉዳዮችን መረዳት አለመቻላቸውና ጥበብ የሚያንሳቸው መሆኑ በሽታቸውን ከሚያመጡት ጉዳቶች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ነገር ግን በእነሱ ቁጥጥር ሥር ያሉ ጸጋዎች አንድ በአንድ እየተወገዱ መሆኑን ማየት አይችሉም፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ሁሉም ጥሩ እንደሆነ ያስባሉ፡፡ በርግጥም ለውጫዊ ገጽታቸው በአካላዊ አቋቋማቸው፣ በገጽታቸውና በአነጋገራቸው ላይ ያለውን ብልሽት መረዳት አይችሉም፡፡ ይህም በአላህ (ሱ.ወ) የሚቀጡት ቅጣትና የራሳቸው ወጥመዶች ወደ እራሳቸው እንዲመለሱ የሚያደርግ ወጥመድ ነው፡፡

## ሙናፊቆች በፍጹም መልዕክተኞችን ድል አልሙቱም

*እነዚያ በናንተ (የጊዜን መዘዋወር) የሚጠባበቁ ናቸው፤ ለናንተም ከአላህ የሆነ አሸናፊነት ቢኖራችሁ ከናንተ ጋር አልነበርንምን? ይላሉ፡፡ ለከሀዲዎችም ድል ቢኖር (ካሁን በፊት) በናንተ ላይ አልተሾምንምን? (እና አልተውናችሁምን?)፤ ከምእምናንም (ኢደጋ) አልከለከልናችሁምን? ይላሉ፡፡ አላህም በትንሳኤ ቀን በመካከላችሁ ይፈርዳል፤ አላህም ለከሀዲዎች በምእምናን ላይ መንገድን በፍጹም አያደርግም፡፡ (ሱረህ አን-ኒሳእ፡141)*

በታሪክ ሂደት ውስጥ ሙናፊቆች እውነት ላይ በማመጽ በአንቀጹ እንደተገለጸው አማኞች ውስጥ በመሆን ጦርነት አውጀውባቸዋል፡፡

*ወደ መዲና ብንመለስ አሸናፊው ወራዳውን በርግጥ ከርሷ ያወጣል ይላሉ፤ አሸናፊነትም ለአላህ፣ ለመልዕክተኛውና ለምእምናን ነው፡፡ ግን መናፍቃን አያውቁም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙናፊቁን፡8)*

ሙናፊቆች ሁሌም ከአማኞች የበላይ እንደሆኑና እንደሚያሸንፏቸው ገልጸዋል፡፡ ምንም እንኳን እነዚህን ሁሉ መሠረት የለሽ ንግግሮች ቢናገሩም አማኞችን በፍጹም ድል መምታት አልቻሉም፡፡ በነሱ ዙሪያ ያሉ አማኞችና መልዕክተኛው ሁሌም ድልን አግኝተዋል፡፡ ይህ ሁኔታ በታሪክ ውስጥ እንደ ሕግ ቆይቷል፡፡

ሁኔታዎች ከቁርአን አንፃር ሲታዩ የዚህን ምክንያት ማየቱ ቀላል ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በፍጹም መናፍቃን በምእመናን እንዲጠቁ አይፈቅድም፡፡ ከዚህ በተቃራኒ በመልዕክተኛውና አማኞች እንዲሸነፉ ያደርጋቸዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ)

በቁርአን ውስጥ አማኞች ላይ ያነጣጠሩ ተግባራት ላይ የሚሳተፉ ሙናፊቆችን አጠቃሎ ሁሉንም ከህዲያን ከብልጣ ብልጥ እንቅስቃሴያቸው ካልታቀቡ እንደሚቀጣቸው አስጠንቅቋል፡፡

*መናፍቃንና እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ያለባቸው፣ በመዲናም ውስጥ (በወሬ) አሸባሪዎቹ (ከዚህ ሥራቸው) ባይከለከሉ በነርሱ ላይ በርግጥ እንቀሰቅስሃለን፤ ከዚያም በርሷ ውስጥ ጥቂትን እንጂ አይጎራበቱህም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አሕዛብ፡60)*

አላህ (ሱ.ወ) በከህዲያን ላይ በሚሠሩት ሥራ በሙሉ ወደእሱ የሚመለሱትንና ከልብ ያመኑትን እንደሚረዳ በምሳሌ ገልጿል፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) እርዳታና ድጋፍ መልዕክተኞቹ (ዐ.ሰ) እጅግ በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ላይ እንኳን ሁሌም ድልን ተጎናጽፈዋል፡፡

ይህ በቁርአን ውስጥ በበርካታ ምሳሌዎች ተጠቅሷል፡፡ ከነዚህ አንዱ በነብዩ ዳውድ (ዐ.ሰ) ጊዜ በከህዲያን ላይ በተደረገ ጦርነት የወታደሮች መሪ የነበረው ጧሉት ነው፡፡ ባሉት የላቁ የውትድርና ችሎታዎች መሪ የሆነው ጧሉት በርካታ መሳሳቢያዎችን ለጦሩ ሰጠ፡፡ ነገር ግን እምነታቸው ደካማ የሆኑ በርካታ ሰዎች መታዘዝ ቢኖርባቸውም ለምክሩ ጀርባቸውን በመስጠት በእራሳቸው ፍላጎት መሠረት ተጓዙ፡፡

*ጧሉትም በሠራዊቱ (ታጅቦ) በወጣ ጊዜ – አላህ በወንዝ (ውኃ) ፈታኛችሁ ነው፣ ከርሱም የጠጣ ሰው ከእኔ አይደለም፤ ያልቀመሰውም ሰው በእጁ መዝገንን የዘገነ ሰው ብቻ ሲቀር፣ እርሱ ከኔ ነው አለ፤ ከነርሱም ጥቂቶች ሲቀሩ ከርሱ ጠጡ፤ እርሱና እነዚያም ከርሱ ጋር ያመኑት (ወንዙን) ባለፉት ጊዜ – ጃሎትንና ሠራዊቱን በመዋጋት ለኛ ዛሬ ችሎታ የለንም አሉት፤ እነዚያ እነርሱ አላህን ተገናኝዎች መሆናቸውን የሚያረጋግጡት – ከጥቂት ጭፍራ በአላህ ፈቃድ ብዙን ጭፍራ ያሸነፈች ብዙ ናት፤ አላህም ከታጋሾች ጋር ነው አሉ፡፡ (ሱረህ አል-በቀራህ፡249)*

ምንም እንኳን አማኞች ጥቂትን እንኳን አለመታዘዝን ሳያሳዩ በጦርነቱ መልዕክተኛውን ቢደግፉም በጦርነቱ ጊዜ ሙናፊቆች በድንገተኛ እምቢተኛነት አማኞች ላይ ጉዳት ማድረስ ይፈልጋሉ፡፡

*ለጃሎትና ለሠራዊቱ በተሰለፉ ጊዜ – ጌታችን ሆይ! በኛ ላይ ትዕግስትን አንቧቧ፤ ጫማዎቻችንንም አደላድል፤ በከህዲያን ሕዝቦችም ላይ እርዳን አሉ፡፡ በአላም ፈቃድ ድል መቷቸው፤ ዳውድም ጃሉትን ገደለ፤ ንግሥንንና ጥበብንም አላህ ሰጠው፤ (ሱረህ አል-በቀራህ፡250-251)*

ከልብ ባላቸው እጅ መስጠትና ቆራጥነት ምላሽ አላህ (ሱ.ወ) ለአማኞች በከሀዲያን ላይ ድልን ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህች ዓለም ላይ ታላቅ ድልን ይቀዳጃሉ፡፡ እንዲሁም በቀጣዩ ዓለም የአላህን ጀነትና ተቀባይነት ያገኛሉ፡፡ ከሀዲያን በእሱ ተረግመው ይቀጣሉ፡፡

## በሙናፊቆች ላይ ሊኖረን የሚገባ አቋም

*አንተ ነብዩ ሆይ! ከሀዲዎችንና መናፍቃንን ታገል፤ በነርሱም ላይ በርታ፤ መኖሪያቸውም ገሀነም ናት፤ ምን ትከፋም መመለሻ! (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተሕሪም፡9)*

ሙናፊቆች ላይ መያዝ ያለበት አቋም በቁርአን ውስጥ ከፍተኛ አትኩሮት ተሰጥቶታል፡፡ አንድ አማኝ የሚፈልገውን ሁሉ ከቁርአን እንደሚማር ሁሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ዓይነት ባህሪይ ማሳየት እንዳለበትም ከቁርአን ይማራል፡፡ በቁርአን ውስጥ ለአማኞች የተሰጣቸው ተምሳሌታዊ ምክር ይህ ነው፡፡ አማኞች ሙናፊቆችን እንደ ጓደኛ መያዝ የለባቸውም፡፡ እንዲሁም ሁለቱ አብረው ከቆዩ ሙናፊቆችን በቁርአን ማስጠንቀቅ ይገባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሰጧቸው ምክር ውጤት አልባ ከሆነ ሙናፊቆችን ከውስጣቸው ማስወጣት አለባቸው፡፡ እዚህ ነጥብ ላይ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው በሙናፊቆች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ መወሰን ያለባቸው፡፡ በመልዕክተኛው አማካኝነት አላህ (ሱ.ወ) አማኞችን ትክክለኛውን ውሳኔ እንዲወስኑ ያስችላቸዋል፡፡ እስቲ አሁን በሙናፊቆች ላይ መያዝ ያለበትን አቋም የሚጠቁሙ አንቀጾችን እንይ፡፡

### (1) ለነሱ ምስጢርን አለማዋየት

*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህ በነሱ ላይ የተቆጣባቸውን ሕዝቦች አትወዳጁ፤ ከሀዲዎች ከመቃብር ሰዎች ተስፋ እንደቆረጡ ከመጨረሻይቱ ዓለም (ምንዳ) በርግጥ ተስፋ ቆርጠዋል፡፡ (ሱረህ አል-ሙምተሒናህ፡13)*

በቁርአን አንቀጾች ነጸብራቅ ከመጀመሪያው እንደተመለከትነው ሙናፊቆች አንድ ሰው እንደ ጓደኛም ሆነ እንደ ምስጢረኛ ሊይዛቸው የማይገቡ ሰዎች ናቸው፡፡ እምነታቸው ደካማ የሆኑና በልባቸው ውስጥ እምነት ያልተገነባባቸው

ሰዎች ብቻ ናቸው አላህን ከመወዳጀት የራቁትን፣ በዚህም ምክንያት እሱ ያራቃቸውን ሰዎች እንደ ምስጢረኛ የሚይዙት፡፡

በዚህ ርዕስ ላይ በአላህ (ሱ.ወ) የወረዱ የቁርአን አንቀጾች አማኞች ከሙናፊቆች ሁልጊዜም እራሳቸውን እንዲጠብቁና በፍጹም እንደ ምስጢር ጓደኛ እንዳይዟቸው ያዛል፡፡ አማኞችን ከሚጠሉትና በመበታተን አደጋ ውስጥ እንዲወድቁ ከሚመኙት ሙናፊቆች እራስን መጠበቅ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

## (2) እነርሱን በፍትሕ ማስተዳደር

*ቢመጡህም በመካከላቸው ፍረድ፤ ወይም ተዋቸው፤ ብትተዋቸውም ምንም አይጎዱህም፤ ብትፈርድም በመካከላቸው በትክክል ፍረድ፤ አላህ በትክክል ፈራጆችን ይወዳልና፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ማኢዳህ፡42)*

ከላይ የተጠቀሰውን አንቀጽ ትዕዛዝ ተግባራዊ በማድረግ ሰዎችን መምራት መልዕክተኛውን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ መልዕክተኛው ሙናፊቆች እንደፈለጉት ይመሯቸዋል አልያም ጀርባቸውን ይሰጧቸዋል፡፡

## (3) ምክርን የሚቀበሉ ከሆነ መምከር

*እነዚህ እነዚያ አላህ በልቦቻቸው ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያውቅባቸው ናቸው፡፡ እነርሱንም ተዋቸው፡፡ ገሥፃቸውም፤ ለነርሱም በነፍሶቻቸው ውስጥ ስሜት ያለውን (የሚያጭር) ቃል ተናገራቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡63)*

ከዚህ አንቀጽ መረዳት እንደሚቻለው ሙናፊቆች ጥሩ ምክር ሊሰጣቸው እንደሚገባ ተጠቁሟል፡፡ በዚህ ጠቃሚና ውጤታማ ዘዴ የሠሩትን ሊያዩና ሊቆጩ ይችላሉ፡፡ እዚህ ጋ ዋናው ነጥብ ቁጭት እንዲሰማቸው የሚያስደርግ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ላይ ነው፡፡ ይህን የመሰለ ምክርን የማይቀ በል ሰው በሃይማኖት የሥነ-ምግባር እሴቶች ላይ ግልጽ ጦርነት አውጇል፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው እነዚህ ሰዎችን ከራሱ ሊያርቅ እንጂ ጓደኛ ሊያደርጋቸው እንደማይገባ በፍጹም መርሳት የለበትም፡፡ አማኞች እነዚህ ሰዎች እራሳቸውን ይለውጣሉ በሚል ተስፋ ምክር ይሰጧቸዋል፡፡ ነገር ግን ለእያንዳንዱ ምክር ጀርባቸውን ለሚሰጡት ሙናፊቆች የቀጣዩን ዓለም ስቃይ ያበረታዋል፡፡

ሁሉም ለሙናፊቆች የሚሰጡት ምክሮች በአላህ (ሱ.ወ) የተዘጋጀላቸው ወጥመድ ናቸው፡፡ ከአማኞች መሃል በመሆንና በምስጢር በመሥራት በቀጣዩ ዓለም በአማኞች መካከል እያሉ ለእያንዳንዱ ለተሰጣቸው ምክር ቅጣት እንዳለባቸው ባለመረዳት ሙናፊቆች እጅግ ጎበዝ የሆኑ ይመስላቸዋል፡፡ በዚህም ሁኔታ በአማኞች

ላይ መጥመድ ለማዘጋጀት ሲሞክሩ መጨረሻ በሌለው ወጥመድ ውስጥ ይወድቃሉ፡፡

## (4) ምክር የማይቀበሉ ከሆነ በማስጠንቀቁ ላይ ችክ አለማለት

በጥሩ ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል የእያንዳንዱ አማኝ ኃላፊነት ነው፡፡ ሆኖም ይህ ገደብ አለው፡፡ ምክር የሚሰጠው ሰው ችክ ብሎ ምክሩን አልቀበልም ካለ ተጨማሪ ነገር ሊነገረው እንደማይገባ አላህ (ሱ.ወ) ገልጿል፡፡

*የምትሰጠው ትምህርት ሊጠቅም ከሚችልበት ቦታ ላይ አስተምር፡፡ የሚፈራ በርግጥ ይገሰፃል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-አዕላ፡9-11)*

ሙናፊቆች በአከራሪው ከህደታቸው በሚቀጥሉበት ጊዜ ተጨማሪ ማስጠንቀቂያዎች ምንም ጥቅም የላቸውም፡፡ ስለዚህ አማኞች እነርሱን ለራሳቸው መተው አለባቸው፡፡

## (5) በከባድና በራቀ ሁኔታ መዋጋት

*አንተ ነብይ ሆይ! ከሀዲያንን እና መናፍቃንን ታገል፡፡ ብርቱ ሁንባቸውም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡73)*

ይህ ከአላህ (ሱ.ወ) የተሰጠ እጅግ በጣም ጠቃሚ ምክር ነው፡፡ ለነዚያ ለአላህ (ሱ.ወ) ቃላቸውን ለማይጠብቁ፣ በሚዋሹና በልባቸው ውስጥ ብልሽትና አመጽን በያዙ ሙናፊቆች ላይ የአማኞች ኃይለኛና ቆራጥነት የተሞላበት አቀራረብ በነርሱ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው፡፡ እነርሱ ከሚፈጥሩት ሁከት ራስን መጠበቅ፣ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግና ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት በሰላ ጊዜ እነሱን መለየት የአማኞች ወሳኝ ኃላፊነቶች ናቸው፡፡ አማኞች ከሙናፊቆች አደጋ ሁሌም እራሳቸውን እንዲጠብቁ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡ እነዚህን በልባቸው ውስጥ በሽታ ያለባቸውን ሰዎች ማጋለጥና ሌሎችም እንዲያስወግዱዋቸው ማድረግ የአማኞች ሥራ ነው፡፡ ሁሉን ተገቢ ቅድመ ጥንቃቄዎችን በማድረግ ሁከትን እንዲፈጥሩ አለመፍቀድ ለሌሎች የሙናፊቆች ትውልድ ማስጠንቀቂያ ነው፡፡

## (6) ከአማኞች ጋር አብረው እንዲታገሉ አለመፍቀድ

ሙናፊቆች መጀመሪያውኑ ከአማኞች ጋር አብረው አይታገሉም፡፡ የዚህም ምክንያት አላህን መፍራት እንደሚገባቸው ስለማይፈሩት፣ ለዓለማዊ ጥቅሞች ስላደሩና ከህዲያንን እጅግ በጣም ስለሚያደንቁ ነው፡፡ ወደኋላ በመቅረት ከአማኞች

የተለየ ሕይወትን ስለመረጡ አላህ (ሱ.ወ) ሙናፊቆች ከአማኞች ጋር መታገልን በፍጹም እንዳይፈቅዱላቸው መልዕክተኛውን አዟል፡፡

*አላህ ወደነርሱ ከመለሰህና ከአንተ ጋር ለመዝመት ፈቃድ ከጠየቁህ "ከኔ ጋር መቼውንም ቢሆን አትዘምቱም፣ ጠላትንም ከኔ ጋር ሆናችሁ አትፋለሙም፣ መጀመሪያውኑ መቀመጥን መርጣችኋል፣ ከኋላ ከሚቀሩት ወገኖች ጋር ተቀመጡ" በላቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡83)*

## (7) ከአማኝ ህብረተሰብ ማስወገድ

*እርሱ (ሙሳ) እንዲህ አለ - ሳምራዊው ሆይ! ይህ ያደረክበት ምክንያት ምንድን ነው? አለ፡፡ "እነርሱ ያላዩትን አየሁ፣ ከመልዕክተኛው ዱካም ጭብጥ አፈር ዘገንኩና ጣልኳት፣ ነፍሴ ይህንኑ ሸለመችልኝ" ሲል መለሰ፡፡ "ሂድ! የዚህች ዓለም ቅጣትህ "ማንም እንዳይነካኝ" ማለት ይሆናል፡፡ የማይጣስ ቀጠሮ አለህ፡፡ ስታመልከው የቆየኸውን ጌታህን ተመልከት፡፡ እናቃጥለዋለን፣ አመዱንም ባህር ውስጥ እንበትናለን" አለ፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ጧሃ 95-97)*

ነብዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) ህብረተሰብ ውስጥ ብልሽትን የፈጠረው ሳማራዊውን በተመለከተ የተያዘው ባህሪይ በሁሉም ሙናፊቆች ላይ የሚመከር እጅግ ውጤታማ ቅድመ ጥንቃቄ ነው፡፡ ምክንያቱም ሙናፊቆች አማኞች ውስጥ ብልሽትን በመፍጠር እራሳቸው ወደ ክህደት በተመለሱበት መንገድ እነሱን ወደ ክህደት ለመመለስ ይፈልጋሉ፡፡ ምንም እንኳን ይህን ባያሳኩም አማኞችን በሥነ-ልቦና ለማዳከም ይፈልጋሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ተገቢው ሥራ ከልብ ካመኑት አማኞች እነሱን ማስወገድ ነው፡፡

## 8. እነሱን አለመቀበል

*በመሆኑም ጥራ፡፡ እንደታዘዝከውም ጽና፡፡ የነርሱን ስሜትና ፍላጎት አትከተል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አሽ-ሹራ፡15)*

ሙናፊቅን መታዘዝም ሆነ ማክበር ከፍተኛ ጉዳትን ያደርሳል፡፡ አላህን የሚያስደስት ባህሪን በመተው ከሙናፊቆች ጋር የሚጓዝ ሰው የሰይጣንን መንገድ እየተከተለ ነው፡፡ ሙናፊቆች ከሰይጣን ጋር የሚጓዙ የርሱ ወታደሮች ናቸው፡፡ እናም በፍጹም በዚህች ዓለምም ሆነ በቀጣዩ ዓለም መድህንን አያገኙም፡፡ በዚህም ምክንያት አላህ (ሱ.ወ) አማኞችን ከዚህ አደጋ በማስጠንቀቅ ከሙናፊቆች ሐሳብ ጋር መስማማትን ከመሰሉ ባህሪያት ያስጠነቅቃቸዋል

## (9) ለሚያደርሱት ችግርና ጉዳት ትኩረት አለመስጠት

አላህ (ሱ.ወ) የአማኞች ጠባቂና ተከላካይ ነው፡፡ በችግርና በመከራ ጊዜ ከርሱ እርዳታን ይሻሉ፡፡ እንዲሁም ታጋሽና ለርሱ ያደሩ ናቸው፡፡ ከሙናፊቆች በሚመጡት ችግሮች ፊት ጀግንነትን በማሳየት ለአላህ (ሱ.ወ) ያድራሉ፡፡ ሙናፊቆች ለማድረስ የሚፈልጉት አደጋ በራሳቸው በሙናፊቆች ላይ እንዲደርስ ይጸልያሉ፡፡ የሙናፊቆች ሴራ ሁሉ ዋጋ ቢስና ውጤት አልባ ስለሆነ አላህ (ሱ.ወ) አማኞችን ለሙናፊቆች ተግባር ምንም ትኩረት እንዳይሰጡ ነግሯቸዋል፡፡

*ቃል ኪዳናቸውን በማፍረሳቸው ረገምናቸው፤ ልቦቻቸውንም ደረቆች አደረግን፡፡ የአላህንም ቃላት ከትክክለኛ ቦታዎች ይለውጣሉ፡፡ ከመልዕክት ከፊሉን ዘነጉ፡፡ ከጥቂቶቹ በስተቀር አብዛኞቹ ላይ የክህደት ምልክትን አሁንም ታያለህ፡፡ ይቀር በላቸው፡፡ ስህተታቸውንም እለፍ፡፡ አላህ መልካም ሠሪዎችን ይወዳልና፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ማኢዳህ፡13)*

*ይቅር በላቸው፤ ሰላም በልም፡፡ በቅርቡ ያውቃሉና፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አዝ-ዙኽሩፍ፡89)*

## (10) ከነሱ ጋር ምንም ዓይነት ጓደኝነትና ፍቅርን አለመመሥረት

ሙናፊቆች የሰይጣን ጓደኞች በመሆናቸው ሰይጣንን እንደተከላካይ ይዘውታል፡፡ ስለዚህ አንድ አማኝ ሰይጣንን ከራሱ እንደሚያርቀው ሁሉ ሙናፊቅንም ከራሱ ማራቅ አለበት፡፡ ሙናፊቆች የአላህ (ሱ.ወ) እና የዲኑ ጠላት ስለሆኑ አማኞች የነሱ ጠላቶች ናቸው፡፡ በልባቸው ውስጥም በሙናፊቆች ላይ ከፍተኛ ቁጣ አለባቸው፡፡ በርግጥም አላህ (ሱ.ወ) በዲን የሚዋጉዋቸውን ጓደኛ አድርገው እንዳይዙ አማኞችን አዟል፡፡

*አላህ የሚከለክላችሁ ከነዚያ በእምነታችሁ ሰበብ ከተዋጓችሁ፣ ከቤቶቻችሁም ካስወጧችሁ፣ እናንተን በማስወጣቱ ተግባር ሌሎችን ከረዱት ጋር እንዳትወዳጁ ነው፡፡ ከነርሱ ጋር የሚወዳጁ እነዚያ እነርሱ በዳዮች ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሙምተሒናህ፡9)*

## (11) እነሱን ማስወገድ

ሙናፊቆች በአማኞች መሃል ሲቆዩ ቀጣይነት ያለው ትግል ውስጥ ገብተዋል፡፡ ከአማኞች ህብረተሰብ ከተለዩ ይህን ተግባር ከሩቁ መሥራታቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ለአማኞች ደህንነትና የአዕምሮ ሰላም አንድ ሰው ሰይጣንን እንደሚያስወግደው ሁሉ ሙናፊቆችን ማስወገዱ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ እንዲሁም አንድ ሰው ከእሳት እንደሚርቀው ሁሉ ከሙናፊቆች መራቁ አስፈላጊ ነው፡፡

አማኖች ካስወገዱዋቸው ሙናፊቆች ምንም ጉዳት ሊያደርሱባቸው እንደማይችሉ አላህ (ሱ.ወ) ቃል ገብቷል፡፡

*መልካም ነገር ሲያገኛችሁ ይከፋቸዋል፡፡ ግና ክፉ ነገር ቢደርስባችሁ በርሱ በእጅጉ ይደሰታሉ፡፡ ከታገላችሁና አላህን ከፈራችሁ ተንኮላቸው ቅንጣት አይጎዳችሁም፡፡ አላህ የሚሠሩትን ሁሉ ተቆጣጣሪ ነውና፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ ኣል ዒምራን፡120)*

## ሙናፊቅ ተውበት ማድረግ ይችላልን?

አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን ላይ እንደገለጸው፡-

*ለአላህ ውሳኔ የተተው ሌሎች ወገኖችም አሉ፡፡ ወይ ይቀጣቸዋል፣ አሊያም ንስሀቸውን ይቀበላል፡፡ አላህ ዐዋቂም ጥበበኛም ነውና፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡106)*

*ብትክዱ አላህ ከናንተ የተብቃቃ ነው፡፡ ለባሮቹም ክህደትን አይወድም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አዝ-ዙመር፡7)*

በሌላ አባባል ባሮቹን ወደ እውነተኛው ጎዳና መምራት፣ ኃጢአታቸውን ይቅር ማለትና ጀነት ማስገባት ይፈልጋል፡፡ ነገር ግን ሙናፊቆች ለዚህ ጥሪ ጀርባቸውን መስጠታቸውን ይቀጥላሉ፡፡ እውነታውን ቢያውቁትም አንቀጾቹ ምንም ተጽዕኖ አያሳድሩባቸውም፡፡ እናም በጭካኔያቸው፣ በኩራታቸውና በክህደታቸው ይቀጥላሉ፡፡ ነገር ግን ከነሱ ውስጥ ጥቂቶቹ የዚህ ዓይነት ባህሪን ማስወገድ ይፈልጋሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ማንኛውም ንስሀ ለመግባት የፈለገ ሰው የርሱን ረዳት አልባነት ሙሉ ለሙሉ መረዳት አለበት፡፡ የአላህን ማርታ ከልቡ መለመን አለበት፡፡ እናም በፍጹም ወደ ንፍቅናው ላይመለስ ንስሀ መግባት አለበት፡፡

ፍጹም ከልቡ ከሆነ አላህ (ሱ.ወ) ከፈለገ የሙናፊቁን ንስሀ ሊቀበለው ይችላል፡፡ በርግጥም በቁርአን ተከታዩ ተነግሮናል፡፡

*ኃጢአት ከፈጸመ በኋላ ንስሀ የገባና ያስተካከለ አላህ ንስሀውን ይቀበለዋል፡፡ አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና፡፡ (ሱረህ አል-ማኢዳህ፡39)*

በርካታ የቁርአን አንቀጾች ስለሙናፊቆች ንስሀ ያወራሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የሠሩትን ኃጢአት አምነው የተቀበሉትንና ከልብ የሆነ ጥሩ ሥነ-ምግባርን ለመልዕክተኛው ማሳየት የፈለጉትን ንስሀቸውን ይቀበላል ተብሎ ተስፋ ሊደረግ ይችላል፡፡

*ኃጢአታቸው የተናዘዙ ሌሎች ወገኖችም አሉ፡፡ መልካም ሥራን ከክፉ ሥራ ቀላቅለዋል፡፡ አላህ ንስሀቸውን ይቀበላል፡፡ አላህ መሐሪም አዛኝም ነውና፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡102)*

አላህ (ሱ.ወ) ባለፉት ጊዜያት ይኖሩ የነበሩ ሙናፊቆች ጥቂቶቹ እንዴት ተውበት እንዳደረጉ ምሳሌ ሰጥቷል፡፡ በቁርአን አንቀጾች እንደተገለጸው የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ጥቂት አባላት ከውጊያ ለመቅረት ሁሉንም ዓይነት ምክንያቶችን ደረደሩ፡፡ እናም ከኋላ ለመቅረት የመልዕክተኛውን ፈቃድ ጠየቁ፡፡ ይህንም በመሥራታቸው በመደሰት የተጠቀሙ መሰላቸው፡፡ በነርሱ አስተሳሰብ የሞትን አደጋ አመለጡ፡፡ እናም በውጊያ ላይ ባለመሳተፍ በሕይወት መቆየታቸውን አረጋገጡ፡፡ ለማስወገድ የሚጥሩት ሞት በቤታቸው ውስጥ እንኳን ሆነው ሊያገኛቸው እንደሚችል አልተረዱም፡፡ እውነታው ግን ለረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ትዕዛዝ ያደሩ ቢሆንና ወደ ጦርነት ቢሄዱ ኖሮ ሞት ቢይዛቸው እንኳን መስዋዕት (ሸሂድ) በመሆን ጀነት የመግባት መብትን ያገኙ ነበር፡፡

ነገር ግን በቀጣዩ ዓለም ጥርጣሬ ስላለባቸው በጦርነት ሜዳ ላይ ሞትን እንደ ከፍተኛ ከስረት ይቆጥሩታል፡፡ ከቤተሰባቸው ጋር ወደኋላ መቅረት፣ እንዲሁም ንግድና ተመሳሳይ ሁኔታዎችን የተሻሉ ጠቃሚዎች አድርገው ቆጥረዋል፡፡ ቁርአን ከነዚህ ሰዎች መካከል ወደኋላ ለመቅረት ያሰቡ ሰዎችን ጠቅሷል፡፡ ልክ እንደ ሌሎች በጦርነት ላይ አልተሳተፉም፡፡ ከአማኞች ጋር አልተባበሩም፡፡ እንዲሁም አማኞችን በከሀዲያን ላይ አልረዱም፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሦስቱ ወደኋላ ከቀሩት ሌሎች ሰዎች ተለይተዋል፡፡ በቁርአን ውስጥ እንደወረደው እነዚህ ሰዎች ወደጦር ሜዳ ባለመሄዳቸው ተቆጭተው በራሳቸው አዝነው ነበር፡፡ የአላህን ማርታ ፈልገውም ከልባቸው ወደ አላህ (ሱ.ወ) ተመለሱ፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ተውበታቸውን ተቀበላቸው፡፡

ለምን ምሕረት ተደረገላቸው? ዋናው ምክንያት አላህን ከልባቸው በመፍራታቸው፣ ለፍላጎታቸው እሱን በመለመናቸውና መሀርታን ስለጠየቁ ነው፡፡ አንድ የቁርአን አንቀጽ ከልባቸው መመለሳቸውንና የተሰቃዩትን ድንገተኛ የሕሊና ቀውስ ያትታል፡፡

*የነዚያን እንዲዘገይ የተደረጉትንም ሦስት ሰዎች ምድር ሰፊ ከመሆኗ ጋር የጠበበች እስከትመስላቸው ድረስ፡፡ ነፍሳቸውም እጅግ ተጨነቀች፡፡ ከአላህ እንደሚያመልጡ፣ ከርሱ ሌላም መጠጊያ እንደሌላቸው አወቁ፡፡ ከዚያም ንስሀ ይገቡ ዘንድ ለማበረታታት ንስሀቸውን ተቀበለ፡፡ አላህ ንስሀን ተቀባይ፣ አዛኝ ነውና፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡118)*

ከዚህ በተጨማሪ አላህ (ሱ.ወ) የሙናፊቆችን መቶበት ለራሳቸው መልካም እንደሆነ ገልጿል፡፡ ይህ በነሱ ላይ የተቸረ ታላቅ ጸጋ ነው፡፡ በቀጣዩ የቁርአን አንቀጽ እንደተገለጸው እሱ ከፈለገ እርጉም ቢሆኑም ኃጢአታቸውን ሊምር ይችላል፡፡

*ንስሀ ቢገቡ ለነርሱ መልካም ይሆናል፡፡ ግና ከሸሹ አላህ በዚህችም በመጭውም ዓለም አሳማሚ ቅጣት ይቀጣቸዋል፡፡ ምድር ላይ ወዳጅም ሆነ ረዳት የላቸውም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡74)*

አብዛኛውን ጊዜ ሙናፊቆች ሁሉንም መጥፎ ነገሮች በመሥራት በእርጅና ጊዜያቸው ወይንም መሞታቸው መሆኑን ሲረዱ ንስሀ የሚገቡ ይመስላቸዋል፡፡ ነገር ግን አላህ (ሱ.ወ) መሞታቸውን ሲያውቁ የሚያደርጉትን ማንኛውንም ንስሀ አይቀበልም፡፡

*እነዚያ ሞት እስኪመጣባቸው ድረስ ኃጢአት የሚሠሩና "እኔ አሁን ንስሀን ገብቻለሁ" የሚሉ ወገኖች፣ እነዚያም ከሀዲያን ሆነው የሞቱት ንስሀቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ ለእነኚህ አሳማሚ ቅጣት አዘጋጅተናል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡18)*

ተቀባይነት ያለው ንስሀ በቁርአን ውስጥ በቀጣዮቹ ቃላት ተገልጿል፡፡

*አላህ የሚቀበለው የነዚያን ኃጢአትን ባለማወቅ የሚሠሩትንና ወዲያውኑም ንስሀ የሚገቡትን ሰዎች ንስሀ ነው፡፡ አላህ የእንዲህ ዓይነት ሰዎችን ንስሀ ይቀበላል፡፡ አላህ ዐዋቂ፣ ጥበበኛ ነውና፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡17)*

## ሙናፊቆች በቀጣዩ ዓለም የሚኖራቸው ገጽታ

*እነሆ አላህንና መልዕክተኛውን የሚቃወም የገሀነም እሳት እንደተዘጋጀለት፣ ከውስጡም ዘወትር እንደሚኖር፣ ይህም ከባድ ውርደት መሆኑን አላወቁምን? (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡63)*

በአላህ (ሱ.ወ) እና በርሱ ዲን ላይ ጦርነት ያወጁት ሙናፊቆች የሚቀጡት ቅጣት በትክክል የሚገባቸውን ነው፡፡ ሙናፊቆች በሕይወታቸው ውስጥ አካላዊና መንፈሳዊ ስቃይን ይሰቃያሉ፡፡ የሙናፊቆች ቀላሉ ቅጣት በዚህች ዓለም ላይ ሳሉ ይጀምራል፡፡ ከከፍተኛ ንቀትና የበታችነት በተጨማሪ በመሬት ላይ እየኖሩ ሳለ በርካታ ሌሎች ዓይነት ቅጣቶች ይጠብቋቸዋል፡፡ ያለ ጥርጥር ታላቁ ስቃይ ጀሀነም ነው - ማለቂያ የለሽ፣ ለዘላለም አቃጣይ እሳት፡፡

## የሞታቸው ጊዜ

ሁሉም ሰዎች በአላህ (ሱ.ወ) የተወሰነላቸውን ዕጣ ፋንታ ይኖራሉ፡፡ እናም አላህ (ሱ.ወ) በወሰነላቸው ሰዓት ይሞታሉ፡፡ በአላህ (ሱ.ወ) ፍላጎት የሚኖሩ የአማኞች ነብስ በመላኢኮች ከአላህ (ሱ.ወ) በሆነ ጸጋ ቀስ ተደርጋ ትወሰዳለች፡፡ እናም በጀነት መልካም አቀባበል ይደረግላታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይህን ብስራት በቁርአን ውስጥ ለአማኞች ነግሯቸዋል፡፡

*እነዚያም በመልካም ሁኔታ ላይ ሆነው መላእክት "በናንተ ላይ ሰላም ይስፈን፤ ትሠሩት በነበረው መልካም ሥራ ጀነት ግቡ" እያሉ ነፍሳቸው የሚወስዷቸው ናቸው፡፡ (አል-ቁርአን፤ ሱረህ አን-ነሕል፡32)*

ሆኖም ይህ ለከሀዲያን አይሠራም፡፡ መላኢኮች ነፍሳቸውን በቀጥታ አይወስዱትም፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ልባቸውን፣ ፊታቸውንና ጀርባቸውን በመምታት ይወስዱታል፡፡ ከሚያጋጥማቸው አካላዊ ሕመም በተጨማሪ ይህ ለነሱ ከፍተኛ ማዋረጃ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ሁሉንም ሙናፊቆችና ከሀዲያን በዚህ ውርደትና ስቃይ አሸብሯል፡፡

*መላእክት ከሀዲያንን ፊቶቻቸውንና ጀርባዎቻቸውን እየመቱ፣ "አቃጣዩን ቅጣት ቅመሱ" እያሉ ሲገድሏቸው ብታይ ትዕይንቱ እጅግ ባስደነገጠ ነበር፡፡ (አል-ቁርአን፤ ሱረህ አል-አንፋል፡50)*

*መላእክት ነፍሶቻቸውን በሞት በሚወስዱባቸው፣ ፊቶቻቸውንና ጀርባዎቻቸውን በሚመቱዋቸው ጊዜ እንዴት ሊሆኑ ነው? (አል-ቁርአን፤ ሱረቱ ሙሐመድ፡27)*

መላኢኮች በዚህ መልኩ ነብሳቸውን ይዘው ሲሄዱ በዚህች ዓለም ላይ ሳሉ ለሠሩት ሥራ የሚሰጣቸውን ቅጣት ይረዳሉ፡፡ በምድር ላይ ለመያዝ እጅግ የደከሙለት ክብር በድንገት ይጠፋል፡፡ በውርደት ይሞታሉ፡፡ በኋላም ወደ ጀሀነም ይወረወራሉ፡፡

*ለነዚያ ለካዱት ሰዎች "በቅርብ ጊዜ ትሸነፋላችሁ፣ ወደ ገሀነምም ትሰበሰባላችሁ" በላቸው፡፡ ገሀነም እጅግ አስከፊ ማረፊያ ናት፡፡ (አል-ቁርአን፤ ሱረህ ኣል ዒምራን፡12)*

*እነዚያ የካዱት ገንዘቦቻቸውን ሰዎችን ከአላህ መንገድ ለማገድ ያውላሉ፡፡ ሃብታቸውን ለዚህ እኩይ ተግባር ማዋላቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ግና የሚተርፋቸው ቁጭት ብቻ ይሆናል፡፡ በመጨረሻም ይሸነፋሉ፡፡ ከሀዲያን ወደ ገሀነም ይሰበሰባሉ፡፡ (አል-ቁርአን፤ ሱረህ አል-አንፋል፡36)*

*እነዚያ በፊቶቻቸው ወደ ጀሀነም የሚነዱት፣ ፍፃሜያቸው እጅግ አስከፊ ማረፊያ፣ የሚከተሉት መንገድም ከእውነት በእጅጉ የራቀ ነው፡፡ (አል-ቁርአን፤ ሱረህ አል-ፉርቃን፡34)*

# የጀሀነም ቅጣት

## (1) የከፋ ቅጣት

አላህ (ሱ.ወ) በቁርአን ውስጥ ከዚህ የበሳ ይገባቸዋል ብሎ የገለፃቸው ሙናፊቆች በቀጣዩ ዓለም ከባድ ቅጣት ይቀጣሉ፡፡ በሌላ አባባል በጀሀነም ቅጣት ይቀጣሉ፡፡

*የምታምኑት በመጽሐፉ ከፊል አስተምህሮ ብቻ ነውን? ቀሪውን አትቀበሉምን? ከመካከላችሁ ይህን የሚፈጽሙ ወገኖች የሚጠብቃቸው ቅጣት በዚህ ዓለምም ውርደት እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ በቀጣዩ ዓለም ለአስከፊ ቅጣት ይዳረጋሉ፡፡ አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ዘንጊ አይደለም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-በቀራህ፡85)*

## (2) የማያቋርጥ ቅጣት

*እነዚህ እነዚያ የዚህችን ዓለም ሕይወት በመጭው ዓለም የለወጡ ናቸው፡፡ ቅጣቱ አይቀልላቸውም፡፡ አይረዱምም፡፡ (ሱረህ አል-በቀራህ፡86)*

ሙናፊቆች ጀሀነም ውስጥ ለዘላለም ይቆያሉ፡፡ እናም ስቃያቸው በምንም መልኩ አይቀንስም፡፡

## (3) ኃይለኛ ቅጣት

*(ሙሐመድ ሆይ!) ለመናፍቃን አሳማሚ ቅጣት እንደተዘጋጀላቸው ብስራት ንገር፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡138)*

እንደ ቁርአን አገላለጽ የጀሀነም ቅጣት እጅግ አደገኛና ከባድ ነው፡፡ እዚያ ያለ ሰው ሁሉ ወደ እሳት ይወርዳል፡፡ ማምለጥ አይቻልም፡፡ በሰንሰለትና በብረት አጥር ይታጠራሉ፡፡ በብረት ጅራፍ ይገረፋሉ፡፡ ብቸኛ ምግባቸው የፈላ ውኃ፣ ምግል፣ የዘቅ-ቁም ዛፍና እሾክ ሲሆን ሙናፊቆች ከጀሀነም መውጣት ይፈልጋሉ፡፡ ሆኖም ስቃያቸው አያልቅም ወይም አይቀንስም፡፡

የዚህ ምክንያቱ እዚህ ዓለም ላይ አላህ (ሱ.ወ) የሚፈለግባቸውን ነገሮች በሙሉ ቢያውቁም በአላህ (ሱ.ወ) እና በዲኑ ላይ ጠርነት አውጀው ዓለማዊ ጥቅማቸውን በመከተል ጀርባቸውን ለእውነት ስለሰጡ ነው፡፡

## (4) እጅግ አዋራጅ ቅጣት

ጀሀነም ያሉ ሰዎች አስፈሪ ገጽታ ሲኖራቸው ሁሉንም ዓይነት ቅጣት ይቀምሳሉ፡፡ ሰውነታቸው በእሳት ይቆራረጣል፡፡ የፈላ ውኃ በጭንቅላታቸው ላይ ይደፋል፡፡ እንዲሁም ከሬንጅና ከእሳት የተሠሩ ልብሶችን እንዲለብሱ ይገደዳሉ፡፡

*ግና እነዚያ አንቀጾቻችን ለማፍረስ የጣሩ እጅግ አሳማሚ የሆነ አስከፊ ቅጣት ይጠብቃቸዋል፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ሰበእ፡5)*

## (5) የአላህ (ሱ.ወ) እርግማን

ከላይ እንደተመለከትነው ሙናፊቆች ጀሀነም ውስጥ በሁሉም አቅጣጫ ቅጣትን ይቀምሳሉ፡፡ ሆኖም ከነዚህ ሁሉ የበለጠ አንድ ቅጣት አለ፡፡ ይህም የአላህ (ሱ.ወ) እርግማን ነው – እነሱን ለማናገር አለመፈለጉና እነሱን ማዋረዱና ማንኳሰሱ ነው፡፡

*እነዚያ ሰዎች ቅጣታቸው በነርሱ ላይ የአላህ፣ የመላእክትና የሰዎች ሁሉ እርግማን መውረዱ ነው፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ ኣሊ ዒምራን፡87)*

*እነዚያ አላህ ከመጽሐፉ ውስጥ ያወረደውን የሚደብቁና በዚህች ጠፊ ዓለም ኢምነት ጥቅም የሚለውጡት ወገኖች ወደ ሆዳቸው የሚያስገቡት እሳትን እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ የትንሳኤ ዕለት አላህ ኢያናግራቸውም፡፡ ኢያጸዳቸውም፡፡ አሳሳሚ ቅጣት ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ (አል-በቀራህ፡174)*

## (6) ብቸኛ ይሆናሉ

በዚህ ዓለም ላይ እንደ ጓደኛ ይቆጥሯቸው የነበሩ ሰዎች በቀጣዩ ዓለም ከእነሱ እጅግ ይርቃሉ፡፡ እያንዳንዱ የራሱ ስቃይ ይኖረዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ጓደኛም ሆነ አጽናኝ አያገኙም፡፡ ሁሌም ብቸኛ ይሆናሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቀጣዩ ዓለም በዚህች ዓለም ላይ ቅርብ የሆኑ ጓደኞቻቸውን ይረግማሉ፡፡

*ለነርሱ ረዳት አታገኝላቸውም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡145)*

*ግና በመጭው ዓለም ከፊላችሁ ከፊሉን ያስተባብላል፤ ከፊላችሁ ከፊሉን ይረግማል። መኖሪያችሁም እሳት ይሆናል። ረዳቶችም አይኖሯችሁም አላቸው። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ዐንከቡት፡25)*

## (7) ከፍተኛ ክስረትን ይከስራሉ

*እነርሱ በመጭው ዓለም ከሳሪዎች መሆናቸው ቅንጣት የሚያጠራጥር አይደለም። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ነሕል፡109)*

እጅግ ውጤታማ ናት ብለው በሚያምኑባት በዚህች ምድር ላይ ኖረው ሲያበቁ በመሞት ወደ እውነተኛ ቤታቸው ጀሀነም ይገባሉ። እዚያ የነገሮችን እውነተኛ ገጽታ ያያሉ። እናም ማንኛውንም ጥቅም ከማግኘት ይልቅ ከፍተኛ ክስረትን እንደከሰሩ ይረዳሉ። በዚህች ዓለም ላይ የሠሩት እያንዳንዱ ነገር ትርጉም አልባ እንደነበርና ምንም ጥቅም ሊሰጣቸው እንደማይችል ይረዳሉ።

## የጀሀነም የታችኛው ደረጃ

*መናፍቃን ከእሳት የታችኛው አዘቅጥ ውስጥ በርግጥ ይሆናሉ። ለነርሱ ረዳት አታገኝላቸውም። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡145)*

አላህ (ሱ.ወ) ከላይ በጠቀሰው የቁርአን አንቀጽ ውስጥ እንደገለጸልን ሙናፊቆች የእሳት የታችኛው ክፍል ላይ ይኖራሉ። የዚህ ምክንያቱ ሁለት ፊት መሆናቸውና በሁከት ላይ የተመሠረተው የሥነ-ምግባር ተምሳሌታቸው ነው።

የሙናፊቆችን የብልጠት ተፈጥሮ የሚገልጹ በርካታ ፀባዮችን አይተናል። እነዚህን ጉድለቶች አንድ በአንድ የመጥቀሳችን ዋነኛ ምክንያት ሙናፊቆች እስካሁን ከኖሩት እጅግ ጨካኝ ከሆኑ ሰዎች እንደሚመደቡ ለማሳየትና ይህም ዕውቀት ለሁሉም እንዲደርስ ምክንያት ለመሆን ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ሙናፊቆች ጨካኝና አክራሪ እንደሆኑ የተገለጹት እነሱ ዕውቀት የተሰጣቸው ሰዎች ስለሆኑ ነው። በሌላ አባባል ስለሃይማኖታዊ የሥነ-ምግባር እሴቶች ተነግሯቸዋል። እንዲሁም እውነትን ከአማኞችና ከራሳቸው ከአላህ መልዕክተኛ ተምረዋል። በነዚህ ሃይማኖታዊ የሥነ-ምግባር እሴቶች ለጥቂት ጊዜያት ኖረዋል። ለአላህ (ሱ.ወ)፣ ለመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እና ለአማኞች ጀርባቸውን ሰጥተዋል። ይህም የሆነው ሕይወታችን ልክ እንደ ከሀዲያን ቀላል ይሆናል ብለው በማሰብ ነው። አላህ (ሱ.ወ) ይህን እውነታ እንደሚከተለው ይገልፃል፡-

*ከፉ ነገር እንዳልተናገሩ በአላህ ይምላሉ፡፡ ግና ለክህደት የሚያበቃን ቃል ተናግረዋል፡፡ እናም ኢስላምን ከተቀበሉ በኋላ ክደዋል፡፡ ሊፈጽሙት የማይቻላቸውን አቅደዋል፡፡ ለዚህ ብቀላ ያነሳሳቸው አላህ ከችሮታው፣ መልዕክተኛውም እነርሱን ለክብር በማብቃታቸው ብቻ ነው፡፡ ንስሀ ቢገቡ ለነርሱ መልካም ይሆናል፡፡ ግና ከሸሹ አላህ በዚህችም በመጭውም ዓለም አሳማሚ ቅጣት ይቀጣቸዋል፡፡ ምድር ላይ ወዳጅም ሆነ ረዳት የላቸውም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አት-ተውባህ፡74)*

ስለዚህ ከፍተኛ ኃላፊነትን ይሸከማሉ፡፡ እናም ዕውቀት ከሌላቸው ይለያሉ፡፡ በሌላ አባባል ወደ ሃይማኖታዊ የሥነ-ምግባር እሴቶች ካልተጠሩና በፍጹም የእስልምና ተከታይ ሆነው ከማያውቁ ሰዎች ይለያሉ፡፡ በቀጣዩ ዓለም የሚቀምሱት ቅጣት ከሌላው ይልቃል፡፡ በቁርአን እንደተገለጸው የዚህ ምክንያት ሙናፊቆች በአማኞች እንዲለዩ የሚያደርጓቸውን አጋላጭ ኃጢአቶች በግልጽ መፈጸምን በመተው ሃይማኖታዊ መምሰላቸው ነው፡፡ ሆኖም ለአላህ (ሱ.ወ) እና ለመልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ምንም ዓይነት ታዛዥነት የላቸውም፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ብልጣ ብልጥ ጥላቻና ጠላትነት አለባቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች በጀሀነም ውስጥ አስከፊ ቅጣት የሚገባቸው መሆኑ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ሙናፊቆች በአማኝ ህብረተሰብ ውስጥ እጅግ የላቀ የሥነ-ምግባር ተምሳሌትነትን አይተዋል፡፡ እጀግ በጣም ሰላማዊ በሆነ አካባቢ ኖረዋል፡፡ እንዲሁም ታላቅ ክብርንና ፍቅርን አግኝተዋል፡፡

ምንም እንኳን ከአማኞች መልካምነትንና በጎነትን እንጂ ሌላ ነገርን ባይመለከቱም በልባቸው ውስጥ ባለው በሽታ ምክንያት አሁንም በነሱ ላይ ጥላቻ ሊኖራቸው ችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚህች ዓለም ሕይወታቸው በአማኞች ላይ ትዕቢተኛና ኩራተኛ ስለሆኑ አላህ (ሱ.ወ) ያስንቃቸዋል፡፡ እንዲሁም ያዋርዳቸዋል፡፡ በአንድ ሐዲሥ የሙናፊቆች ደረጃ እንዲህ ተገልጿል፡-

*በቂያማ ቀን እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ የሚኖረው ሁለት ፊት ሰው ነው፡፡ (ሰሒሐል ቡኻሪና ሙስሊም)*

በዚህች ዓለም ላይ አማኞችን ለማታለል ይፈልጋሉ፡፡ ሆኖም በቀጣዩ ዓለም ለትንሽ እርዳታ እንኳን ሳይቀር አማኞችን ይጠይቋቸዋል፡፡ ነገር ግን አማኞች በዚህ አያግዙም፡፡ ለአላህ (ሱ.ወ) ገደብ የለሽ ፍትሕ ምስጋና ይግባውና ለዘላለም በርሱ ጸጋ ይኖራሉ፡፡

የተለያዩ የቁርአን አንቀጾች የሙናፊቆችን የጀሀነም ውስጥ የማያልቅ ለቅሶ ይናገራሉ፡፡

*የሴትና ወንድ መናፍቃን ለነዚያ ለአመኑት "ተመልከቱን፤ ከብርሃናችሁ እንዋስ" በሚሉበትም ቀን "ወደኋላችሁ ተመለሱ፤ ሌላ ብርሃን ፈልጉም" ይባላሉ። በመካከላቸውም በውስጠኛው በኩል ችሮታና እዝነት፣ በውጪው በኩል ደግሞ ቅጣት ያለበት ባለበር አጥር ይደረጋል። "አብረናችሁ አልነበርንምን?" በማለት ይጠሯቸዋል። "አዎ! ግና ነፍሶቻችሁን ወደ ጥፋት መራችሁ፤ ውድቀታችንንም ተመኛችሁ፤ እውነትንም ተጠራጠራችሁ፤ ከንቱ ምኞቶች አቄሉአችሁ – የአላህ ትዕዛዝ እስከመጣበት ዕለት ድረስ፤ አታላዩም በአላህ አታለላችሁ" ይሏቸዋል። ዛሬ ከናንተም ከነዚያ ከካዱትም ቤዛ አይያዝም። መኖሪያችሁ እሳት ናት። የቅርብ ወዳጃችሁም ትሆናለች። እጅግ አስከፊ መመለሻ! (ይባላሉ)። (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አል-ሐዲድ፡13-15)*

# ማጠቃለያ

ሙናፊቆች ለአላህ (ሱ.ወ) እጅ የመስጠትን ጭንብል አጥልቀው ከነርሱ ጋር በሚቆዩበት ጊዜ እነርሱን ለመጉዳት የሚፈልጉና ወደ አማኝ ህብረተሰብ የሚገቡ ሁለት ፊት ሰዎች ናቸው። ለከሀዲያን ምስጢር ይናገራሉ። እንዲሁም በአማኞች መካከል ያለውን አንድነትና ትብብር ማፍረስ ይፈልጋሉ። አብዛኞቹ ከአማኞች ጋር ይኖራሉ። ሆኖም ከነርሱ ጋር ከሚቆዩበት ጊዜ ምስጢራዊ ዓላማን በመያዝ ለራሳቸው ቁሳዊ ፍላጎት ይሠራሉ። ቆይተውም ሆነ ወዲያውኑ እነዚህ ሰዎች ከአማኞች ምንም ጥቅም እንደማያገኙ ሲረዱ ይህን ከነርሱ ለመለየት በቂ ምክንያት አድርገው ይወስዱታል።

ጥቂቶች አማኝ ህብረተሰብ ውስጥ ሲገቡ እምነት ነበራቸው። ሆኖም ሕሊናቸው ቀስ በቀስ በመጠውለጉ እራሳቸውን ለሰይጣን አሳልፈው ይሰጣሉ። ልባቸው ውስጥ ባለው በሽታ ምክንያት ሰይጣን ለቁርአን አንቀጾች ያላቸውን ታማኝነትና ስሜት ያዳከመዋል። ከዚያም የድንቁርና ሃይማኖት ውስጥ ወይም በሰይጣን የምስጢር ሃይማኖት ውስጥ ይገባሉ።

እነዚህ ሰዎች ሁኔታዎችን በቁርአን ነጸብራቅ መሠረት ከማየት ይልቅ ከሃይማኖት የሞራል እሴቶች ከማይኖር ህብረተሰብ አተያየት አንፃር ያዩታል። የዚህ ግልጹ ምሳሌ የሚከሰተው በችግር ጊዜ ነው። ቁርአን በአላህ (ሱ.ወ) መወከልንና በችግር ጊዜ ተስፋ አለመቁረጥን ሲያስተምር በእንደዚህ ዓይነት ጊዜ ሙናፊቆች ከደንቆሮ ህብረተሰብ ጋር ተመሳሳይነትን ያሳያሉ። ሚዛናዊ ያልሆነ ጸባያቸውን ሁሉም እንዲያየው በማጋለጥ ወይ ይቆጣሉ አሊያም ይሸበራሉ።

እስካሁን የገለጽናቸው ባህሪያት በዚህም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ሙናፊቆች የሚኖራቸውን ደረጃ ይገልጹልናል፡፡ እንዲሁም ገጽታቸውንና አጠቃላይ መንፈሳዊ ሁኔታቸውን ያሳውቁናል፡፡ የሙናፊቆች ሁኔታ በቁርአን አንቀጾች በደንብ ተገልጿል፡፡ እነዚህ አላህን እንደሚገባው መፍራት የማይችሉ ሰዎች በዚህች ዓለም ላይ በአማኞች ላይ የማያቋርጥ ትግልን ያደርጋሉ፡፡ ይህን እንደ ግዴታ ተግባራዊ የሚያደርጉ ሲሆን ይህን ጸባያቸውንም በከፍተኛ ድርቀት ይዘው ይቆያሉ፡፡ ይህ የነርሱ ተፈጥሮአዊ ጸባያቸው ነው፡፡ ሰይጣንም የሚሠሩትን ሥራ ጥሩ እንደሆነ ያሳያቸዋል፡፡

ሰይጣን ስለተቆጣጠራቸው እነዚህ ለአላህ (ሱ.ወ) አናቅጽ ምንም ግምት የማይሰጡት ሙናፊቆች ከእምነት ወደ ክህደት ሄደዋል፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው ይህ የነርሱ ባህሪይ በርካታ ገጽታዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡ ሆኖም በስተመጨረሻ ከሁሉም በስተጀርባ ያለው ዓላማና ፍላጎት ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህም የግል ጥቅማቸውን በተቻለው ፍጥነት ማባዛትና የሚችሉትን አደጋ አማኞች ላይ አድርሰው ከነርሱ መለየት ነው፡፡ ምንም ያህል ጊዜ ሙናፊቆች ከአማኞች ጋር ቢቆዩም በስተመጨረሻ እንደሚተዋቸው ያውቃሉ፡፡ ለመለየት የወሰኑት ጊዜ በአጠቃላይ የችግር ጊዜ ነው፡፡ እንደምናውቀው እያንዳንዱ ነብይ (ዐ.ሰ) የተላከው እምነት የሌላቸውን ሰዎች ለማስጠንቀቅ ነው፡፡ ባደጉበትና በለመዱት በአያቶቻቸው ሃይማኖት የሚኖሩት ከሀዲያን ሁሌም እነዚህን የተመረጡ ሰዎች ተቃውመዋል፡፡ እንዲሁም ማመን ሲገባቸው በክህደት ላይ ጸንተዋል፡፡

በርካታ አካላዊና የቃላት ጥቃቶችን በማድረስ ተጽዕኖአቸውን ለማስወገድ ጥረዋል፡፡ ሆኖም በታሪክ ሂደት ውስጥ የዚህ ዓይነት ባህሪን ያሳዩ ከሀዲያን በሙሉ ዓላማቸውን አላሳኩም፡፡ በተደበቀው ሕግ ምክንያት በዚህችም ሆነ በቀጣዩ ዓለም ተስፋ ቆርጠዋል፡፡ ይህ የተደበቀ ሕግ አማኞች በአላህ (ሱ.ወ) ጥበቃ ሥር የመሆናቸው እውነታ ነው፡፡ ከሀዲያን በፈጹም ሊጎዷቸው አይችሉም፡፡ በአንቀጾቹ የሚከተለው ተነግሮናል፡፡

*አላህም ከሀዲያንን በአማኞች ላይ የበላይ ፈጽሞ አያደርግም፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረህ አን-ኒሳእ፡141)*

ሆኖም ከሀዲያን ይህን ሕግ አይረዱትም፡፡ ሁሌም መልዕክተኞችንና አማኞችን ለመጨቆንና ወደራሳቸው ሃይማኖት ለመቀየር ሞክረዋል፡፡ የከሀዲያንን ትንኮሳ የሚፈሩት ሙናፊቆች ሁሌም ከትግል ለመቅረት የአማኞችን ፈቃደኝነት ጠይቀዋል፡፡ በዚህ ሁኔታም በመሸሸ እራሳቸውን ማዳን እንደሚችሉ ያስባሉ፡፡ ነገር ግን ምንም ያህል ተጠቅመናል ብለው ቢያስቡም ሙናፊቆች በእንደዚህ ዓይነት ባህሪያቸው በቀጣዩ ዓለም አስከፊ ደረጃን ይይዛሉ፡፡ በዚህች ዓለም ጊዜያቸው

አንዴ እንኳን ተውበት ለማድረግ አስበው አያውቁም፡፡ እውነት ላይ ልባቸውን በማጠንከር በቁርአን ቃላት እነዚህ ሰዎች "እንደ አለት ወይም ከዚያ በላይ የጠጠሩ" (ሱረህ አል-በቀራህ፡74) እንደሆነ ተገልጾዋል፡፡

ከአላህ (ሱ.ወ) ርቀውና በርሱ ሃይማኖት ላይ ታላቅ ጦርነት አውጀው ኖረዋል፡፡ ለዚያ ነው በቀጣዩ ዓለም እጅግ የሚዋረዱት፡፡ እነሱን ለማስጠንቀቅ ነብያት (ዐ.ሰ) ተልከው ነበር፡፡ እውነትም ተነግሯቸዋል፡፡ እንዲሁም ኃጢአት እንዳይሠሩ ተከልክለው ነበር፡፡ ስለጥሩና መጥፎ፣ እንዲሁም ለአላህ (ሱ.ወ) ስለመኖር ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ነገር ግን አሁንም ጀርባቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአላህን መኖርና ኃይል መረዳት ስላልቻሉ የቅጣት ማስጠንቀቂያ አያስደነግጣቸውም፡፡ በጀሀነም መኖር ባለማመን ከርሱ የራቁ ይመስላቸዋል፡፡ እንዲሁ ሙሉ ለሙሉ ሐሳባዊ ቦታ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

የቀጣዩ ዓለም ጉዳይ ሲነሳ ነብሳቸውን የበከለው የራስ መብቃቃት በሽታ ራሱን ይገልፃል፡፡ ስለቅጣት አያስቡም፡፡ የዚህ ዋነኛ ማስረጃ በቀጣዩ ዓለም ስለመቀጣታቸው እንኳን በፍጹም አለማሰባቸው ነው፡፡ ነገር ግን በቀጣዩ ዓለም ስለሠሩት ሥራ ስለመጠየቅ ለጥቂት ጊዜ እንኳን ማሰብና አንድ ሰው በሠራው ኃጢአት ምክንያት ጀሀነም ሊገባ እንደሚችል ማሰብ ያለውን ፋይዳ ብንመለከት አንድ ነገር እንዲሠራ ወይም ቢያንስ እንኳን ስለራሱ እንዲያስብ ያደርገዋል፡፡ በሃይማኖታዊ የሥነ-ምግባር እሴቶች ላይ ጦርነት ማወጃቸው ይህን የማይቀር እውነታን እንደዘነጉት ያሳያል፡፡

ሆኖም በራሳቸው መብቃቃታቸው በዚህ ዓለም ላይ ከውርደት ውጪ ምንም አያመጣላቸውም፡፡ በሌላ በኩል በቀጣዩ ዓለም የናቋቸው ተግባራትን ቅጣት ያገኛሉ፡፡ እንዲሁም ለተግባሮቻቸው ይረገማሉ፡፡ በጥረታቸው ውጤት የሚገባቸው ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የሙናፊቆችን ዕጣ ፋንታ እንደሚከተለው ገልፆታል፡-

*ሰማያትና ምድርም እስካሉ ድረስ በውስጧ ዝንተ ዓለም ይኖራሉ፡፡ አላህ የሻባቸው ሲቀሩ፡፡ ጌታህ የሚሻውን ሠሪ ነውና፡፡ (አል-ቁርአን፣ ሱረቱ ሁድ፡107)*

# በአላህ ፈቃድ ተጠናቀቀ!!

ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ (ሱ.ወ) የተገባ ይሁን፡፡ የአላህ (ሱ.ወ) ሰላምና እዝነት በባሪያውና በመልዕክተኛው ሙሐመድ ላይ ይሁን፡፡ እንዲሁም ሰላም በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና የሐቅን መንገድ እስከ ፍርዱ ቀን በቅንነት በሚከተሉት ሁሉ ላይ ይሁን፡፡